# የሥነ - ጥበባት ትምህርት

# የመምህራን መምሪያ 8ኛ ክፍል


## አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች

ደነደአ ቦጋለ

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

## አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች

ዳሜ ቶሊና

ሉባባ ጃማል

ታደሰ ድንቁ

## በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሰን

## ተርጓሚዎች

ደቀቦ ጉዬ

ድርባ ማሞ

እስማኤል ሐሰን

## የጥራት ቁጥጥር

ደቀቦ ጉዬ

## ግራፊክስ

ታደሴ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምዕራፍ 1: ጥበባዊ ግንዛቤዎች 1

**1.1 የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ድርሻና ጥቅሞች** ........ 2

1.2 የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶች፣ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝት እና ውዝዋዜ ........ 8

1.3 የትያትር እና ፊልም ጥበብ ፕሮዳክሽን አላባውያን ........ 17

ምዕራፍ 2 የፈጠራ ችሎታ ........ 28

2.1. ሶልፌጅዮን በኢትዮጲያ ሙዚቃ ቅኝት (አንቺ ሆዬ ለኔ እና አምባሰል) ........ 29

2.2 ባህላዊ ውዝዋዜ ........ 39

2.3 የትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን (ፈጠራ፣አጭር ታሪክ መፃፍና መመዘን) ........ 41

2.4. የህትመት ስራ እና ቅርፃ ቅርፅ ........ 44

ምዕራፍ 3: የስነ-ጥበባት ባህልና ታሪክ ........ 59

3.1 የሙዚቃ ባህላዊ ገጽታ፣የሙዚቃ መሳሪያና ዉዝዋዜ ........ 60

**3.2 ቅርጻቅርጺ (የሃዉልት) ጥንታዊ የእጅ ስራ ታርክ** ........ 63

**3.3 በአከባቢያችን የሚታወቁ ተረቶችን በትያትርና ፊልም/ምስለ-ድምጽ መቅረብ፡፡** ........ 74

ምዕራፍ 4 : የስነ-ጥበብ መስህብነት ........ 77

**4.1. የስነ-ጥበባት ስራዎችን በተግባር የማስተማር ጥቅሞች** ........ 78

**4.2. በተግባር የምታዩ ስነ-ጥበባትን ማነጻጸር (ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣የትያትር እና የፊልም ስነ-ጥበብ)** ........ 81

4.3 የሃዉልት እና የጥንት ዘመን የእጅ ስራ ሙያ ምልክቶች መልእክት ........ 84

ምዕራፍ 5: የስነ-ጥበባት ትስስር ........ 99

5.1. የስነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርት ዓይቶችና ከወቅታዊ ጉደይ ጋር መያያዝ ........ 99

የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ ........ 108

# አጠቃላይ መግቢያ

በመማር እና ማስተማር ሂደት ውስጥ፤ የእያንዳንዱ ተማሪ ተሳትፎ እንዳይወሰን፤ መምህር የሁሉም ቡድን ተሳትፎ መከታተል፣ ማገዝ፣ መምራት እና ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን በትምህርት ሂደት ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ሃሳብ በመስጠት፣ በመወያየት፣ በመከራከር፤ ያገኙትን ዕውቀት፣ ግንዛቤና ያላቸውን ሙያ በመለዋወጥ፤ የሚፈለገዉ የትምህርት ውጤት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አለባቸዉ፡፡ መምህራን ይህንን የስነ-ጥበብ ትምህርት ሲያስተምሩ መግቢያ፣አቅርቦት፣ማጠቃለያ እና ከማቀድ በፊት የሚከናወኑ ድርጊቶች በስርዓት ማዘጋጀት እና መፈፀም አለበቸው፡፡.

## *1. በመግቢያ የሚከናወኑ ድርጊቶች*

ተማሪዎች ያለፈዉን የትምህርት ይዘት በደንብ መማራቸዉን ለማረጋገጥ፤ መምህር የተለያዩ ከትምህርቱ ጋር የተያያዙትን ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እና ከዕለቱ ትምህርት ጋር ማያያዝ አለበችዉ፡፡ በተለይ የተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ እንዲሰጡ እድል መስጠት፡፡ መልስ ያላገኙ ጥያቄዎች ደግሞ ጎበዝ ተማሪዎቸች መልስ እንዲመልሱ በማድረግ፤ ሁሉም ተማሪዎች በትኩረት እንዲከታተሉ፣ አእንዲሳተፉ፣ እንዲዘጋጁ እና ተወዳዳሪ በመሆን በትምህርት እንዲበረቱ አድርጉ::

ከእለቱ ትምህርት ጋር በተያያዘ፤ ተማሪዎች ያላቸዉን የቀድሞ እዉቀት ለማወቅ፤ አስፈላጊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች አስቦበት እንዲመልሱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም የዕለቱን ትምህርት ጥቅም፣ አስፈላጊነት እና አላማ ጋር በማስተዋወቅ ለእለቱ ትምህርት እንዲዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## *2. በአቅርቦት የሚከናወኑ ድርጊቶች*

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በትምህርት አቅርቦት ጊዜ፡-

- የይዘቱ ሁኔታ እና በዓላማ ላይ በመመስረት፤ ዉስን የሆኑ የተማረዎች ቡድን በማደራጀት እና በዉይይት ርዕስ ላይ እናዲወያዩ መምራት፡፡
- የውይይት ርዕስ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑን፤ ለቡድን በተዘጋጀ ጥያቄ መሰረት በሳሌዳ ላይ መፃፍ፡፡
- መምህር በዱድን ውስጥ ተማሪዎች መማራቸዉን መከታተል፣ መምራት እና ማገዝ አለበችዉ፡፡

- የእያንዳንዱ ተማሪዎች በቡድን እና በክፍል ውስጥ ያላቸዉን ተሳትፎ መከታተል እና ማበረታታት፡፡
- በጥንድ ወይም በዉስን ቁጥር ቡድን የተወያዩበትን/ የሰሩትን እያንዳንዱ የቡድን አባላት፣ ተራበተራ በተለያዩ ትምህርት ጊዜ እንዲያብራሩ በማድረግ፣ ተሳትፏቸዉ እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡
- የውይይቱ አንኳር ነጥብ ወይም ከሰሩ በኋላ ተማሪዎች ያቀረቡትን በሳሌዳ ላይ መፃፍ፡፡
- የትምህርቱ ይዘት ከአከባቢያቸዉ ጋር በማያያዝ፣ በመርጃ መሳሪያ በመጠቀም የእለቱን ትምህርት መተንተን፡፡

### 3.በማጠቃለያ የሚፈፀሙ ድርጊቶች

- የእለቱየትምህርት ዓላማ ስኬት ለማረጋገጥ፣ የክፍል ስራ፣የቤት ስራ ፕሮጀክት እና የመሳሰሉትን በቡድን፣በጥንድ ወይም ለብቻቸዉ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- የቤት እና የክፍል ስራለሰሩ ተማሪዎች አስፈላጊ ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- የክፍል ስራ፣የቤት ስራ ፕሮጀክት እና የመሳሰሉትን መልስ መስጠት እና መስራት ያቃታቸዉን ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎች የሚቀጥለዉን የትምህርት ክፍል አንብበዉ እንዲመጡ መምራት

## ሀ. ትምህርት ከማቀድ በፊት

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የስነ-ጥበባት መምህራን እዉቀት፣የትምህርቱን ይዘት ግንዛቤ ለማጎልበት እንዲሁም ሙያቸዉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሳደግ አለባቸዉ፡፡ ማንኛዉም የተማረ ሰዉ የማያነብ/ የማይለማመድ ከሆነ፣ በሚያስተምርበት ትምህርት መርሳቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ እሂንን ክፍል የሚያስተምሩ የስነ-ጥበባት መምህራን ከታች የተዘረዘሩትን የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡

- ለዕለቱ የታቀደዉን የትምህርት ይዘት ወይም ለማስተማር የተያዘዉን በደንብ ማንበብ እና መረዳት፡፡
- ትምህርቱን ለማስተማር ካቀዱት ጋር የተያያዘዉን ከተማሪዎች መፅሐፍ ማስታወሻ መያዝ፡፡ .
- ለዕለቱ ትምህርት በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የተገለፁት ነጥቦች ወይም ሃሳቦች በቂ ካልሆኑ፣ የዋቢ መፅሐፍ በመጠቀም ተጨማሪ ነገር ማግኘት ይቻላል፡፡

- ተግባራት፣ ሙከራ፣ መልመጃዎች እና በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ ያለዉን ሁሉም የምዕራፍ ክለሳ ጥያቄዎችን ቀድመዉ መስራት፣ መሞከር እና መለማመድ አስፈላጊ ነው፡፡

# ምዕራፍ 1: ጥበባዊ ግንዛቤዎች

## የስነ-ጥበባት ግንዛቤዎች

*ለዚህ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ............24*

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤት:**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:

- የቅርፃ ቅርፅ ምንነት እና ትርጉም ይገልፃሉ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ አላባውያንን በመለየት ይዘረዝራሉ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ጥቅሞችን ይገልፃሉ፡፡
- የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያ አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝትና ውዝዋዜ ባህሪያትን ያብራራሉ፡፡
- ለትያትርና ፊልም ጥበብ ዝግጅት የሚያስፈልጉ አላባውያንን ይዘረዝራሉ፡፡
- በትያትር ጥበብ ውስጥ የልብስ እና የመብራት ሚናን ይገልጻሉ፡፡

**መግቢያ**

የቅርፃ ቅርፅ ሥራ የስነ-ጥበብ ስራዎች ከሚሠሩባቸው መንገዶች ወይም ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ እንደ አሁኑ ጊዜ በስልጣኔ ዕድገት ምክንያት የቴክኖሎጂ ውጤት ከመስፋፋታቸው በፊት የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮውን ለመምራትና ለመሻሻል በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተለያዩ ነገሮችን በመስራት ይገለገልበት ነበር፡፡ የቅርፃ ቅርፅ ጥበብ እድገትም ከዚሁ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

በሰበተኛ ክፍል የስነ-ጥበብ ትምህርት ውስጥ ስለ ሙዚቃ ባህሪያትና ባህላዊ ውዝዋዜ፣ ስለ ሶልፌጅዮና የሃገራችን የሙዚቃ ቅኝት፣ ስለ ኦሮሞ ሙዚቃ ታሪክ፣ ስለ ሃገራችን አንጋፋ ሙዚቃኞችና ተወዛዋገሮች፣ እንዲሁም ስለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና በሙዚቃና በሌሎች የትምህርት መስኮች ያለውን መስተጋብር ተምረቸዋል፡፡ በዚህ ክፍል ትምህርት

ውስጥ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ሶልፌጅዮ፣ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝትና የሙዚቃ ባህላዊ አቅጠጫ ምን እንደሆነ ትማራላችሁ፡፡ ባለፈው ትምህርት ውስጥ ስለ ትያትር፣ የትያትር አጀማመርና ዕድገት እንዲሁም ትያትርና ድራማ ያላቸውን ልዩነት ተረድታችሁ ነበር፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ የስነ-ትያትርና የስነ-ፊልም ፕሮደክሽ ሂደቶችን ትማራላችሁ፡፡

**የምዕራፉ አንኳር ይዘቶች፡-**

- *1.1.* ***የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ድርሻና ጥቅሞች***
- 1.2. የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶች፣ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝትና ውዝዋዜ
- 1.3. የትያትር ጥበብ እና የፊልም ጥበብ ፕሮዳክሽን አላባውያን

## 1.1 የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ድርሻና ጥቅሞች

***ለዚህ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ--------------------6***

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**:

**በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡**

- ቅርፃ ቅርፅ ምን እንደሆነ ያብራራሉ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ ባህርያትን ይዘረዝራሉ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ አላባውያንና ያላቸውን ጥቅም ይገልፃሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- ጉብኝት/ምልከታ
- ማሳያ (በተግባር ማሳየት)
- ልምምድ
- የቡድን፣ የጥንድ እና የሙሉ ክፍል ውይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ለዚህ የትምህርት ርዕስ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-

- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ከሰል፣ ክራዮን እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች
- ቻርት
- ፖስተር
- ሞዴል

### የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎች ስለ ቅርፃ ቅርፅ አላባውያን አይነቶች፤ በፊት የነበራቸዉን ግንዛቤ እንድገልፁ በመጠየቅ፤ የዚህን ምዕራፍ ትምህርት መጀመርና ማስተማር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች የቅርጻ ቅርጽ አላባውያን አይነቶች፣ ትርጉም እና ጥቅም ላይ እንዲወያዩ በማድረግና የዉይይታቸዉን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

- በያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፤ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፤ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
  - በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
  - ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡
  - መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
  - መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ከሰሩ እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**የተከታታይ ምዘና ስልቶች/ዘዴዎች**

- የግል እና የቡድን ዕብረቃ
- ፖርትፎሊዮ/ዘገባ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ፈተና
- ፈተና
- የግል እና ቡድን ፕሮጀክት ስራዎች

*1.1.1. የቅርፃ ቅርፅ ትርጉም*

*ተግባር 1*

በተማሪ መጸሀፊ ውስጥ የውይይት ነጥቦችና ድርግቶች በተመለከተ ተማሪዎች በርዕሱ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ለይ በመመርኮዚ ተጨማሪ ገለፀና ግብረመለስ ስጡአቸዉ፡፡

*ተማሪዎቸች የሸክላ አፈር፣ ካርቶኒ  እና የመሳሰሉትን ነገሮችን በመጠቀም  የሰዉ፣ የእንስሳት፣የመኪና፣ የቤት እና የመሳሰሉትን ሰርተዉ ተጫዉተዉ የሚያዉቁ እንደሆነ ጠይቁቸዉ፡፡  ሰርተዉ የሚያዉቁ ከሆነ፤ ከሸክላ አፈር የሰዉ ቅርፃ ቅርፅ ወይም እንስሳት እንዲሁም ከካርቶኒ እና ሌሎች ነገሮች መኪና ወይም ቤት የሚሰራ ሁሉም የቅርፃ ቅርፅ ስራዎች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ህፃናት ከልጅነታቸዉ ጀምረዉ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን በመጠቀም ሲሰሩ የነበሩት ነገሮች ቅርፃ ቅርፅ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከሚያዉቁት ነገር በመነሳት፤ ከእለቱ ይዘት ጋር በማያያዝ የራሳቸውን ሃሳብ እንዲሰጡ በማድረግ በተማሪዎች ሃሳብ ላይ ግብረ መልስ ስጡዋቸው፡፡ በመቀጠል የቅርፃ ቅርፅ ትርጉምን እንደሚከተለዉ አብራሩላቸዉ፡፡*

ቅርፃ ቅርፅ የስነ-ጥበብ ስራዎች ከሚሰሩባቸው ዘዴዎች አንዱ ሲሆን፤ የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ አኗኗሩን ውብ እና ምቹ ለማድረግ በአከባቢ የሚገኙ ነገሮችን በመጠቀም

እንዲሁም በቀጥተም ሆነ በተዘወዋዋሪ የተለያዩ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎችን ሲሰራ እንደ ነበር አስረዱ፡፡

ይህም የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እንደ አሁኑ ስልጣኔ ሳይስፋፋና የተለያዩ መሳሪያዎችን ሰርቶከመጠቀሙ በፊት፤ በአከባቢ የሚገኙ ቀላል የሆኑ ነገሮችን በመቅርፅ እና በመጥረብ ስጠቀምበት ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ከድንጋይ፣ እንስሳት አጥንት፣ እንስሳት ቀንድ፣እንጨት እና የመሳሰሉትን ቀርፀዉ (ቅርጽ በማውጣት) እንደ ጦር፣ ብለዋ እና የመሳሰሉትን ሰርተው ይጠቀሙበት እንደነበር በደንብ አስረዱ፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች ከዚህ በላይ የቀረበዉን የቅርጻ ቅርጽ ትርጉም በዚህ ሁኔታ የተረዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ ከዚሁ ጋር የሚያያዙ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

**ተግባር 2**

ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ ሰዎች እንጨት በመጥረብና በመላግ ቀንበር፣ ሙቀጫ፣ ወንበር እና የመሳሰሉትን ስጠርቡ አይተው እንደሆነ ጠይቁ፡፡ አይተዉ የሚያዉቁ ከሆነ፤ እንዴት እንደሚጠረብ /እንደሚሰራ ለክፍል እንዲያብራሩ አድርጉ፡፡ በመቀጠል የተማሪዎችን ሃሳብ ከተቀበሉ በኋላ፤ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት ለአጠቃላይ ሃሳብ ከዚህ በታች በተሰጠው ሃሳብ መሠረት አስረዱ፡፡

የመጥረብ/የመላግ ሙያ ቅርፃቅርፅ ከሚሰሩባቸው መንገዶች አንዱ ሆኖ፤ ይህም መጠረብ ወይም መላግ የሚችሉ ነገሮችን በመጠቀም የሚሰሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ድንጋይ፣ እንጨት፣ የዝሆን ጥርስ፣ አጥንትና የመሳሳሉትን በመጥረብ ወይም በመላግ ቅርፃ ቅርፆች መስራትን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ሂደትም ሰዎች የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠቀም ቅርፃ ቅርፅን እንደሚሰሩ ካስረዱዋቸው በኋላ ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ገለፃ የተገነዘቡ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

**ዉይይት 1**

*ተማሪዎች የቅርጻ ቅርጽ አላባውያን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን በመሆን ሃሳብ ከተለዋወጡ በኋላ፤ ለክፍል እንዲያቀርቡ አበረታቱ፡፡ ተማሪዎቹ ለክፍል ከአቀረቡ በኋላ፤ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት ለአጠቃላይ ሃሳብ ከዚህ በታች በተፃፈ መሰረት አስረዱ፡፡*

በጥቅሉ ሲታይ የሥነ-ጥበብ አላባውያን ለአንድ ጥበብ ስራ መፈጠር ምክንያት እንደሚሆኑ ሁሉ፤የቅርፃ ቅርፅ አላባውያንም ለቅርፃ ቅርፅ ወይም ፎርም መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ አንድን ቤት ለመስራት ድንጋይ፣ ጭቃ፣ እንጨት፣ ብረት፣ ሲሚንቶ፣አሸዋ፣ቆርቆሮ ወይም ሳር እና የመሳሰሉት አስፈላጊ እና ወሳኝ እንደሆኑና ከነዚህ ነገሮች ውጪ ቤት መስራት እንደማይቻል ይታወቃል፡፡ እንደዚሁ ከቅርፃ ቅርፅ አላባውያን በስተቀር የቅርፃ ቅርፅ ስራ ወይም ፎርም መስራት አይታሰብም፡፡ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎች የሆኑት ለቤተ-እምነት፣ ለመስዕብ፣ለመታሰቢያ፣ገቢ ለማስገኘት፣ታሪክን ለመግለፅ እና ለመሳሰሉት የተሰሩ ነገሮች ሁሉ የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ውጤት መሆናቸውን አስረዱ፡፡ በመቀጠልም የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን የሚባሉት የሚከተሉት መሆናቸውን ንገሩዋቸው፡፡ እናሱም፡-

- ቦታ
- ይዘት/ መጠን
- መስመር
- ገፅታ/የገፅ አካል
- ቅርፅ
- የቀለም ንጣት እና መደብዘዝ/ value/
- ሸካራነት እና ለስላሳማነት
- ቀለም ናቸው፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ውስጥ መሰረታዊ የሆኑት ቦታ እና መጠን/ይዘት መሆናቸውን አስረዱ ፡፡ በመጨረሻም በዚህ መልክ የቅርፃ ቅርፅ ባህርያት ጥቅም እና ትርጉም ካስረዳችሁ በኋላ፤ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፤ ተያያዥ የሆኑ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

*ተግባር 3*

*ተማሪዎች ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራባቸዉ ነገሮች ምን እንደሆኑ እንዲዘርዝሩ ጠይቋቸዉ፡፡ የተማሪዎችን መልስ ከተቀበሉ በኋላ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት ለአጠቃላይ ሃሳብ ከዚህ በታች በተፃፈ መሰረት አስረዷቸዉ፡፡*

ቁመት፣ ርዝመት እና ወርድ ያላቸው ነገሮች ሆነው፤ በሁሉም አቅጣጫ መታየት የሚችሉ ነገሮች ሁሉም የቅርፃ ቅርፅ ስራዎችን ለመስራት እንደሚያገለግሉ ለተማሪዎች

ይገለፁላቸው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ቅርፃቅርፅ የሚሰራባቸዉ ነገሮች የሚከተሉት መሆናቸውንም አስረዱ፡፡ እነርሱም፡-

- ድንጋይ
- ብረት
- ብር
- ወርቅ
- ነሃስ
- ሸክላ አፈር
- ሰም
- እንጨት
- ፕላስትክ
- ወረቀት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በዚህ ሁኔታ ለተማሪዎቹ ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራባቸዉን ነገሮች ከአስረዱዋቸዉ በኋላ፤ቅርፃ ቅርፅ ከምን እንደሚሰራ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፤ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡.

**ልምምድ 1**

በዚህ ምዕራፍ ከቀረባው ትምህርት ስለ ቅርፃቅርፅ ትርጉም እና ምንነት፣ አለባውያን እንዲሁም ቅርፃቅርፅ ስለሚሰራባቸው ነገሮች ተምሯል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራባቸዉን ነገሮች ከአከባቢያቸዉ በመፈለግ፤ መኪና፣ቤት፣ሰዉ፣እንስሳት እና የመሳሰሉትን በግላቸዉ ሰርተዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ ከአቀረቡ በኋላ የስራቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ከመምህራቸውና እና ከክፍል ተማሪዎች ጋር ማስተካከያ ሃሳብ እንድቀበሉ ያድርጉ፡፡ የሚቀበሉት የማስተካከያ ሃሳብ ለሚቀጥለዉ ስራ እንደ ግብዓት እንደሚያገለግላቸው በመንገር ገንቢ ሃሳብ ስጡዋቸዉ፡፡

1.2 የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶች፣ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝት እና ውዝዋዜ
**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ…………………..3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች**

- የሀገራችንን የሙዚቃ ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፡፡
- የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ቅኝት ይለያሉ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

መምህር/ት፡ አንድን ዘፈን ለመስራት ወይም ለማቀናጀት ዋና እና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ለሚል ለግንዛቤ በቀረባላቸው ጥያቄ ላይ ከተወያዩበት በኋላ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍላቸው እንዲገልፁ አድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- የጥንድ፣ የቡድንና የሙሉ ክፍል ውይይት
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- በተግባር ማሳየት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

የዚህን የትምህርት ርእስ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡

- ከበሮ
- ሙዝቃ የተቀዳበት ካሴት(CD)
- ቴፕ (ዘመናዊ ሞባይል)

**የመምህር ድርሻ**

- ተማሪዎች በሰባተኛ ክፍል የተለያዩ የሙዚቃ ይዘቶች የተማሩትን እንዲገልፁ በመጠየቅ ይህንን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡

- ተማሪዎች በሙዚቃ ትርጉምና በሙዚቃ ዓይነት ላይ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩበት በማድረግ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘናና ክትትል**

- በዚህ ርዕስ ስር የተጠቀሱት ሃሳቦች ጋር የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት/ችሎታ መያያዝ ትምህርቱን ለመረዳት ስለሚያገለግላቸው በቡድን በመመካከር ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- የተማሪዎችን ስራ ለእያንዳንዱ ተማሪ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## 1.2.1. ትላልቅ የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶች

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ………3

ተማሪዎች ቢያንስ መጎነፀፍ የሚገባቸው ብቃት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የሀገራችን የሙዚቃ አይነቶችን ይገልፃሉሁ፡፡
- የሀገራችን የሙዚቃ አይነቶችን ይናገራሉሁ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- በግንባር መስተማር

- የቡድን፣ የጥንድ እና የሙሉ ክፍል ውይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ
- ልምምድ

## *የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች*

ለዚህ የትምህርት ርዕስ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-

- ስዕሎች
- በካሴት የተቀዱ ባህላዊ ሙዚቃዎች

## *የተከታታይ ምዘናና ክትትል*

- የቃል ጥያቄ
- የቤት ስራ
- የሙከራ ፈተና
- የቡድን ስራ

የመምህሩ ድርሻ

- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ባለፈው የትምህርት ርዕስ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ የሙዚቃ አይነቶች የተማሩትን እንዲገልፁ በማድረግ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የቅርጻ የሙዚቃ መሳሪያዎች አይነት ላይ እንዲወያዩ በማድረግና የዉይይታቸዉን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያ በኋላ በትምህርቱ ይዘት ላይ እንደሚከተለው ገለፃ መስጠት ይቻላል፡፡

1. **የገዳ ዘፈን** ፡ የገዳ ዘፈን የገዳ ስርዓት በሚፈጸምበትና በሚከበርበት ጊዜ ቅደም ተከተል ባለዉ ስርዓት ሁኔታዉን ጠብቆ የሚዘፈን ነው፡፡

2. **የአቴቴ ዘፈን**: ይህ ዘፈን ድርቅ በሚረዝምበት ጊዜ፣አቴቴ በሚዘሩበት ጊዜ፣አራስ ሴት በምትመታበት ወይም በምትገረፍበት እና በመሳሳሉት ጊዜ የሚቀርብ ነው፡፡
3. **ማህበራዊ ዘፈን**: ይህ ዘፈን አንድ ማህረበረሰብ ማህበራዊ የሆኑ ሁኔታዎችን በሚያካሄድበት ጊዜ የሚዘፈን ነው፡፡ይህምለሰርግ ፣ለልደት ፣በበዓላት ፣ በዘን እና በመሳሰሉት ጊዜ የሚቀርብ ነው፡፡
4. **የስራ ዘፈን**: ይህ ሰዎች በስራ ላይ በሚረዳዱበት ጊዜ የሚቀርብ ዘፈን ነው፡፡ ለምሳሌ፤
    - እህል ሲያጭዱ
    - መኖሪያ ቤት በሚሠሩበት ጌዜ
    - ቡና በሚለቀምበት፣ ሴቶች ተሰብስበው እህል በሚወቅጡበት ጊዜና ሰዎች በጋራ በመሆን የተለያዩ ስራዎችን አብረዉ በሚሰሩበት እና በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚዘፈን ነው፡፡
5. **የፖለቲካ ዘፈን**፡ይህ ዘፈን ሰዎች ፖለቲካንለመቀስቀስ ለመደገፍ ወይም ለመቃወም የሚጠቀሙበት ነው፡፡
6. **ዜማ**: የተለያዩየዜማ ዓይነቶች ብኖሩትም አብዛኛዉን ጊዜ በቤተ-ዕምነቶች ውስጥ፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለትምህርት ጉዳይ ፣ስለ ሀገር ለማዜም፣ከብቶችን ሲጠብቁ እና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚጠቀሙበት ነው፡፡
7. **ጌረርሳ/ቀረርቶ**: ጌረርሳ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በአብዛኛዉ የሚታወቅና ለየት ባለ መልክ የሚጫወቱት ነው፡፡ጌረርሳ የአንድን ሰው ጀግንነት ወይም ብርታትን ለመግለጽ የሚጫወቱት ነው፡፡ እንደ ኦሮሞ ባህል ጌረርሳ የሚዜመዉ/የሚቀርበው አዋቂ በሆኑ ሰዎች ሲሆን እሱም ከአንድ ምክንያት ጋር በማያያዝ ይዜማል፡፡ ጌረርሳ አብዛኛዉን ጊዜ የሚዜመዉ በጦር ግንባር ተዋጊዎችን ለማበረታታት፣ የራሳቸዉን ጀግንነት ለመግለጽ፣ የራሳቸዉን ጎሳ (ዘር)ለማወደስ ወይም ለመግለጽና ለመሳሰሉት ነው፡፡
8. **ዘመናዊ ዘፈኖች**:ዘመናዊ ዘፈኖች በዘመናዊ መልክ ለተለዩ ጉዳዮች ለምሳሌ ለንግድ፣ለመዝናናትና ለመሳሰሉት በሙዚቃ መሳሪያ ተቀነባብረዉ የሚቀርቡ ናቸው፡፡

### 1.2.2. የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ……………………..3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉ የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- የሃገራችን የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለይተዉ ይገልፃሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ ከምገኙ ቁሳቁሶች የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎችን ሰርተዉ ያሳያሉ፡፡

**የተግባር 4 መልስ**

ከሀገራችን የሙዚቃ አይነቶች የተወሰኑት የገዳ፣ የአቴቴ፣ የስራ፣ ቀረርቶና የመሳሳሉት ናቸው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- የጥንድ፣ የቡድን እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት ማስተማር
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- የፕሮጀክት ዘዴ
- ልምምድ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

**የዚህን ርእስ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡**

- ስዕሎች
- የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች

**የመምህር ድርሻ**

- ተማሪዎች በሰባተኛ ክፍል የተለያዩ የሙዚቃ ይዘቶች የተማሩትን እንዲገልፁ በመጠየቅ ይህንን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በሙዚቃ መሣሪያ ዓይነቶች ላይ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩበት በማድረግ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

- በተጨማሪም ቀጥሎ ያለውን ይዘት በመጀመሪያ በማንበብ ከተዘጋጁ በኋላ ቀጥሎ በተሰጠው ሃሳብ መሠረት ለተማሪዎች ይግለፁላቸው፡፡

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በዓለም ላይ ስራ ላይ መዋል ከጀመሩ ዓመታትን አስቆጥረዋል፡፡ እንዲሁም በሃገራችን ውስጥም ለብዙ አመታት ስራ ላይ ሲውሉ የነበሩና አሁንም አገልግሎት እየሰጡ ያሉ በርካታ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዳሉ ለተማዎች ይንገሩዋቸው፡፡ በተጨማሪም በሀገራችን የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያች  በሶስት ትላልቅ ቦታዎች እንደሚከፈሉ ያስረዱዋቸው፡፡

እነርሱም፤

- የምት(በመምታት ድምጽ የሚያወጡ)
- የትንፋሽ (በመንፋት ድምጽ የሚያወጡ)
- የክር(በመገዝገዝ ወይም መምቻን በመጠቀም ድምጽ የሚያወጡ)

**ተከታታይ ምዘና**

- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉ መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የተግበር 5 መልስ**

የምትና የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል ያለዉን ልዩነት በቡድን ከተወያዩ  በኋላ ለክፍል እንድያቀርቡ አድርጉ፡፡  በተጨማሪም የምትና የትንፋሽ ሙዝቃ መሣሪያ ይዘት

ለይ በደንብ በመዘጋጀት መስታወሻ በመስጣት ግለፁላቸው፡፡ ተማሪዎችም በአከባቢያቸዉ ከሚገኙ ነገሮች አንድ የትንፋሽ  ሙዚቃ መሣሪያ ሰርተዉ እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ክራር ከምን እንደሚሰራ በመዘርዘር የአሰራሩን ቅድም ተከተል በቡድን ተወያይተዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡

**የተግባር 6 መልስ**

እንጨት፤ ጎድጋዳ ሰህን፣ ክር፤ እኩል ዉፍረት የላዉ ሽቦ፤ የፍየል ቆዳ፤ ምስማርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**የክራር አሰረር ቅድመተከተል**

- የምያሰፈልጉትን መሣሪየዎች መዘጋጀት
- ሁለት ለቋሚ የሚሆኑ እንጨቶችን ከ50ሰ.ሜ - 70ሰ.ሜ መቁረጥ
- ለአግድም የሚሆን እንጨት ከ30ሰ.ሜ-50ሰ.ሜ መቁረጥ
- የፍየል ቆዳ በሳህን ላይ ማሰር
- ቡርኩማ በማዘጋጀት ክሩን ላዩ ላይ ማሰር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 1.2.3. ቅኝትና ውዝዋዜ

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ..................................6**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-**

- የቅኝት ትርጉም እና ጥም ይገልጻሉ፡፡
- የቅኝትና ውዝዋዜ ግንኙነት ይዘረዝራሉ፡፡
- የተለያዩ ቅኝቶችን በማቃኘት ይጨወታሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ውይይት እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት ማስተማር
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ

- የፕሮጀክት ዘዴ
- ልምምድ

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

**ለዚህ ርእስ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-**

- የባህል ሙዝቃ መሣሪያዎች

**የመምህር ድርሻ**

- ተማሪዎች በሰባተኛ ክፍል የተለያዩ የሙዚቃ ይዘቶች የተማሩትን እንዲገልፁ በመጠየቅ ይህንን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በሙዚቃ መሣሪያ ዓይነቶች ላይ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩበት በማድረግ ርዕሱን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የቅኝትና የዉዝዋዜ ግንኙነት በጥንድና በቡድን እንዲዋያዩ በማድረግ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም ቀጥሎ ያለውን ይዘት በመጀመሪያ በራሳችን አንብበን ከተዘጋጀን በኋላ በተጨማሪ ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ  መግለፅ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ የሙዚቃ እስኬሎች እንዳሉ በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ  ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ካሉት እስኬሎች ውስጥ ፔንታቶኒክ እስኬል በስፋት ይታወቃል፡፡በዚህ እስኬል ስር ታዋቂ የሆኑ አራት ቅኝቶች  አሉ፡፡ እነርሱም፤

- የትዝታ ቅኝት
- የባቲ ቅኝት
- የአምባሰል ቅኝት
- የአንቺሆዬ ለኔ ቅኝት በመባል ይታወቃሉ፡፡

## ተከታታይ ምዘናና ክትትል

- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፣ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የተግባር 7 መልስ**

አራት ዓይነት ታዋቂ  እስኬሎች አሉት፣እነዚህም፣

- የትዝታ ቅኝት
- የባቲ ቅኝት
- የአምባሰል ቅኝት
- የአንቺሆዬ ለኔ ቅኝት በመባል ይታወቃሉ፡፡

**የተግባር 8. መልስ**

ተማሪዎች በቡድን በመሆን የፒያኖ ሰንትዘይዘር ቁልፍ ፣ሥዕል፣በካርቶን /በእንጨት ላ ይ በምያምር ሁኔታ በማንሳት ለክፍል ተማሪዎች በማሳየት እንዲያወደድሩ አድርጉ፡፡

## 1.3 የትያትር እና ፊልም ጥበብ ፕሮዳክሽን አላባውያን

**የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ---------------------6**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣**

- ለትያትርና ፊልም ጥበብ ዝግጅት የሚያስፈልጉ አላባውያንን ይዘረዝራ፡፡
- በትያትር ጥበብ ውስጥ የልብስ እና የመብራት ሚናን ይገልጻሉ፡፡
- የትወናን የልምምድ ዘዴ ይገልጻሉ፡፡
- የፊልም ጥበብ ዝግጅት ሂደትን ይናገራሉ፡፡

**የምዕራፉ  ዋና ዋና ነጥቦች**:

- የትያትር ፕሮደክሽን አላባዊያን
- ትወና ብቃት
- የፍልም ፕሮደክሽን አላባዊያን

**የይዘት ማብራሪያ /መግለጫ**

### 1.3.1. የትያትር ጥበብ ዝግጅት አላባውያን

የትያትር ጥበብ ተዘጋጅቶ በመድረክ ላይ ለተማልካቾች ለመቅረብ ብዙ ሂደቶች አሉት፡፡ ይህም ማለት የትያትር ጥበብ ዝግጅት በአንድ ሰውና በአንድ ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ሳይሆን በቡድን የሚሠራና ጊዜን የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ የትያትር ጥበብ ዝግጅት አላባውያን ማለት አንድ ትያትር ከዝግጅቱ ጀምሮ ለተመልካች ለመታየት እስኪበቃ ድረስ በውስጡ የሚያካትተቸዉ ናቸው፡፡ በትያትር ጥበብ ዝግጅት አላባዉያን ውስጥ መድረክ ላይ ወጥተዉ ትወናን ከሚያከናዉኑ ሰዎች ዉጪ ለዝግጅቱ የቴክኒክ ሥራ እንደ ተመረጠዉ የፈጠራ ሥራ ድረሻቸዉን በአግባቡ የሚወጡ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህም በትያትር ጥበብ ዝግጅት ውስጥ ደጋፊዎች ተብለዉ ይጠራሉ፡፡

በሌላ በኩል የትያትር ጥበብ ዝግጅት ወይም ፕሮዳክሽን ማለትአንድትያትር በብቃት ተቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያልፍበት ሂደት ማለት ነው፡፡ ይህም ሥራ ሁሉም ተወንያን በሙያቸዉ አንፃር የሚሳተፉበት ነው፡፡አንድ የትያትር ጥበብ ዝግጅት በሚሠራዉ ዝግጅት በመመስረት የሚከተሉት ነገሮች ያስፈልጉታል፡፡

- አልባሳት፣
- ሜክ አፕ/ገፅ-ቅብ
- ድምፅ፣
- የመድረክ መልክ
- ተዋንያን፣
- ተራኪ
- ከመድረከ በስተጀርባ ያሉ ባለ ሙያዎች፣
- ደጋፊዎች እና
- መብራት ናቸው፡፡

## ሀ. አልባሳት

ባለፈው ክፍለ-ትምህርትውስጥ ስለ ትያትር ጥበብ አጀማመር ታሪክ እንደተማራችሁ፣ ትያትር ሲጀምር በግሪክ ሀገር ውስጥ የዲትረም መዝሙር ቡዲን የዳይኖሰስ ሥርዓት ትዕይንትን ስያቀርቡ ከፍየል ቆዳ የተዘጋጀ ልብስ ለብሰው ስያቀርቡ ነበር፡፡ የትያትርጥበብ ዝግጅት አልባሳት ታሪክም ከዚህ ከፍየል ቆዳ ከተዘጋጀ ልብስ ታሪክ ይጀምራል፡፡

በሮማዉያን ትያትር ጥበብ አጀማመር ታሪክ ውስጥም ተወንያን ቀሚስ እና ሸርጥ በመልበስ ትያትር ያቀርቡ ነበር፡፡ እንደዚሁ በመካከለኛ ዘመንም ትያትር ስቀርብ ለትያትሩ የሚያስፈልግ ቀሚስ በማሰፋት ይጠቀሙበት እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡

በ1500-1600 ዓ. ም የኤልዛቤት ትያትር በመድረክ ላይ ሲቀርብ እንግሊዛዉያን በፋብሪካ የተመረተ አልባሳት ለብሰው ትያትሩን ስያቀርቡ ሌሎች አቅማቸዉ ለፋብሪካ ልብስ የማያበቃቸው በምፈለገው ልክ የሚያምር ልብስ መልበስ የማይችሉ ሰዎች የዘወትር ሥራ ልብሳቸዉን ለብሰው ትያትር ስያቀርቡ ነበር፡፡

ባጠቃላይ፣ የትያትር አልባሳት በልብስ ዲዛይን ጥበብ በተካነ ሰው እና በመድረክ ላይ ለሚቀርበዉ ትያትር ተካፋይ በሆነ ሰው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ስለዚህ የትያትር ልብስ ዲዛይነር የሚከተሉት ድርሻዎች ይኖሩታል፡፡

- ተዋንያን ለብሰው የሚያቀርቡትን ልብስ መለየት

- ልብስ ማዘጋጅት (ዲዛይን ማድረግ)እና
- ሰሰየተዋንያን  ልብስ ማቅረብ ናቸው፡፡

**ለ. ገፅ-ቅብ /መዋቢያ**

ገፅ-ቅብ/መዋቢያ በተዋናይ ፊት ላይ የሚሰራ ነገር ነው፡፡ ይህም በዝግጅቱ ላይ ተመስርተው የሚሰራ ነው፡፡ የተዋንያንን የአቋቋም ሁኔታ ለመቀየር የሚያግዝ ነው፡፡ አብዛኞቹ ዝግጅቶች መሰረታዊ የመዋቢያ ሜካፖች የሚጠቀሙ ቢሆንም አንዳንዶቹ እርጅና ለማሳየት፣ ህመምተኛ ለማስመሰል እና ለመሳሰሉት ሁኔታዎች ልዩ ሜካፕ ያስፈልጋቸዋል፡፡

**የመዋቢያ/ሜካፕ ጥቅሞች**

- በተዋናይ ፊት ላይ ጠባሳ ከተገኘ ለማጥፋት
- የተዋናይ ፊት በደምብ እንዲታይ
- ፊትን በመግለጽ ከድረጊት ጋር ለማወሃድ
- ተዋንያንን ማራኪ ለማድረግ
- ተዋንያን የሚፈልጉትን ድርሻ በነፃነት እንዲተዉኑ ለማድረግ

**ሐ. መብራት**

መብራት ልክ እንደ አልባሳት በመብራት በለሙያ ለትያትሩ እንደሚመች ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡ መብራት በመድረክ ላይ ተዋንያን ከመሳየት ጀምሮ የትያትሩን ታሪክ እዉን ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለዉ፡፡

የመብራት በለሙያ ድርሻ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ተዉኔቱን ስክሪፕቱን) በማንበብ የሚያስፈልገዉን መብራት መለየት፡፡
- ትያትሩ የሚቀርብበት ቦታ በመሄድ መጋረጃና ለመብራት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት፡፡
- ለመብራት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት፣
  ለምሳሌ፡- አስፈላጊዉ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም በመብራት ላይ እንዲጨመሩ ማድረግ፡፡

**መ. ግባዓተ-ድምፅ**

የድምፅ ባለሙያ ስክሪፕቱን በማንበብ ለታሪኩ የምስማማን ድምፅ በመለየት ያዘጋጃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በእስክሪፕቱ ውስጥ የንጋት /የጎህ መቅደድ/ ታሪክ ተጽፎ ከተገኘ ንጋትን የሚገልጹ ድምፆች እንደ የወፎች ጫጫታ፣ በከተማ አከባቢ የፀሎት ድምፅ እና የመሳሰሉትን ከሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ጋር ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፡፡

**ሠ. የመድረክ መልክ**

የመድረክ መልክበትያትር ፕሮዳክሽን ውስጥ የትረካዉን ቦታ በሚገልጽ ስሜት የሚገነባ ነው፡፡ የመድረክ መልክበትረካዉ (ስክሪፕቱ) ላይ መቼቱ በተደራጀ መልክ የሚገለጽበት ሁኔታ ነው፡፡ የመድረክ መልክከወንበር ጀምሮ ድራማዉ የተከናወነበትን ቦታ፣ የተገነባ ቤትን ጨምሮ በመድረክ ላይ የየምንጠቀምባቸውን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡

በአጠቃላይ የመድረክ መልክማለት አንድ ድራማ ተፈጥሮአዊ ሆኖበሚያምር መልክእዉናዊ መስሎ እንዲቀርብ የሚደረግበት ጥበብ ነው፡፡

**ረ. ተዋንያን**

ተዋንያንማለት በትያትር ዝግጅት ውስጥ የተሰጣቸዉን ገፀ-ባሕርይወክለዉ በአንድነት መድረክ ላይ ወጥተዉ የሚያሳዩ ሰዎች ናቸው፡፡ተዋንያን ወንድም ሴትም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ሰ. ትወና**

ትወና በትያትር፣ በፊልም፣ በራዲዮ ድራማ እና በሌሎችም ጭውውትውስጥ የአንድ ኩነት ታሪኪ በተዋንያን ከተለማመዱ በኋላ፣ ታሪኩን ከማስመሰል ወደ እውነተኛ ኩነት መስሎ ማቅረብ መቻል ነው፡፡

ትወና አርቆ የማሰብ ትንታኔ፣ ስሜትን መግለጽ፣ ትርጉም ያለዉ የአካል እንቅስቃሴ፣ ከፍ ያለ ድምፅ፣ በደንብ የሚሰማ ንግግር እና እስክሪፕቱን የመተርጎም ጥበብን ያካተተ ጥበብ ነው፡፡

እንዲሁም ትወና የተለያዩ ቃለቶችን፣ ንግግሮችን፣ ድንገቴ ፈጠራ፣ ጭዉዉቶችን፣ ማይምክ፣ የመድረክ ግጭቶችን እና የመሳሰሉትን ጥበባት ያካትታል፡፡ ስለዚህ ተዋንያን

ደጋግመው መለማማድ አለባቸዉ፡፡ በትወና ልምምድ ውስጥ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋና የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ. የሜይስኔሪ ዘዴ

የሚይስኔሪ ዘዴበእውነተኛ ትወና ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተዋንያን በዉስጣቸዉ የሚሰማዉን ስሜት እንዲጫወቱ ያበረታታል፡፡ በአዕምሮ ከሚብሰለሰል ይልቅ ልባቸዉ የሚናገራቸዉን ሆነው እንዲሰሩ የሚያሳይ ነው፡፡

### ለ. የእስታንስላቭስኪ ዘዴ

የእስታንስላቭስኪ ዘዴተዋንያን ያለፈ ትዝታቸዉን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡ ተዋንያን በህይወታቸዉ ያሳለፉትን፣ ማስታወሻቸዉን ወደ ኋላ ተመልሰው እንዲያሰላስሉ ይጠይቃል፡ ፡ ወይም ተዋንያን "ይህ ኩነት በእውነት እኔ ላይ ቢፈጸም እንዴት ሊተዉን እችላለሁ?" ብለዉ ራሳቸዉን እንዲጠይቁ የሚያደርግ ነው፡፡

የእስታንስላቭስኪ ዘዴ አራት አላባውያን አሉት፣

- ትኩረት
- ነፃ አካልና ሃሳብ
- የትዝታ ስሜት
- እውነተኛነት

### ሐ. ደጋፊዎች

ደጋፊዎች ማለት በቀጥታ መድረክ ላይ የማይታዩ ግን በሚዘጋጀዉ ትያትር ውስጥ በቴክኒክ ሥራ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚደግፉ ናቸው፡፡

### ቀ. መብራት

መብራት በትያትር ፕሮዳክሽን ውስጥ የታሪኩን መቼት እውን እና ሙሉ ለማድረግ የሚንጠቀምበት ሆኖ በመጠንና በአይነት የተለያዩ ናቸው፡፡

በትወና ልምምድ ውስጥ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡

- የሜይስኔሪ ዘዴ በእዉነተኛ ትወና ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተዋንያን በስስጣቸዉ የሚሰማዉን ስሜት እንዲጫወቱ ያበረታታል፡፡ በአእምሮ ከሚብሰለሰል ይልቅ ልባቸዉ የሚናገራቸዉን ሆነው እንዲሰሩ የሚያሳይ ነው፡፡
- የእስታንስላቭስኪ ዘዴ ተዋንያን ያለፈ ትዝታቸዉን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡ ተዋንያን በህይወታቸዉ ያሳለፉትን፣ ማስታወሻቸዉን ወደ ኋላ ተመልሰዉ እንዲያሰላስሉ ይጠይቃል፡፡ ወይም ተዋንያን "ይህ ኩነት በእዉነት እኔ ላይ ቢፈጸም እንዴት ሊተዉን እችላለሁ?" ብለዉ ራሳቸዉን እንዲጠይቁ የሚያደርግ ነው፡፡

የእስታንስላቭስኪ ዘዴ አራት ኤሌሜንቶች አሉት፡

- ትኩረት
- ነፃ አካልና ሃሳብ
- የትዝታ ስሜት
- እዉነተኛነት

### 1.3.2. የትያትር ጥበብ ፕሮዳክሽን ደረጃዎች

የትያትር ጥበብ ፕሮዳክሽን ደረጃዎች ማለት በአንድ ጥያትር ዝግጅት ውስጥ የሚታለፉ ደረጃዎች ማለት ነው፡፡ አነዚህም ደረጃዎች በሦስት ትላልቅ ቦታዎች ይከፈላሉ፡፡

እነሱም፡

- ከዝግጅት በፊት
- የዝግጅት ጊዜ
- ከዝግጅት በኋላ

### 1. ከዝግጅት በፊት ደረጃ

ይህ ደረጃ የመጀመሪያዉ የትያትር ዝግጅት (ፕሮዳክሽን) ቅድመሁኔታነው፡፡ ይህም፤አንድ ታሪክ (ተዉኔት) ተመርጦ ከሚዘጋጅበት ጊዜ አንስቶ የተዋንያን መረጣ፣ የቦታ መረጣ፣ የበጀት እና የቁሳቁስ መረጣ እንዲሁም የልምምድ ጊዜና ሁሉንም የቴክኒክ ዝግጅቶች ያጠቃልላል፡፡

2. የዝግጅት ጊዜ

ይህ ደረጃ ደግሞ አንድ ትያትር ልምምድ ከተጠናቀቀ በኋላ መድረክ ላይ ለእይታ ሲቀርብ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተዋንያን በመድረክ ላይ የሚያሳዩትን ተግባር፣ የተመልካቾች ስሜት፣ የመድረክ አያያዝ ሁኔታ፣ የልብስና ሜካፕ፣ የተዋናይ ስሜት፣ የመብራት እና ድምፅ አጠቃቀም ይጠቃልላል፡፡

3. ከዝግጅት በኋላ

ይህ ደረጃ አንድ ትያትር ልምምዱ ተጠናቅቆ ለመድረክ ክፍት ሲሆን፣ የማስታወቂያ እና ማከፋፈያ ጊዜን ያጠቃልላል፡፡ ይህም ትያትሩ ለህዝብ እንዲቀርብ ቦታ መምረጥ፣ ተመልካቾችን መምረጥ እና በቀጥታ ማሳየትን ያካትታል፡፡

### 1.3.3. የፊልም ጥበብ ዝግጅት አላባውያን

የፊልም ጥበብ ዝግጅት አላባዉያን የሚባሉት በአንድ የፊልም ዝግጅት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የሚታቀፉት ነገሮች ናቸው፡፡ እነሱም፡ ገጸ-ባህሪይ (የተወናይ ድርጊት)፣ መቼትና ቁሳቁስ፣ ካሜራ፣ መብራት፣ ቀለም፣ ድምፅ፣ ሙዚቃ እና የመሳሰሉ ናቸው፡፡

ገጸ-ባህሪይ በአንድ ፊልም ውስጥ አንድን ታሪክ ተዋናይ ተካፍሎ ስያከናዉን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም በፊልም ጥበብ ቴክኒክ ዝግጅት ውስጥ የተዋናይ ድርጊት ወደ ቀረፃ እንዴት እንደሚመጣ ከካሜራ አንግል ጋር በማቀናጀት የሚያሳይ ነው፡፡

በፊልም ጥበብ ዝግጅት ውስጥ አንድ ታሪክ መቼና የት እንደተፈጸመ፣ በዝግጅቱ ውስጥ ምን አይነት ቁሳቁስ በመጠቀም የታሪኩን እዉነታ ለመግለፅ እንደሚገባ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም ታሪኩ መቼና የት እንደተፈጸመ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማህበረሰብ ውስጥ ያለዉን እዉነታ ጋር አቀናጅቶ የሚያቀርብና ታሪኩ በተፈጸመበት ዘመን የነበሩትን ቁሳቁስ እና በዘመኑ የነበሩትን ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚገልጽ ነው፡፡

ካሜራ የአንድ ፊልም ታሪክ ተዋንያን ተለማምዶ ከተዘጋጀ በኋላ የሚቀረጽበት እና ቪዲዮዉን ወደ ፊለም በመቀየር የሚቀርብበት መሳሪያ ነው፡፡ ይህም በፊልሙ የታሪክ ግንባታ ላይ በሚገኝበት ሁኔታ ሪቀት፣ አንግልና የተለያዩ እንቅስቃሴ ያለዉና የቀረበዉን ታሪክ እዉነታን ለመግለጽ ከፍተኛ ሚና አለዉ፡፡

መብራት በፊልም ጥበብ ዝግጅት ውስጥ እይታን ለማሳመር፣ መቼትን እዉን ለማድረግ፣ እንዲሁም የተዋንያን ስሜት ሙሉ ለማድረግ የሚጠቅም ነው፡፡ ይህም በፊለሙ ታሪክ ላይ

በመሞረኮዝ አይነት እና አቅጣጫ፣ እንዲሁም በተለያዩ ጥንካሬ ወደ ፊልም ጥበብ የሚጨመር ነው፡፡ በፊልም ውስጥ ቀለም ተዋናዩ የለበትን ስሜት ለመግለጽ የገለግላል፡፡ ይህም ጸሃፊዉ በፊልሙ ውስጥ ታሪኩን አቀናጅቶ ባስቀመጠዉ መሰረት ይሆንል፡፡ የተለያየ ቀለም እንደምንጠቀም የተዋናይ ስሜትም በቀለሙ ውስጥ እዉናዊ ይሆናል፡፡

ድምፅ እና ሙዚቃ በፊልሙ የታሪክ ጽሁፍ ላይ በመመርኮዝ የተዋናይን ስሜት እዉን ለማድረግ፣ እዉናዊዉን መቼት ለመፍጠር፣ እንዲሁም የአንድን የፊልም ጥበብ መልዕክት ሙሉ ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ይህም ከፊልሙ ታሪክ ጋር የሚገናኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰዉ ሰራሽ ድምፆች በመጠቀም የተዋንያንን ስሜት በሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀም መግለጽ፣ የፊልሙን መልዕክት ሙሉ ማድረግ እና የተዋንያንን የትወና ብቃት ሙሉ ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡

### 1.3.4. የፊልም ፕሮዳክሽን ደረጃዎች፣

አንድ ፊልም ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻዉ በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ በማለፍ ይዘጋጃል፡፡ፊልም ከትያትር ይልቅ የተለያዩ ባለሙያዎችንና የሰዉ ጉልበትን ይጠይቃል፡፡ በፊልም ዝግጅት ሂደት ውስጥ ሶስት ትላልቅ ደረጃዎች አሉ፡፡ ክፍፍሉም እንደአፈጻጸም እና ከሚሰራዉ ሥራ አኳኋን ነው፡፡

እነሱም፡

- ቅድመ ፊልም ዝግጅት
- የዝግጅት ጊዜ እና
- ከዝግጅት በኋላ ይባላሉ፡፡

### ሀ. ቅድመ ፊልም ዝግጅት

በቅድመ ፊልም ዝግጅት ጊዜ የሚሰሩ ሥራዎች፣ አብሮ የሚሰሩትን ተዋንያን መለየት፣ ቁሳቁስና የልምምድ ጊዜን ማሳወቅ፣ የልምምድ የጊዜ ሰሌዳን ማዘጋጀት፣ የሚያስፈልጉትን በጀት ማዘጋጀት፣ ፊልሙን ከሚደግፉት ጋር ለመሥራት ዝግጅት ማድረግ፣ ተዋንያን ስክሪፕት ማንበብ፣ ተዋንያን ከአዘጋጁና አብሮ ከሚሰሩት ከመብራት ባለሙያ፣ ከድምፅ አሳማሪ ባለሙያ፣ የአልባሳት ባለሙያ፣ እና ሌሎችማ የቴክኒክ ሥራ ከሚሰሩት ጋር መተዋወቅ፡፡

በተጨማሪም በፊልሙ አሰራር ላይ አስፈላጊዉን ገለጻ መሰጣጠት፣ ታሪክና መከፋፈል፣ በተከፋፈሉት ላይ ሊያጋጥማቸዉ የሚችሉትን ችግሮች በመለየት እና ተዋንያን ፊልሙን ከሚያዘጋጀዉ አካል ጋር ዉል መፈራረም እና ወደ ሥራ መግባት፡፡

### ለ. የዝግጅት ጊዜ

የዝግጅት ጊዜ ፊልሙ የሚሰራበት ጊዜ ማለት ነው፡፡ የሚያስፈልጉ ነገሮች ተዘጋጅቶ የልምምድ ጊዜ የሚደረግበት እና ፊልሙ በየእይታዉ ተከፋፍሎ የሚቀረጽበት ጊዜ ነው፡፡ በፊልሙ ፕሮዳክሽን ጊዜ ሁሉም ተዋናይና ደጋፊዎች የድርሻቸዉን የሚወጡበት ጊዜ ነው፡፡

ባጠቃላይ በፕሮዳክሽን ጊዜ የሚከናወኑ ሥራዎች፡-

- ፊልም መቅረጽ
- የተቀረጸዉን ፊልም ግድፈቱን በመለየት አንደገና እንዲቀዳ ማድረግ
- በተቀረጸዉን ፊልም ውስጥ አላስፈላጊ ነገሮችነ ማዉጣት

### ሐ. ከዝግጅት በኋላ

ከዝግጅት በኋላ የሚሰራዉ ሥራ የተሰራዉን ፊልም መሰብሰብ፣ አርታኢ ማድረግ፣ የማያስፈልጉትን ነገሮች ማስቀረት፣ በትክክል መሰራቱን በማረጋገጥ ማዘጋጀትን የጠቃልላል፡፡

## የትምህርት መርጃ መሣሪዎች

ይህን ይዘት ለማስተማር የሚያስገልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡

- የልምምድ ክፍል አደራሽ (የትያትር አደራሽ)
- ለትያትር የምያስፈልጉ ቁሳቁሶች
- የትያትር አልባሳት

## የመምህሩ ድርሻ

- የዚህን ትምህርት ርዕስ ከማስተማር በፊት ተማሪዎች ያለቸዉን ልምድና ግንዛቤ ለእርስ በርሳቸዉ እንዲያከፍሉ በማድረግ ትምህርቱን ማጠናከር ይቻላል፡፡

- የተሰጡትን ተግባራትና ጥያቄዎችን እንደ የቤት ስራ፣ የግል ሥራ፣ የጥንድ ሥራ የቡድን ስራና እና በፕሮጀክት መልክ እዲሰሩ ያድርጉ፡፡.
- ተምረዉ ያለፉትን የትምህርት ርዕስ እንዲያስተዉሱ ያግዙዋቸውቸዉ፡፡
- መነናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- ተማሪዎች መነናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡

## የተግባር መልስ

በዚህ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች ተምረዉ ከለፉት የትምህርት ርዕስ ጥያቄ በመጠየቅ ግንዘቤያቸዉን መለየትና መመዘን ይቻላል፡፡ ባለፈው የትምህርት ርዕስ ውስጥ ሰለ ትያትር ጥበብ ምንነት፣ በተዉኔት ፕሮደክሽን ውስጥ የልብስ አጠቃቀም እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ትያትር እንዴት እንደምቀርብ እንዲሁም ስነ-ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ስለ ትወና ምንነት፣ ዝግጅት፣የተዉኔት አፃፀፍ ስልት ለተማሪዎች አስረዱ፡፡ በተጨማሪም የራሳችንን ዘዴ ተጠቅመን እንዴት በትያትርና በፊልም ጥበብ ውስጥ ሀሳብ እንደምንግልፅ፣እንዲሁም የትያትርና ፍልም ጥበብ ተጠቅመን የሀገር በቀል-እዉቀቶችን እንዴት እንምናደምቅ ፣የፍልምና ትያትር ልዩነት መለየት፣ ለትያትርና ፊልም ሀሳብ ከየት እንደምናመነጭ፣ እና የትያትር ጥበብና የፊልም ጥበብ የማህበረሰቡ ሀገር በቀል እዉቀቶችን እንዴት ማምንጨት እንደሚችሉ በጥያቄና መልስ መልክ ማቅረብ ይቻላል፡፡

### ተከታተይ የምዘናዎች

- የግል ማብራሪያ
- የቡድን ሥራ ጽብሪቃ
- ቃለ-መጠየቅ

- የቤት ሥራ
- ንዑስ ፈተና
- መጠቃለያ ፈተና
- የተማሪዎች ኑበሬ  ወረቀት
- ትወና ትርኢት

**የምዕራፍ 1 መልመጃ መልስ**

**ሀ. የእዉነት ወይም ሐሰት ጥያቄ  መልስ**

1. እዉነት  2. እዉነት  3. ሐሰት  4. እዉነት

5. ሐሰት  6. ሐሰት  7. እዉነት  8.እዉነት

9. ሐሰት  10. እዉነት  11. ሐሰት  12. ሐሰት

13. ሐሰት  14. ሐሰት  15. እዉነት  16. ሐሰት

17. እዉነት

**ለ. የምርጫ ጥያቄ መልስ**

1. ለ  2. መ  3. መ  4.መ  5.ለ

6. ሐ  7.መ  8.ሐ  9. ሀ  10. ሐ  11. ለ  12. ለ

13. ሀ  14. ለ  15. መ  16. ለ  17. ሐ

**ሐ. በፅሁፍ የምመለስ ጥያቄ መልስ**

1. ከበሮ ፣ከበላ ፣መርከሻ ወዘተ.......
2. በሶስት ይከፈላሉ እናሱም-
   - የምት(በመምታት ድምፅ የምያወጣ)
   - የንፈስ( በመንፈት ድምፅ የምያወጣ)
   - የክር ( በመምቻ ወይም በማሸት ድምፅ የምያወጣ)
3. የባቲ ቅኝት

# ምዕራፍ 2  የፈጠራ ችሎታ

***ለዚህ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ.........22***

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤት**:

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት ቦኋላ ተማሪዎች፤

- የተለያዩ የጊዜ ቆይታ ያላቸዉን ኖታዎች ያነባሉ፡፡
- የአንቺሆዬ ለኔ እና የአምባሰልን ቅኝቶችን ይለያሉ፡፡
- በአንቺሆዬ ለኔ እና በአምባሰል ቅኝት በመጠቀም  ቀለል ያለ ሙዚቃን ይጫወታሉ፡፡
- ባህላዊ  ውዝዋዜን በተግባር ያሳያሉ፡፡
- የግራፊክስ ትምህርት ትርጉም ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የፔፐር ማሼ ስራ ሂደት ይለያሉ፡፡
- የሸክላ ስራ ምንነት ይገልፃሉ፡

**መግቢያ**

በምዕራፍ አንድ ውስጥ ስለ ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሳሪያ ዓይነቶች፣ጠቀሜታ እና ድርሻ፣ስለ ቅኝትና ዉዝዋዜ ተምራዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሶልፌጅዮ ምንነት እና አጠቃቀም እንዲሁም የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝቶችን (አንቺሆዬ ለኔ እና አምባሰልን) እንዴት መጨወት እንደሚቻል ከባህላዊ ዉዝዋዜ ጋር አያይዛችዉ ይማራሉ፡፡ በምዕራፍ አንድ ውስጥ የስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም ፕሮዳክሽን ተምራዋል፡፡ እንዲሁም በተዉኔት ዘዴዎች ውስጥ  የሚፈጸሙትን  ስራዎች ተረድተዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ለትያትር እና ፊልም ፕሮዳክሽን ምን እንደሚያስፈልግ እና ሂደቱን የምትማሩ ይሆናል፡፡በተጨማሪም፣የትያትር እና ፊልም አጭር ታሪክ ፈጠራ  እና አንድ የትያትር  ጥበብ ለመመዘን እንድትችሉአስፈላጊውን ክህሎት የሚጎናጸፉ ይሆናል፡፡
የሸክላ ስራ ሙያ የቅርጻቅርጽ ሙያ የሚሰራበት ስራ ነው፡፡  የሸክላ አፈር ዓይነቶች፣ለሸክላ ስራ ሙያ የሚውሉ ከቦታ ቦታ ልዩነት አሏቸው፡፡የሸክላ አፈር፣

የፔፐር ማሼ እና የህትመት ስራ ውጤቶች ለተለያዩ ነገሮች አገልግሎት ለማስዋቢያ ስራ ይዉሉ ነበር፡፡

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት አብይ ይዘቶች፡

2.1. ሶልፌጅዮ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት (አምባሰልና አንቺ ሆዬ ለኔ)

2.2. ባህላዊ ውዝዋዜ

2.3. ትያትርና ፊልም ጥበባት ስራ ፕሮዳክሽን (ፊጠራ፣አጭር ታርክን መጻፍ እና መተቸት)

2.4. የግራፊክስ ትምህርት እና ቅርጻቅርጽ (የሸክላ አፈር፣ፔፐር ማሼ)

## 2.1. ሶልፌጅዮን በኢትዮጲያ ሙዚቃ ቅኝት (አንቺ ሆዬ ለኔ እና አምባሰል)

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ............ 4**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች**

- የሶልፌጅዮ ትርጉም እና ጥቅምን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የአንቺ ሆዬለኔ እና የአምባሰል ቅኝቶችን ለይተው ይገልጻሉ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ሙዚቃን ለመጫወት ዋና ወይም የጀርባ አጥንት  የምንለዉ ምንድን ነው?ለምን ምክኒያት ዋና ወይም የጀርባ አጥንት ተባለ?   በምለዉ ጥያቄ ላይ በቡድን ከተወያዩ በኋለ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፣ በመቀጠል ከዚህ በታች ያለዉን የሶልፌጆ ይዘት ለተማሪዎች ግለጹ፡

## ሶልፌጅዮ

ሶልፌጅዮ ማለት ከሙዚቃ ሳይንስ አንዱ ሆኖ ሙዚቃን ማዳመጥ፣መፃፍና ማንበብ ውስጥ ባለዉ ችሎታ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የተለያዩ የሙዚቃ ምቶች፣የኖታዎችን ድምጽ በጆሮ ሰምቶ መለየትና የተጻፌዉን ዜማ ማንበብ እና መማር የሚቻለው በሶልፌጅዮ ነው፡

ሶልፌጅዮ እንደ ሌሎች የትምህርት መስኮች በሂደት ወይም በልምምድ መማር ይቻላል፡፡ በሙዚቃ ሳይንስና የሙዚቃ ችሎታን በማሳደግ ሂደት ውስጥ ያለዉ አስተዋጽዎ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደሚታወቀዉ በሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ ዘፌኖችና ዜማዎች በተቀናጀ እና ዉበት ባለዉ መልክ የሰዉን ስሜት እንዲማርክለማድረግና እና በሰው ውስጥ ተነሳሽነትን የሚፈጠረውበሶልፌጅዮ አማካኝነትነው፡፡ ስለዚህ ሶልፌጅዮ ለተለያዩ ምቶችና ዜማዎችን ከዋናዉ እስከ ላይ ድረስ ለመማር የሚያስችል ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ውይይት እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት ማስተማር
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- በፕሮጀክት ዘዴ
- ልምምድ

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

**የዚህ ርእስ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

- የባህል የምት ሙዝቃ መሣሪያዎች

## የመምህር ድርሻ

- ተማሪዎች የለፈዉን ርዕስ ስለ ቅኝት ዓይነቶችና ስለ ውዝዋዜ እንድገልጹ በማድረግ ርዕሱን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የሶልፌጅ፣ የምትና ድምጽ ግንኙነት በጥንድና በቡድን እንዲዋያዩ በማድረግ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡

- በንዑስ ርዕስ ሥር የተሰጠው ተግባር የተማሪዎችን እዉቀትና ችሎታን ለማወቅ ስለሚረዳ ፣ወደ ገለጻ ከማግበታቸዉ በፊት በቡድን ተወያይተዉ እንዲገልጹ አድርጉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡


የተግበር 1 መልስ

ተማሪዎች የምት ልምምድ ሲማሩ የተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን ምቶች ‹ታ ወይም ላ ማለት ካሳዩዋቸዉ በኋለ ተማሪዎች እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡

**ልምምድ 1**

1.ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመርኮዝ "ታ" ወይም "ላ" በማለት ተለማማዱ፡፡

ሀ.



ልምምድ 2.

2. ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመርኮዝ "ታ" ወይም "ላ" በማለት ተለማማዱ፡፡




ልምምድ 3

3. ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመርኮዝ "ታ" ወይም "ላ" በማለት ተለማማዱ፡፡




ልምምድ 4

ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመርኮዝ "ታ" ወይም "ላ" በማለት ተለማማዱ፡፡



ልምምድ 5

5.ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመርኮዝ "ታ" ወይም "ላ" በማለት ተለማማዱ፡፡



2.1.2. **የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት**

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ............2**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች**

- የአንቺ ሆዬ ለኔ እና የአምባሰልን ቅኝቶችን ይለያሉ፡፡
- በአንቺሆዬ ለኔ እና በአምባሰል ቅኝት በመጠቀም ቀለል ያለ ሙዚቃን ይጫወታሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- የቡድን ውይይት
- የጥንድ ውይይት እና የሙሉ ክፍል ውይይት

- በማሳየት ማስተማር
- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- በፕሮጀክት ዘዴ
- ልምምድ

### የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

### የዚህ ርዕስ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-

- የባህል ሙዝቃ መሣሪያዎች

### የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎች የሶልፌጅዮ፣ የምትና ድምጽ ግንኙነት እንድ ገልጹ በማድረግ ርዕሱን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በአንቺሆዬ ለኔ እና በአምባሰልን ቅኝቶችን ለይ በጥንድና በቡድን እንዲዋያዩ በማድረግ የዉይይታቸዉን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡
- በንሁስ ርዕስ ሥር የተሰጠ ተግባር የተማሪዎችን እዉቀትና ችሎታን ለማወቅ ስለምረዳ ፣ወደ ገለጻ ከማግበታቸዉ በቡድን ተወያይተዉ እንዲገልጹ አድርጉ፡

### ተከታታይ ምዘናና ክትትል

- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መነናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፣ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መነናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡


- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

## የተግባር 2 መልስ


1. $B^{b}$አምባሰል $B^{b}C^{b}$ $E^{b}$ F $G^{b}$ $B^{b}$



G, አምባሰል G$A^{b}$ C D $E^{b}$ G




3, $E^{b}$, አምባሰል $E^{b}$ $F^{b}$ A $B^{b}$ $C^{b}$ $E^{b}$




## የተግባር 3. መልስ


1. E, አንቺሆዬ ለኔ  E $F^b$ A  $B^b$ C E



2. $B^b$, አንቺሆዬ ለኔ  $B^b$ $C^b$ $E^b$ $F^b$ G $B^b$



3. D. አንቺሆዬ ለኔ D $E^b$ G $A^b$ B D



## 2.2 ባህላዊ ውዝዋዜ

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ……………..4**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች**

- የባህል ውዝዋዜዎችን የሚተገበሩበትን ጊዜ ይለያሉ፡፡
- በህብረተሰቡ ውስጥ የባህል ዉዝዋዜዎችን ያደንቃሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ያሉ የባህል ዉዝዋዜዎችን ይለማመዳሉ፡፡

ባህላዊ ውዝዋዜ  እንደ ሌሎች ባህላዊ እሴቶችየአንድን ማህበረሰብ ማንነት ማሳያ ከሆኑ እሴቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የምግብ፣የአልባሳት፣የመረዳዳት፣የእምነትና የመሳሰሉት ባህሎች አንዱን ብሔር  ከሌላዉ እንደሚለዩ ሁሉ የባህል ውዝዋዜ ሁኔታም ከቦታ ቦታ ልዩነት አለዉ፡፡  በውዝዋዜ የሚሳተፉ ሰዎች እድሜ፣እንቅስቃሴ፣ ጊዜ እና ስነ ስርዓት ከቦታ ቦታ ተመሳሳይነትና ልዩነት አለዉ፡፡

አንድ ማህበረሰብ ባህሉን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ በተለያየ መልክ በማስተላለፍ፤ እርስ በረሱን እያዝናና እና እያበረታታ ይኖራል፡፡ከነዚህ አይነት ባህላዊ እሴቶች ውስጥ የዘፈንና ባህላዊ ውዝዋዜዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ውዝዋዜና ዘፈን በአብዛኛው አብረዉ የሚሄዱና የማይለያዩ ሆነው በየጊዜው ልሻሻሉና ልዘመኑ ይችላሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- የቡድን ስራዎች
- ጥንድ ስራዎች
- የሙሉ ክፍል ውይይት
- የፕሮጀክት ስራዎች

**የትምህርት መርጃ መሣሪያ**

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያገለግሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ።

- የባህል ልብስ

• የሙዚቃ መሳሪያዎች (ፒያኖ፣ ከበሮ፣... ወዘተ)

**የመምህሩ ድርሻ**

- ተማሪዎች በለፉ ርዕስ ውስጥ በአንቺሆዬ እና በአምባሰል ቅኝት የተሰሩትን ቀለል የሉትን ዜማዎች እንዲገልጹ በመጠየቅ ርዕሱን መጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በባህላዊ ዉዝዋዜ ለይ በጥንድና በቡድን እንዲዋያዩ በመድረግ ዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በንዑስ ርዕስ ሥር የተሰጡ የተግባር ጥያቄዎች የተማሪዎችን እዉቀትና ችሎታ ለማወቅ ስለምረዱ ወደ ገለጻ ከመሄድ በቡድን ተወያይተዉ እንዲገልጹ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘናና ክትትል**

- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መኀናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መኀናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**ማሳሰቢያ፡** ተግባር 4 ለተማሪዎች የተሰጠዉ በአካባቢያቸው ካሉ ወይም በሌሎች አካባቢ ከሚገኙ ባህላዊ ውዝዋዜዎች አንዱን በመምረጥ በቡድን በመለማመድ በተግባር እንዲያሳዩ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ተግበራዊ ያድርጉ።

## 2.3 የትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን (ፈጠራ፣አጭር ታሪክ መፃፍና መመዘን)

የተሰጠው ክፍለ ግዜ……………..6

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**:

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፥**

- የትያትርና ፊልም ጥበብ ፕሮደክሽን ሂደት ይገልፃሉ፡፡
- አጭር የፈጠራታሪክ ለትያትርና ፊልም ጥበብ ይፅፋሉ፡፡
- የስነ-ጥበብ መተችያ መንገዶችን ይለያሉ፡፡

**የምዕራፉ  ዋና ዋና ነጥቦች**:

- ፈጠራ
- ሂስ
- የጥበብ ሂስ ህደቶች

**የይዘት መብራሪያ /መግለጫ**

ፈጠራ፣ የጥበብ ሥራ፤ትያትር፣ፊልም ጥበብ እና፣ሙዚቃ ብቻ የሚወስን  ሳይሆን፤ በኢኮኖሚ፣በምርት፣በቴክኖሎጂ፣በአስተዳደር፣እና የመሳሰሉት ውስጥም ይገኛል፡፡

ተጨባጭ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎች፤የስነ ጥበባት ሥራዎች፤መፅሐፍት፣ሙዚቃ፣የክነ-ህንፃ ስራዎች፣ማሽኖች ሲሆኑ፤ተጨባጭ ያልሆኑ የፈጠራ ስራዎች ደግሞ ሃሳብ፣አገልግሎት፣ዘዴ፣ ተረፈ ምርት እና ማከፋፈያን ያጠቃልላሉ፡፡

ስለዚህ ከላይ የተገለፁትን የፈጠራ ስራዎችን በማጠናከር፤ ለታለመ ግብ ማድረስ አስፈላጊ ነው፡፡ይህም መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች የጥበብ ባለሙያዎች ተነሳሽነት እና ለጥበብ ያላቸዉ ክብር ናቸው፡፡ በተጨማሪም በተለምዶ ያሉትን ነገሮችን ማዘመን እና ተጨባጭነ ጥበባዊበሆነ መንገድ ነገሮችን መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ጥበባዊ ስራዎች የሚያምሩ የክነ ህንፃ ዲዛይኖች፣የልብ ወለድ መፅሐፍቶች፤ማሽኖች አስተዳደራዊ ስርዓት እና በሃገር ሰላም ጥበቃ ዘርፍ ግንዛቤዎችን ለማሳደግ ሊሆን ይችላል፡፡

የዘመናዊ ፈጠራ ታሪክ የተጀመረው በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን (1950 እ.አ.አ) ነበር፡፡ ምሁራን የፈጠራ ስራ በግለሰብ እድገት እና አኗኗር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለዉ ያምናሉ፡፡

ስለዚህ የፈጠራ ስራ በተማሪዎች ዘንድ ወደ ተጨባጭ የፈጠራ ስራ ክንውኖች በመለወጥ የፈጠራ ስራ ምዘና እና እድገት ክፍል ውስጥ የዉይይት ነጥብ መሆን አለበት፡፡ ይህም የፈጠራ ስራ አስፈላጊነትን በማነቃቃት፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሰዉ ልጅ እድገት እና ስልጣኔ አካሄድን ማስተዋወቅ ይቻላል፡፡ እነዚህም፡

1ኛ. አካሄድ/ የፈጠራ ሃሰብ

2ኛ. የሰዉዬዉ የፈጠራ ችሎታ

3ኛ. ከፈጠራዉ የተገኘውጤት

ስለዚህ ፈጠራ እንደምክንያትና ውጤት የሚወሰደዉ፤በሰዎች ፈጠራ ችሎታ እና አካሄዳቸዉ ላይ በመመስረት ነው፡፡ በዚህ በሂደት የሚመጣዉ ችሎታ ደግሞ ውጤት ነው፡

ሂስ ማለት በጥናት ላይ የተመሰረተ ዋና አጀንዳ በጥልቀት የሚካሄድ ፍቺ የሚሰጥ፣ የሚገመግም፣ማብራሪያ የሚሰጥ ፣ውሳኔ፣የሙስና ሀሳብ እንዲንጣራ የሚያግዘን በስልት የተሟላ የጥበብ ዘርፍ ሆኖ ስለ መቼት ትርጉም ሰፊና መልካም እድል ለህያሲያን ይሰጣል፡፡የስነ-ፅሑፍ ሂስ ስራ የአንድ ሰው የስነ-ፅሁፍ ምርምር ስሆን፤የመልካም አመለካከትና ከፉኛ አመለካከት ይዘት ያለው ጥበብ ነው፡፡

ሂስ ማላት የጥበብ ስራ የምንገልፅበትና የሚገመገምበት የስልት ዓይነት ነው፡፡በሌላ በኩል ሂስ ሳይንሳዊ የሆነ ምርምር በስነ-ፅሁፍና ስነ-ጥበብ ላይ የምከናወንበት ስልት ነው፡፡

ሂስ የስነ-ጥበብ ስራዎች ላይ የውይይት አጀንዳን የምቀርፅ እንዲሁም የስራው መልካምነትላይ ዉሳኔ መስጠት እና የስራው ደከማ ጎን የምገልፅበት መንገድ ነው፡፡

***የመርጃ መሣሪዎች***

- የመላማመጃ ክፍል (ትያትር አደራሽ)
- እርሳስ
- አልባሳት
- ወረቀት

**የመምህር ድርሻ**

- በትምህርቱ ተማሪዎች በፈጠራ ምንነት ላይ ሃሳበቸዉን እንዲሰጡ በማድረግ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡፡
- የፈጠራ ስራ በትያትር እና ፊልም ጥበብ ላይ ብቻ የማይገደብ መሆኑን አስረዱዋቸው፡፡
- ተማሪዎች በትያትርና ፊልም ጥበብ ላይ አጭር ታሪክ ፈጠራ እንዲፅፉ አድርጉ፡፡

- የዚህ ትምህርት ርዕስ ተግበራትን ተማሪዎች እንዲሰሩ ከትትል ያድርጉ፡፡.
- ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የተግባር 5 መልስ**

ፈጠራ ማለት የነበሩ ነገሮችን በአድስ መንገድ መየት፣የግንዛቤ ልምዳችን ማሳደግ የጥበባዊ ሥራዎችን ለምሳሌ የሕንፃዎች አሰራር፣አዳድስ ዲዛይኖችና ዉበታዊ ዲዛይኖች እና የተለያዩ እስከምፈጥር የምሄድ ማለት ነው፡፡ፈጠራ በስነ-ጥበብ ብቻ ውስጥ ሳይሆን በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ውስጥም ይገኛል፡፡ለምሳሌ፤በኢኮኖሚ፣ በቴክኖጂ፣መኑፋክቸሪንግ እና በአስተደደር ውስጥም ስራ ላይ የምዉል ጥበብ ነው

የመጻፍ ቅደም ተከተል በተመለከተ በሰባተኛ ክፍለ ውስጥ የተማሩትን እንዲያስተወሱ በማድረግ ፤ተማሪዎችን ከሳተፍክ በኃላ መልስ መልስላቸዉ፡፡ እነዚህም የመፀሐፍ ቅደመ ተከተል የሚከተሉ ነቸዉ፡፡

- የቅደመ-መፀሐፍ
- መስመር ማስያዝ
- በድጋሚ-መጻፍ
- መገምገም
- ማሳተም

**የምዘና ዘዴዎች**

- የግል መብራሪያ
- የቡድን ሥራ ጽብሪቃ
- ቃለ-መጠየቅ
- የቤት ሥራ
- ንዑስ ፈተና
- መጠቃለያ ፈተና
- የተማሪዎች ኑበሬ  ወረቀት

## 2.4. የህትመት ስራ እና ቅርፃ ቅርፅ (ሸክላአፈር፣ፐፔር ማሼ/ ወረቀት የማቡካት ስራ)፡፡

***ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ---------6***

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

**በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፣**

- የሸክላ ስራ እና ፔፐር ማሼን ይገልፃሉ፡፡
- የፔፐር ማሼ አሰራር ይዘረዝራሉ፡፡
- የሸክላ ስራ  ምንነት ይስረዳሉ፡፡
- የህትመት ስራ ምንነት ይነግራሉ፡፡
- የህትመት ስራ አይነት በመለየት ይዘረዝራሉ፡፡

***የመማር ማስተማር ዘዴ***

- ማሳያ
- ልምምድ
- የቡድን፣የጥንድ እና ሙሉ ክፍል  ወይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- ፕሮጀክት

***የትምህርት መርጃ መሳሪያ***

ለዚህ የትምህርት ርዕስ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-

- ጋዜጣ፣የተለያዩ መፅሔቶች፣ሙጫ/ኮላ፣እርሳስ፣ክራዮን እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች
- የሚለማመዱበት ክፍል/ ስቱዲዮ
- ወረቀት፣እርሳስ፣ከሰል፣ክራዮን እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች፡፡
- ቻርት
- ፖስተር እና ሞዴል ናቸው፡፡

***የመምህር ድርሻ***

- ተማሪዎች ስለ ፔፐር ማሼ ስራ፣የሸክላ ስራ እና ህትመት ትርጉም እና ምንነት፣ በፊት ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲገልፁ በመጠየቅ፣ ይህን ምዕራፍ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ስለ ፔፐር ማሼ ስራ፣የሸክላ ስራ እና ህትመት ትርጉም እና ምንነት በግል ከሰሩ በኋላ፣በቡድን እንዲወያዩ አድርጉ፡፡ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት መረዳት ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዳ፣ ወደ ማብራሪያ ሳትገባ/ቢ በፊት በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ከአደረጋችሁ፣ ተማሪዎቻችሁ እንዲነቃቁ ይረዳል፡፡
- ተግባራት እና ከመጀመሪያ ጥያቄዎች የተወሰኑትን፣ የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት የስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፣ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**ተግባር.6**

ተማሪዎቸች በአከባቢያቸዉ ሰዎች ስንደዶ/ሰርዶ ቀለም ውስጥ ሲነከር አይተዉ እንደሆነ ጠይቋቸዉ፡፡

አይተዉ የሚያዉቁ ከሆነ፣ እንዴት እንደሚነከር ከተወያዩበት በኋላ፣ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታታት ማጠቃላይ ሃሳብ ስጡ፡፡

**ተግባር. 7**

ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የወተት መያዣ ቅል ላይ ዲዛይን ሲሰራ አይተዉ የሚያዉቁ እንደሆነ ጠይቋቸዉ፡፡ አይተዉ የሚያዉቁ ከሆነ፣ እንዴት እንደሚነከር ከተወያዩበት በኋላ፣ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታታት ማጠቃላይ ሃሳብ ስጡ

**ልምምድ 6**

የህትመት ሂደት ወረቀት በመቆራረጥ እንደሚታተም፣ ከታች የተገለፀዉን ሂደት መሰረት በማድረግ፣ አስመስለዉ በመስራት እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ ተማሪዎች ይህንን ልምምድ ከመስራታቸዉ በፊት እንዴት እንደሚሰራ እና የስራዉን ቅደም ተከተል በደንብ አስረዱዋቸዉ፡፡

**ለዚህ ስራ የሚያስፈልግ ነገሮች**

- ዲዛይን የሚሰራበት ወረቀት
- የሚለጠፍበት ወፍራም ወረቀት
- እርሳስ
- ላጲስ
- መቅረጫ

- ወረቀት የሚንቆርጥበት ነገር/ከተር
- ሙጫ/ኮላ
- ጥቁር ቀለም
- ብሩሽ

## 1. ወረቀት የመቆራረጥ ስራ ሂደት

- በወረቀት ላይ ንድፍ ወይም ስዕል መሳል፡፡
- የተሳለውን ስዕል በጥንቃቄብርሃን እና ጥላ መስራት፡፡
- ሥዕሉን ለመለጠፍ የተዘጋጀውን ወፍራም ወረቀት ጥቁር ቀለም በመቀባት ማድረቅ ወይም በተዘጋጀው ዲዛይን ላይ ጥላ ያለበት ቦታ ቀለም በመቀባት ቆርጠውበማውጣት መለጠፍ፡፡
- የብርሃን እና ጥላ ቦታ በመለየት ብርሃን ያለበት ቦታ ቆርጠውማውጣት፡፡
- ከቆረጥን በኋላ ወረቀት ስስ ስለሆነ እንዳይጨማደድ በጥንቃቄ ኮላ/ማጣበቂያ መቀባት
- የተቀባው ማጣበቂያ ሳይደርቅ ቶሎ ብለን መለጠፍ ነው፡፡

ለክፍል ከአቀረቡ በኋላ በእርስበርሳቸዉ ስራ ላይ ጠንካራ ጎን እና ደካማ ጎን በመለየት፤ ስራዎቻቸዉን እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታታት ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸው ለወደፊት ስራቸዉን ለማሻሻል እንደሚረዳቸው በመስረዳት የማጠቃለያ ሃሳብ ይስጡዋቸው፡፡



ሥዕል 2.1 ወረቀት በመቆራረጥ የተሰራ የህትመት ስራ

## ልምምድ 6

ከዚህ በታች የተገለፀዉን የእስክራች ዘዴዎች በመከተል ስእሉን ከሳሉ በኋላ፣ በክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ መምህርት ተማሪዎች እሄንን ልምምድ ከመስራታቸዉ በፊት የአሰራር ሂደት እን ቅደም ተከተሉን በደንብ አስረዱዋቸዉ፡፡

### ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮች:

- ወፍራም እና ጠንካራ ወረቀት፡፡
- ሳሙና
- ዉኃ
- ሻማ
- የቀለም ብሩሽ
- ጥቁር ቀለም
- ስለት ያለዉ ነገር መርፌ እና የመሳሰሉት መጠቀም እንችላለን፡፡

### 1. የስክራች ስራ ሂደት


- የተዘጋጀው ወፍራም እና ጠንካራ ወረቀት ዝርግ በሆነ ነገር ላይ በማስቀመጥ እንዳይጎብጥ ማድረግ፡፡
- የተዘረጋ ወፍራም ወረቀት ላይ ሻማ በማሸት መቀባት፡፡
- የተቀባ ሻማ ላይ በብሩሽ ፈሳሽ ሳሙና መቀባት፡፡
- እስክደርቅ በትዕግስት መጠበቅ፡፡
- በደንብ ከደረቀ በኋላ ጥቁር ቀለም በብሩሽ መቀባት፡፡
- የተቀባ ቀለምበደንብ ከደረቀ በኋላ፣ በመርፌ ቀስ ብለን የፈለግነውን ንድፍ መንደፍ፡፡
- የብርሃን እና ጥላ አቅጣጫ በመለየት፣ ብርሃን መስለዉ የሚታየዉን አቅጣጫ በደንብ መፋቅ፡፡

- ጥላ ያለበት አቅጣጫ አስፈላጊ ከሆነ በስተ ጀርባዉን በማላቀቅ ወይም በቶሪ መስመር መስራት ነው፡፡

- ለክፍል ከአቀረቡ በኋላ በእርስበርሳቸዉ ስራ ላይ ጠንካራ ጎን እና ደካማ ጎን በመለየት፤ ስራዎቻቸዉን እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡  በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታታት ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸው ለወደፊት ስራቸዉን ለማሻሻል እንደሚረዳቸው በመስረዳት የማጠቃለያ ሃሳብ ይስጡዋቸው፡፡

ሀ.





ሥዕል 2.2 በስክራች የተሰራ ስራን የምያሰይ ሥዕል

ሀ. ለፔፐር ማሼ ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

**ተግባር 9**

ተማሪዎች ወረቀት በማቡካት ሞዴል የሚሰራበት ሂደት በመከተል፤ ጎድጓዳ ሳሃን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የዚህ ስራ ዉጣዉረድ፣ በስራ ውስጥ የነበሩ ችግሮች እና የተማሩበትን ነገር ለክፍል ተማሪዎች እንዲገልፁ አድርጉ፡፡ በመቀጠል ይህንን ልምምድ ከመስራታቸዉ በፊት ሂደቱን እና ቅደምተከተሉን በደንብ እነዲረዱ ያድርጉ፡፡.

ለፔፐር ማሼ ስራ ከሚያስፈላጉ መሳሪያዎች የተለያዩ ነገሮችን መስራት እንደሚቻል ከጥበብ ታሪክ መረዳት እንችላለን፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሳሪያዎች ማንኛውም የወረቀት ቅርጻ ቅርፅ ስራ ለመስራት ያገለግላሉ፡፡ እነዚህም መሳሪያዎች በአከባቢያችን የሚናገኛቸው ወይም በፋብሪካ የሚሰሩ ሊሆኑ ያችላሉ፡፡

እነርሱም፡-

- የተለያዩ ወረቀቶች
- የተለያዩ ቀለማት
- የብርጭቆ ወረቀት
- የተለያዩ ሽቦዎች
- የሚለጠፍበት ነገር (ሰሌዳ፣ኮምፖርሳቶ፣ብረት እና የመሳሰሉት)
- የተለያዩ መጠን ያላቸው ብሩሾች
- ሳሙና፣ ቫዝሊን እና ዘይት
- ጨው
- ጎድጎድ ያሉ እቃዎች ( ጎድጋዳ ሳህን፣ባልዲ እና የመሳሰሉት)
- ፒንሳ
- ቫርኒሽ
- መሮ
- ለማጣበቂያነት የሚያገለግሉ፤ ኮላ፣ ኡሁ፣ ሙጫ፣ ቅንጭብ፣ጥድ እና የመሳሰሉት መውሰድ እንችላለን፡፡ ከዱቄት ደግሞ ስንዴ፣ጤፍ፣ገብስ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- ውኃ
- እስኮች
- ማንኪያ
- የተለያዩ ፎጣዎች
- ቅርጽ ማውጫ ነገር ምላጭ፣ መቀስ፣ካተር እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የፔፐር ማሼ ቅርፃ ቅርፅ ሰራ የሚያገለግሉት መሳሪያዎች ያላቸው ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **ወረቀት**:ለዚህ ስራ ማኛውም ወረቀት ብያገለግልም፤ በቀላሉ ወይም በአጭር ጊዜ የሚበሰብስ ቢሆን ይመረጣል፡፡
- **ወረቀት እንዲያያዝ የሚያደርጉ ነገሮች**፡የማያያዝ ባህሪይ ያላቸው ነገሮች እንደ ኮላ፣ ከእህል ዱቄት የተዘጋጀ ሊጥ፣ ተልባ እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአከባቢያችን የሚገኙ ነገሮችዱቄት እና የተቦካ ወረቀት በደንብ የሚደባለቅ/የመሳሳብ ባህሪይ ያላቸው ከእነርሱም የስንዴ ዱቄት እና አጃ ሲሆን፤ ለመስራት የማይመቹ ደግሞ የማሽላ እና ቦቆሎ ዱቄት ለስለስ ስለሚል መጠቀም አስፈላጊ አይደለም፡፡
- **ነጌቲቭ አካል**:ነጌቲቭ አካልበፔፐር ማሼ ስራ ለሚሰራ ነገር ፎርም የሚሰጥ ነው፡፡ ይህም ነገር እንደ ሞዴል መጠን መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ፡-በዚህ ጥበብ የሲኒ ሞዴል የሚሰራ ከሆነ እንደ ነጌቲቭ የሚንጠቀመዉ ከገበያ የሚገዛ ሲኒ ነው፡፡
- **ሳሙና ፣ ዘይት፣ ቫዚሊን እና የመሳሰሉት**:ይህ ደግሞ የሚሰራ ሞዴል ከነጌቲቭ አካል ጋር እንዳይያያዝ ያገለግላል፡፡ ይህም የሞዴል አካል ከነጌቲቭ ጋራ በሚሰራበት በኩል ሲሆን፤ በነጌቲቭ አካል በውሥጥ በኩል የሚንሰራ ከሆነ፤ በውስጥ በኩል እንቀባለን፡፡ በውጪ በኩል የሚንሰራ ከሆነ እንቀባለን፡፡በአከባቢያችን ከሚንገኝ ነገሮች መስራት እንችላለን፡፡
- **ቀለም**፡የሚሰራ ሞዴል ከተሰራ በኋላ በሰራ ሞዴል ላይ አስፈላጊ ዲዛይን ለመስራት/ለማስዋብ የሚያገለግል ነው፡፡
- **የብርጭቆ ወረቀት**፡በዚህ ስራ የብርጭቆ ወረቀት ጥቅም የተሰራውን ሞዴል አካል ለማስተካከል/ለማሸት ያገለግላል፡፡
- **ጨው**፡ የተቦካ ወረቀት እንድብላላ ያገለግላል፡፡

## ለ. የፔፐር ማሼ አሰራር

ከፔፐር ማሼ የተለያዩ ሞዴሎች የሚሰራበት ሁኔታ ከሚቀጥለው መረዳት እንችላለን፡፡

- ለዚህ ስራ የሚያገለግል ወረቀት በማቆራረጥ በንፅሁ ውኃ ውስጥ እንድረጥብ ማቆየት፡፡
- በእህል ዱቄት የሚንጠቀም ከሆነ፤ የእህል ዱቄት እና በጨው የተበጠበጠ ውኃ በመጨመር ሊጥ ማዘጋጀት፡፡ ይህም ሊጥ እሳት ላይ በመጣድ ከፈላ በኋላ

እንዲቀዘቅዝ ማድረግ፡፡ ኮላ ማግኘት የሚንችል ከሆነ ደግሞ በዱቄት ሊጥ ፋንታ ኮላ መጠቀም እንችላለን፡፡

- በውኃ ውስጥ የረጠበ ወረቀት በሊጥ ወይም ከኮላ ጋር ማዋሃድ፡፡
- ሊጥ እና የተቦካ ወረቀት ሲናደባልቅ እኩል በሆነ መጠን መሆን አለበት፡፡
- በደንብ እንድብላላ ለሃያ አራት (24 ሰዓት) ማቆየት፡፡
- ለሚሰራ ሞዴል እንደ ነጌቲቭ አከል የሚያገለግል ነገር ማዘጋጀት
- ሞዴል በመሚሰራበት በኩል ነጌቲቭ አካል ሳሙና ወይም ዘይት መቀባት፡፡
- የተደባለቀ ወረቀት እና ሊጥ በደንብ ታሽተው መስራት በፈለግን ሁኔታ ዘይት ወይም ሳሙና በተቀባበት በኩል በነጌቲቭ አካል ላይ በመለጠፍ ሞዴሉን መስራት፡፡
- የሚሰራ ሞዴል ደርቀው የነጌቲቭ አካል እስክለቅ ድረስ እንዲቆይ ማድረግ፡፡ የሚሰራ ሞዴል ከደረቀ በኋላከነጌቲቭ አካል ማስለቀቅ፡፡
- ከተቦካ ወረቀት የተሰራ ሞዴል ደርቀው ከነጌቲቭ አካል ካስለቀቅን በኋላ እኩል ያልሆነ ቦታ በብርጭቆ ወረቀት በማሸት እኩል ማድረግ፡፡
- በመጨረሻም ቀለም በመጠቀም የተሰራውን ሞዴል ላይ ዲዛይን በመስራት ማስዋብ፡

**ከዚህ በላይ የተዘረዘረዉን የተቦካ ወረቀት አሰራር በመከተል፤ የጎርጓዳ ሳሃን ሞዴል በመስራት ለክፍል አቅርቡ፡፡**

ከተቦካ ወረቀት የተለያዩ ሞዴሎችን መስራት እንደሚቻል ተምረሃል፡፡ ስለዚህ ለፔፐር ማሼ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማዘጋጀት፤ ከላይ የተገለፀውን የፔፐር ማሼ አሰራር በመከተል፤ ጎርጎድ ያለ ሳሃን በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ የዚህ ስራ ውጣውረድ እና ያጋጠማችሁን ነገር እንዲሁም ምን እንደተማራችሁ ለክፍል ተማሪዎች አስረዱ፡፡

**ተግባር 10**

የሳህን ሞዴል ከሰራችሁ በኋላ የሚከተለዉን አሰራር በመከተል፤ ከፔፐር ማሼ ከአዋፋት፣ የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳት በመምረጥ ከሰራችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ በመጨረሻም አጠቃላይ የስራ ሂደት እና በዚህ ስራ ያጋጠመዉን ነገር እንዲሁም የተማራችሁበትን ነገር ለተማሪዎች አስረዱ፡፡

**የአሰራር ቅደም ተከተል**

- የምትፈልጉትን ንድፍ በወረቀት ላይ በእርሳስ የአዋፋት፣የቤት እንስሳት እና የዱር አራዊት ንደፉ፡፡
- የተሰራውን ንድፍ በማየት የእንስሳት ሞዴል መስራት ከፈለጋችው፤ በሽቦ ሞዴሉን መስራት ትችላላችሁ፡፡ሽቦ ለማግኘት የሚያስቸግር ከሆነ በክር እና ቀጫጭን እንጨት መጠቀም ይቻላል፡፡

  .የተቦካ ወረቀት እና ከኮላ ጋር በማዋሃድ አዘጋጁ፡፡
- ፎርሙን በሽቦ ወይም ከእንጨት በተሰራ ላይ የተቦካውን ወረቀት በትንሹ የሚሰራውን ፎርም በማየት ማያያዝ፡፡
- ትንሽ ከቆያችሁ በኋላ ከላይ መጨመር፡፡
- በመጨረሻም የሚሰራ ነገር እስከ መስል ድረስ ስሩ፡፡
- ከጨረስክ በኋላ እንዲደርቅ ፀሀይ ውስጥ አድርጉ፡፡
- እኩል ያልሆነ አካል ላይ የሚስተካከለል ነገር ካሌ በብርጨቆ ወረቀት በማሸት ማስተካከል፡፡
- በመጨረሻም አስፈላጊ የሆነ ዲዛይን በሞዴሉ ላይ በመስራት በቀለም አሳምሩ፡፡

## 2. ወረቀት በማያያዝ ሞዴል መስራት

የዚህ ዘዴ ወረቀት በውኃ ውስጥ በመዘፍዘፍ የሚሰራ ሳይሆን፤ ወረቀት በማቆራረጥ በሙጫ/ኮላ ደጋግሞ በማያያዝ የተለያዩ ሞዴል የሚሰራበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ ስራ በጥሩ መልክ ከተሰራ የተለያዩ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳል የቤት እቃ እና ጌጣ ጌጥ መስራት ይቻላል፡፡.

በዚህ ዘዴ የሚሰሩ እቃዎች ኩባያ፣ሳሃን፣ ሰው፣የቤት እንስሳት እና የመሳሰሉትን መስራት ይቻላል፡፡

**ሀ. ለዚህ ስራ የሚያገለግሉ ነገሮች**

- ለዚህ ስራ ምቹ የሆነ ወረቀት ጋዜጣ፣ የተለያዩ መፅሔት እና የመሳሰሉት፡፡
- መቁረጫ/ከተር
- ሙጫ
- ለሞዴል የሚያገለግል ነጌቲቭ አካል
- የብርጭቆ ወረቀት

- እርሳስ
- ቀለም እና ብሩሽ
- ዘይት

**ለ. የስራዉ ሂደት**

- የሚሰራውን ሞዴል መወሰን፡፡
- ለዚህ ስራ የሚያገለግል ወረቀት ማዘጋጀት፡፡
- የተዘጋጀውን ወረቀት በመቁረጫ በቀጭኑ መቁረጥ፡፡
- ሞዴል በሚሰራበት አቅጣጫ በነጌቲቭ አካል ላይ ዘይት መቀባት፡፡
- ወረቀት በውኃ በመንከር፤ ሙጫ/ኮላ ሳይቀባ ለመጀመሪያ ዙር በነጌቲቭ አካል ላይ ማያያዝ እና መለጠፍ፡፡
- የተቆራረጠውን ወረቀት ሙጫ/ኮላ በመቀባት፤በማደራረብ ማያያዝ፡፡
- በዚሁ ሁኔታ ወረቀት እስከወፍር ድረስ ደጋግመሞ መለጠፍ፡፡
- መስራት የፈለግነውን ሞደል ከመሰለልን እንዲደርቅ ፀሀይ ላይ ማስቀመጥ፡፡
- ከደረቀ ቦኋላ ዳር ላይ የሚቀሩ ወረቀት ስለት በሆነ ነገር ማስተካከል እና የማያስፈልግ ነገር መቁረጥ፡፡
- የተሰራውን ሞዴል ከነጌቲቭ አካል ማለያየት፡፡

በዚህ ስራ መታወቅ ያለበት ነገር፤ ወረቀት በሙጫ/ኮላ በመቀባት በነጌቲቫ አካል ሳንያያዝ በፊት፤ በመጀመሪያ ዙር ወረቀት በዉኃ በመንከር፤ በነጌቲቭ አካል ላይ ማያያዝ የሚንሰራበት ወረቀት ነጌቲቭ አካል እንዳይነካ ያገለግላል፡፡

- የተሰራውን ሞዴል በብርጭቆ ወረቀት በማሸት ማስተካከል፡፡
- በመጨረሻ ለማሳመር ኮላ አቅጥነን በብሩሽ መቀባት፡፡
- ከዚህ በኋላ እንዲደርቅ ማድረግ፡፡
- ይህ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ወይም ሞዴሉ ከደረቀ በኋላ ቀለም በመቀባት የተለያዩ ዲዛይን በማሳመር እንደጥቅሙ መጠቀም እንችላለን፡፡

**ተግባር.11**


ወረቀት በሙጫ/ኮላ በማያያዝ የተለያዩ ሞዴሎች እንደሚሰራ ተምራቸዋል፡፡ ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሟላት፣ ወረቀት በማቆራረጥ የሉል ሞዴል እነደሚሰራ የሚከተለዉን ቀድም ተከተሉን በመከተል፣ የሉል ሞዴል በመስራት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡ በመጨረሻም ያለዉን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ከተማሪዎች እና ከመምህርህ ተቀበሉ፡፡

## ሐ. የአሰራርሂደት ቅደም ተከተል

- ለዚህ ስራ የሚመቸውን ወረቀት በቀጫጭን መጠን በመቁረጥ ማዘጋጀት፡፡
- እንደ ነጌቲቭ አካል የሚያገለግል መሳሪያ አዘጋጁ፡፡ ለምሳሌ፡- ክብ ቅርጽ ያለው ድስት ወይም ለዚህ ስራ የሚሆን ጎድጓዳ ሳህን፡፡
- በመቀጠል ነጌቲቭ አካል ዘይት መቀባት፡፡
- በመጀመሪያ ዙር የነጌቲቭ አካል ወረቀት ውኃ ውስጥ በመንከር አያይዙ፡፡
- በሁለተኛ ዙር በውኃ ተነክሮ የተያያዘውን ወረቀት ላይ ሙጫ/ኮላ በመቀባት ሌላ ወረቀት በማያያዝ መስራት የፈለግነውን ቅርፅ እስክመስል ድረስ ማያያዝ፡፡
- እንዲደርቅ ፀሀይ ላይ አድርጉ፡፡
- ከደረቀ በኋላ፣ ዳር ላይ የሚቀሩ ወረቀት ስለት ባለው ነገር በመቁረጥ ማስተካከል፡፡ ይህም ክብ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ከነዚህ ዘዴዎች አንዱ የሚንሰራበት ሞዴል በታች በኩል ግማሽ ክብ አካፍላችሁ በስፒል/በአከባቢያችሁ በሚገኝ ነገር አያይዙ፡፡
- መርፌ/በአያይዛችሁት ነገር ላይ ክር በማሰር፣በሌላኛው ክር ጫፍ እርሳስ በማሰር፣ ክብ መስመር ስሩ፡፡
- የሚናሰምረው መስመር እኩል በሆነ ርቀት/ራዲየስ ማስመር አለብን፡፡

በዚሁ መሰረት ሁለተኛዉን ሞዴል በመስራት ለሉል/ግሎብ/ ስራ የሚመቸዉን ወረቀት አዘጋጁ፡፡

የዚህ ስራ አሰራር ግልፅ እንዲሆንላችሁ ከታች ያለዉን ስዕል ተመልከቱ፡፡





በዚህ ስራ ሁለት የተዘጋጁ ሞዴሎች እንዳይበላለጡ በሁለቱም ላይ በእርሳስ የሚሰራውን በመስመር መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ይህ ካልሆነ ሁለቱ የሚሰሩ ሞዴሎች ስለሚበላለጡ፤ ላይገጣጠሙ ይችላሉ፡፡ በዚሁ ሁኔታ ሌላ ዘዴ ካለ መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህ ሁለቱ ቅርፆች እንዲያያዙ/እንዲገጣጠሙ፤በተለያየ ዘዴ መጠቀም ይቻላል፡፡ይህምመካከለኛ ውፍረት ያለው ወረቀት/ ወርዱ ስድስት ሴንት ሜትር (6ሴ.ሜ) እና ርዝመቱ ከተሰራ ሞዴል አፍ ጋር እኩል የሆነ ክላሰር አዘጋጁ፡፡ ይህን ወፍራም ወረቀት ሶስት ሶስት ሴንትሜትር ሁለት ቦታ አካፍሉ፡፡

- እስከ ሶስት ሴንትሜትር (3ሴ.ሜ) ሙጫ/ኮላ ቀቡ፡፡
- ሙጫ/ኮላ በተቀባዉ በኩል በአን ቅርፅ ውስጥ በማስገባት፤ የተሰመረዉን መስመር በመከተል በአፉ ቅርፅ ወረቀቱን በማዞር አያይዙ፡፡
- ሶስት ሴንትሜትር ያህል የቀረዉ ደግሞ ወደ ዉጪ ይቀራል፡፡
- ሶስት ሴንትሜትር ወረቀት/ክላሴር በኣንዱ ቅርፅ አፍ ወደላይ የቀረዉን በማዞር በዉጪዉ በኩል ሙጫ/ኮላ ቀቡ፡፡
- ሁለተኛዉን ስራ በማምጣት ሙጫ/ኮላ የጠቀባዉን ክላሰር በውስጥ በኩል በማድረግ ክደኑ፡፡
- በውስጥ በኩል ሙጫ/ኮላ የተቀባዉ ወረቀት ሁለቱን ቅርፅ ለማያያዝ ያገለግላል፡፡
- ይህ የተሰራ የሉል ሞዴል የአፉ ዳር ተስተካክለው እና ተያይዘው ከደረቀ በኋላ፤ የተሰራውን ሞዴል በውጪ በኩል የሚበላልጠውን ቦታ በብርጭቆ ወረቀት በማሸት ማስተካከል፡፡

- ሙጫ/ኮላ በማቅጠን ሞዴሉን በዉጪ በኩል ቀቡ፡፡ ይህም የሚቀባ ቀለም ወረቀቱ እናዳይመጥ እና የቀረ ቀዳዳ ካሌ ለመድፈን ያገለግላል፡፡
- ሁለቱ ቅርፅ ከተያያዘ በኋላ የስፍር ፎርም ወይም ሉል የሚመስል ቅርጻ ቅርጽ ማግኘት እንችላለን፡፡
- የአለም ካርታ/ የሉል ስዕል ከመፅሐፍ ወይም ከሌላ ነገር በማየት ውኃ ያለበት ቦት ነጭ-ሰማያዊ (ውኃ ሰማያዊ) ቀለም ቀቡ፡፡ መሬት ያለው ቦታ ደግሞ የተመረጠውን ቀለም ቀቡ፡፡
- በመጨረሻም የመሪዲያን እና ሎንግትዉድ እንዲሁም የመሬት ወገብ የሚያሣይ መስመር በመስራት እንደግሎብ መጠቀም እንችላለን፡፡

ከዚህ በላይ የተገለፁት ዘዴዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ዘዴ የተሰራዉን ሉል/ግሎብ ተመልከቱ፡፡



ስዕል 2.3 ወረቀት በማያያዝ የተሰራ ሞዴል

ለክፍል ከአቀረቡ በኋላ በእርስበርሳቸዉ ስራ ላይ ጠንካራ ጎን እና ደካማ ጎን በመለየት፤ ስራዎቻቸዉን እንዲያደንቁ አድርጉ፡፡  በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታታት ጠንካራ

እና ደካማ ጎናቸው ለወደፊት ስራቸዉን ለማሻሻል እንደሚረዳቸው በመስረዳት የማጠቃለያ ሃሳብ ይስጡዋቸው፡፡

**የምዕራፍ 2 መልመጃ መልስ**

I. **የእዉነት ወይም ሐሰት መልስ**

1. ሐሰት 2. ሐሰት 3. እዉነት 4. እዉነት 5. ሐሰት

**6.እዉነት 7. ሐሰት 8. ሐሰት 9. ሐሰት 10. እዉነት**

**11. ሐሰት 12. እዉነት 13. እዉነት 14. ሐሰት 15. እዉነት 16. ሐሰት 17. እውነት 18. እውነት 19. ሐሰት**

II. **የምርጫ መልስ**

**1. ሀ 2. ሐ 3. መ 4.መ 5.መ 6.መ 7. መ 8. ሠ 9. መ 10. ለ 11.ለ 12. ሐ 13. ለ 14. ሐ 15. ሀ 16. መ**

# ምዕራፍ 3: የስነ-ጥበባት ባህልና ታሪክ

*ለዚህ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ.........9*

## የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤት:

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት ቦኋላ ተማሪዎች፤

- የሙዚቃን ባህላዊ እሴት ይለያሉ፡፡
    - ሙዚቃ በባህል ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ይለያሉ፡፡
    - የሙዚቃ፣ሙዚቃ መሳሪያዎችና ዉዝዋዜ ግንኙነት ይገልፃሉ፡፡
    - የሃውልት፣መታሰቢያ ሀዉልትና ቅርጻ ቅርጽ  ምንነትና  ትርጉም መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራሉ፡፡
    - የሃውልትን ትርጉም ይገልፃሉ፡፡
    - በጥንት ዘመን ከተሰሩት ሃውልቶች ውስጥ ጥቂቶቹን አይተው ያደንቃሉ፡፡

**መግቢያ**

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የምት ጠቀሜታ በሶልፌጂዮ ውስጥ፣እንዴት እንደምናነብ፣የአንቺ ሆዬ ለኔና አምባሰል ቅኝት በመታገዝ እንዴት መጨወት እንደሚቻል ተምራቿል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሙዚቃ፣የሙዚቃ መሣሪያና ውዝዋዜ በባህል ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ትማራላችሁ፡፡ የእጅ ስራ ሙያ የተለያዩ  ነገሮችን ያካትታል፡፡ለምሳሌ፣ ከድንጋይ የተሰሩ መሳሪያዎች፣ከሸክላና ብረት  የተሰሩ መሳሪያዎች እንደ ጦር ሲጠቀሙበት ነበር፡፡ እንዲሁም ለውበት የሚውሉ  ነገሮች እንደ ልብስ አዝራር/የልብስ ቅልፍና የህክምና ልብስ ያካትታል፡፡ሐውልቶችና የመታሰቢያ ሐውልቶች  የተሰሩበትን ሁኔታ ልዩነት ቢኖራቸውም በሚያስተላልፉት መልዕክት ላይ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

ማንኛም የስነ-ጥበብ ስራ ከህብረተሰቡ ኑሮ ሁኔታ ጋር እንደሚያያዝ ባለፉት ትምህርት ክፍል ከተማራችሁ ተረድታቿል፡፡ስነ-ጥበብን ለመስራት እንደ መነሻ ሀሳብ ሊሆንልን የሚችለዉ የህብረተሰብችን አኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የኦሮሞን አፈ-ታሪክ የሚናውቀውን ወደ ስነ-ትያትር በመቀየር ህብረተሰቡን  እንዲናስተምር ነው፡፡እንዲሁም

የማናዉቀዉንም በመጠየቅ እንዲንማር የሚጠቁመን ነው፡፡የዚህ ርዕስ ዋና ትኩረቱ የኦሮሞን ህዝብ ተረቶች ወደ ትያትርና ፊልም በመቀየር እንዲንችል ነው፡፡

## የምዕራፉ አንኳር ይዘቶች

3.1. የሙዚቃ ባህላዊ ገጽታ፣የሙዚቃ መሳሪያዎችና ዉዝዋዜ፡፡

3.2. ቅርጻ ቅርጽና የጥንታዊ ዘመን በእጅ የተሰራ ሀዉልት ታሪክ፡፡

3.3. በአከባቢያችን የሚታወቁ ተረቶችን በትያትርና ፊልም/ምስለ-ድምጽ መግለፅ፡፡

## 3.1 የሙዚቃ ባህላዊ ገጽታ፣የሙዚቃ መሳሪያና ዉዝዋዜ

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ………… 3**

### ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት

### በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች

- በህልን፣በሙዚቃ፤በሙዚቃ መሳሪያዎችና በዉዝዋዜ አኳያ ይገልፃሉ፡፡
- በህልን፣በሙዚቃ፤ በሙዝቃ መሳሪያዎችና በዉዝዋዜ አኳያ በህብረተሰብ ውስጥ ያለዉ ጥቅም ይዘረዝራሉ፡፡

የግንዛበ ጥያቄዎች

ተማሪዎቹ የግንዛቤ ጥያቄ ላይ እንዲወያዩ እና የውይይታቸውን ውጤት በክፍሉ ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ. ከዚያም ጥያቄውን ከሚከተሉት መሰረታዊ ሃሳቦች ጋር በማያያዝ ያብራሩ::

ባህላዊ ዘፈን፣ዉዝዋዜ፣እንዲሁም የሚዝፈንበትና የሚወዛወዝበት የራሱ የሆነ ምክኒያት አለዉ፡፡የሚንጠቀምበት የሙዚቃ መሳሪያዎችም እንደዝህ ናቸው፡፡ ሙዚቃ የህብረተሰቡ ያለዉን ቋንቋ፣ባህልና እሴት ከዉስጡ የያዘ ሆኖ ከዉዝዋዜና ሙዚቃ መሳሪያ ታጅቦ ይቀርባል፡፡እንዲሁም፣ሙዚቃና ዉዝዋዜ የህብረተሰባችንን የእምነት ስርዓት፣ ኢኮኖሚ፣ ባህልና ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የህብረተሰቡን ልምድ ለማሳደግና ለማስተሳሰር፣ እንዲሁም ባለበትነት እንዲሰማበትና እንዲሳተፍ በማድረግ ውስጥ ድርሻዉ ከፍተኛ ከፍተኛ ነው፡፡

ሙዚቃና  ባህላዊ ዉዝዋዜ ጀግንነትን የሚያሞግስ፣አንድ ሰዉ ለሀገሩ ያለዉን የሚያሞግስ፣ የአንድን ሰዉ ኑሮዉን ለማካሄድ የሚያሳየዉን  የግል ችሎታ ማድነቅና ሌሎች ስዎች እንደርሱ እንዲሰሩ ለማነሳሳት፣የማይሰሩትን ደግሞ ለመስደብና ለማበረታታት ህብረተሰባችን ይጠቀምበት ነበር፡፡አሁንም እየተጠቀመበት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ዉዝዋዜና ሙዚቃ ታሪክን ለመናገር ማቆየትና ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለማስተላለፍ፣ለህብረተሰቡ ዕድገት፣ ለሀገር ፍቅርና ደስታ ለመባል እየተከፈለበት የነበረዉ ዋጋ በቀላል መልኩ ትዉልድ እንዲማርበት ኃይል አለዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የቡድን ሥራ
- ጥንድ ስራ
- የሙሉ ክፍል ውይይት
- ማብራሪያ
- ጥያቄ እና መልስ
- የፕሮጀክት ሥራ

## የትምህርት መርጃ መሣሪያ

ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚያገለግሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ።

- የልምምድ ክፍል
- የሙዚቃ መሳሪያዎች

**የመምህሩ ድርሻ**

- ተማሪዎች በለፉ ርዕስ ውስጥ የተማሩትን ስለ የበህላዊ ዉዝዋዜ በመጠየቅ ርዕሱን መጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በህልን፣በሙዚቃ፣ በመሳሪያዎችና በዉዝዋዜ አኳያ የለዉን እይታ ለይ በጥንድና በቡድን እንዲዋያዩ በመድረግ ዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በንሁስ ርዕስ ሥር የተሰጠ ተግባር የተማሪዎችን እዉቀትና ችሎታን ለማወቅ ስለምረዳ ፣ወደ ገለጻ ከማግበታቸዉ በፊት በቡድን ተወያይተዉ እንዲገልጹ አድርጉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- በያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፣ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፣ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፣ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**ተግበር 1**

ተማሪዎቹ ፣ በአከባቢያቸዉ ስለምታወቀዉ ሙዚቃ፤ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና የባህል ዉዝዋዜዎች ጠይቀዉ ለክፍላቸዉ እንድያቀርቡ አድርጉ።

## 3.2 ቅርጸቅርጺ (የሃዉልት) ጥንታዊ የእጅ ስራ ታርክ

***ለዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ…………………3***

***ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:***

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- የሞኑመንት ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የሃዉልት እና የመታሰቢያ ሃዉልት ምንነት እና ትርጉም ይናግራሉ፡፡
- ከሞኑመንት ስራዎች አይነት የተወሰነውን በመለየት ይዘረዝራሉ፡፡

***መግቢያ***

የእጅ ጥበብ  ሙያ የተለያዩ ነገሮችን ይይዛል፡፡ ለምሳሌ፡- ከድንጋይ የተሰሩ እቃዎች፣ የሸክላ ስራዎች፣ ብረታ ብረት ደግሞ ጦር እንዲሁምለጌጣ ጌጥ የሚያገለግሉ የልብስ ቁልፎች፣ጌጥ እና ልብስ ሊሆን ይችላል፡፡

ሃዉልት እና የመታሰቢያ ሃዉልት አሰራር ብለያይም የሚያስተላልፉ መልዕክት ተመሳሳይነት አላቸዉ፡፡

***የመማር ማስተማር ዘዴ***

- መሳል
- ማሳየት
- የቡድን እና ጥንድ ዉይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- ፕሮጀክት

### የትምህርት መርጃ መሳሪያ

የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚያስፈለጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያ፡፡

- ስዕል
- ፖስተር

### የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎች ስለ የሃዉልት ቅርፃ ቅርፅ እና ጥንታዊ የእጅ ፅሑፍ ታሪክ በፊት ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲገልፁ በመጠየቅ፣ ይህን ምዕራፍ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ስለ ቅርፃ ቅርፅ እና ጥንታዊ የእጅ ፅሑፍ ታሪክ በግል ከሰሩ በኋላ፤በቡድን እንዲወያዩ አድርጉ፡፡ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት መረዳት ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዳ፤ ወደ ማብራሪያ ሳትገቡ በፊት በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ከአደረጋችሁ፤ ተማሪዎቻችሁ እንዲነቃቁ ይረዳል፡፡
- በያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፤ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፤ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡

*ተከታታይ ምዘና*

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ፡፡
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ
- ፈተና
- የግል እና ቡድን ፕሮጀክት፡፡

***መልስ*** በተማሪ መጻህፊ ውስጥ የውይይት ነጥቦችና ድርግቶች በተመለከተ ተማሪዎች በርዕሱ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ለይ በመመርኮዚ ተጨማሪ ገለፀና ግብረመለስ ስጡአቸዉ፡፡

**ዉይይት 1**

**የእጅ ሙያ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን በመወያየት፤ በመጨረሻም ለአጠቃላይ ሃሳብ ግብረ መልስ ስጡ፡፡**

የእጅ ሙያ ጥበብ ማለት በአጠቃላይ በሰዉ ልጅ የሚሰሩ ስራዎች መሳሪያዎች ወይም የስነ-ጥበብ ስራ፤ በተለይ ለአርክኦሎጂ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን የሚገልፁ ናቸው፡፡ በአርክኦሎጂ የእጅ መያ ስራ የሚባል ቃል በአጠቃላይ ለመሳሪያዎች የሚንጠቀማቸዉ እቃ የሚል ሲሆን በስነ-ጥበብ ታሪክ ደግሞ የስነ-ጥበብ ስራ መሆኑን በደንብ አስረዷቸዉ፡፡

የእጅ ጥበብ ሙያ የተለያዩ ነገሮችን ይይዛል፡፡ ለምሳሌ፡- ከድንጋይ የተሰሩ እቃዎች፣ የሸክላ ስራዎች፣ ብረታ ብረት ደግሞ ጦር እንዲሁምለጌጣ ጌጥ የሚያገለግሉ የልብስ ቁልፎች፣ጌጥ እና ልብስ ሊሆን እንደሚችል አስረዷቸዉ፡፡

የእጅ ሙያ ስራዎች የባህሪይእና ለዉጥ ዉጤት ነው፡፡ የባህሪይ ሂደት የጥሬ እቃ ግኝት፣ ወሳኝ የሆኑትን ነገሮችን ማምረት እና ከተጠቀምንባቸዉ በኋላ የሚወገዱትን ይይዛል፡፡

የለዉጥ ሂደትየባህሪይ ለዉጥ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥል ነው፡፡ ይህም የእጅ ሙያ መለወጠዉ በተፈጥረዉ ወይም ሰዉ-ሰራሽ ነገር ከተገኘ በኋላ ነው፡፡ ይህ ሁለቱ ሂደቶች የእጅ ሙያ ስራዎች ይዘት ቅድመ ሁኔታዎችን ለመመዘን እንደሚያስፈልግ አስረዷቸዉ፡፡

የእጅ ሙያ ትርጉም በዚህ ሁኔታ ከገለፃችሁ በኋላ፤ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፤ ስለ የእጅ ሙያ  የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

**ዉይይት2**

*ሞኑመንት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን እንዲወያዩ አድርጉ፡፡ በመጨረሻም ለአጠቃላይ ሃሳብ ግብረ መልስ ስጡ፡፡*

ሞኑመንት ማለት የቤት አሰራር ወይም የአንድን ህብረተሰብ ጥንታዊ/ታሪካዊ ክንዉን መሆኑን አብራሯላቸዉ፡፡ ሞኑመንት ለታሪካዊ ነገር ወይም ታሪካዊ ቅርስ በጥበባዊ፣ ታሪካዊ፣የፖሎቲካ መልዕክቶች እና ጥቅም ቀላል በሆነ አሰራር ለማስታወስ የሚሰራ መሆኑን ንገሯቸው፡፡ ሞኑመንት የተለያዩ ስራዎችን ይይዛል፡፡ ለምሳሌ፡-የመታሰቢያ ሃዉልት፣ሃዉልት፣ታሪካዊ ግንባታ፣የአርክኦሎጂ ቦታዎች፣ቱባ ባህሎች እና የመሳሰሉት እንደሆኑ ንገሯቸዉ፡፡

ሞኑመንት የሚል ቃል ከላቲን ቋንቋ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም *ማስታወስ* ወይም *መምከር* ማለት ነው፡፡ ሞኑመንት ያለፉት ነገሮች  ምን እንደሚጠቅሙን ግንዛቤ በማስጨበጥ፤ የወደፊቱን ደግሞ በደንብ አይተን እንዲናዉቅ እንድንረዳን እና የመታሰቢያ ሃዉልት በህይወት የሌሉትን ነገሮችን ለማስታወስ የሚሰራ መሆኑን በደንብ  አብራሯላቸዉ፡፡

ሞኑመንት ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያየ ቦታዎች ከሺዎች አመታት በላይ ያስቆጠሩ እና ረጅም እድሜ ያላቸዉ  ሆነው፤ የሰዉ ልጅ የጥንት ስልጣኔ እድገት ማሳያ ነው፡፡ ስለዝህ በጥንት ዘመን የተሰሩ ትልልቅ የሆኑ ሞኑመንት በአከባቢ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር ብዛት ያላቸዉ እና ምንያህል በስልጣኔ እንዳደጉ የሚያሣይ መሆኑን አስረዷቸዉ፡፡

ለተለያዩ ጉዳዮች የተሰሩ ግንባታዎች ከእዉቅና፣እድሜ፣መጠን እና ታሪካዊ ከመሆናቸው የተነሳ እንደ ሞኑመንት ይቆጠራሉ፡፡ ምክንቱም ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ እና በመጠን ትልቅ ስለሆኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም የጥንት ዘመን እና ታሪካዊ ከመሆናቸው የተነሳ ነው፡፡

ብዙ ሃገራት ሞኑመንት እና በጥንት ዘመን የተሰሩት ሌላ ነገሮች የተጠበቁ ግንባታ እና የአርክቴክቸር ስራዎችን ለማሳየት እንደሚያገለግል አስረዷቸዉ፡፡

ሞኑመንት ታሪካዊ የሆኑ እና የፖለቲካ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም የህብረተሰቡ ወሳኝ ክንዉኖች ለማስተማር እንደሚረዱ አስረዷቸዉ፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልቶች አንደ ታሪካዊ ቅርስ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን በጦርነት ወይም ከግጭት የተነሳ ታሪካዊ ቅርሶች ልወድሙ እንደሚችሉ ንገሯቸዉ፡፡

ሞኑመንት ብዙ ነገር ይይዛል ከነዚህ የተወሰኑትን እንመልከት፡-

- የመታሰቢያ ሃዉልት
- ሃዉልት
- በጥንት ጊዜየተሰራ ቤቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡.

የሞኑመንት  ትርጉም በዚህ ሁኔታ ከገለፃችሁ በኋላ፣ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፣ ስለ የሞኑመንት  የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋገጡ፡፡

**ዉይይት3**

*የመታሰቢይ ሃዉልት ማለት ምን እንደሆነ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች ከአቀረቡ በኋላ፣ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት ለሃዉልት ትርጉም አጠቃላይ ሃሳብ ግብረ መልስ እንደሚከተለዉ ስጡ፡፡*

የመታሰቢያ ሃዉልት ብዙ ጊዜ በህይወት ለሌሉ ሰዎች እና እንስሳቶች በአደባባይ የሚቆም/የሚሰራ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በህብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት፣ክብር፣እዉቅን እና ተቀባይነት ያላቸዉ ሰዎች ማለትም የሃገር መሪዎች፣ ጀግኖች፣የተለያዩ ግኝቶችን ያገኙ ሰዎች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ጠሆኑ ሰዎች እና ለመሳሰሉት እሴት፣ታሪክ፣እዉቀት፣ጀግንነት እና መሪነታቸዉን ለሚቸጥለዉ ትዉልድ ለማስተላለፍ የሚሰራ ነው፡፡የመታሰቢያ ሃዉልት ብዙ ጊዜ ሰዎች ከተሰዉ በኋላ የሚሰራ ቢሆንም፣ በሕይወት ላሉ ሰዎችም ሊሰራ እንደሚቻል ንገሯቸዉ.

የመታሰቢያ ሃዉልት ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራበት ዘዴ ቢሆንም ልዩነት ይኖራቿል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ሲንል የስነ-ጥበብ ስራ ሆኖ ቁመት፣ርዝመት እና ወርድ ያለዉ ወይም ጠጣር የሆነው

በእጅ የሚዳሰስ እና ዙሪያዉን በመዞር ማየት እንደሚቻል ንገሯቸዉ፡፡ ነገር ግን ቅርፃ ቅርፅ ሲንል ጥበባዊ መሆን አለበት፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሙሉ በሙሉ በባለ ሙያ /የፈጠራ ችሎታ በቀራፂ የሚሰራ ነው፡፡ ይህ የፈጠራ ስራ የመታሰቢያ ሃዉልት መስራት ውስጥ አይታይም፡፡

የመታሰቢያ ሃዉልት ብዙ ጊዜ ከሸክላ አፈር፣ግንጋይ እና ብረታ ብረት/ ከነሃስ ይሰራል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ደግሞ የስነ-ጥበብ ስራዎች የሚሰራበት ዘዴ ሆኖ፤ ቁመት፣ወርድ እና ርዝመት ያለዉን በእጅ የሚዳደስ ሲሆን፤ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ለመስራት ከሚያገለግሉ ሁሉም የሚሰራ መሆኑን አስረዷቸዉ፡፡ ይህ ሃዉልት ብዙ ጊዜ ከሸክላ አፈር፣ግንጋይ እና ብረታ ብረት/ ከነሃስ ይሰራል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ደግሞ የስነ-ጥበብ ስራዎች የሚሰራበት ዘዴ ሆኖ፤ ቁመት፣ ወርድ እና ርዝመት ያለዉን በእጅ የሚዳደስ ሲሆን፤ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ለመስራት ከሚያገለግሉ ሁሉም የሚሰራ መሆኑን በደንብ አስረዷቸዉ፡፡

የመታሰቢያ ቅርፃ ቅርፅ ስራ ሙሉበሙሉ በተፈጥሮ ያለዉን ነገር በማስመሰል የሚሰራ ሲሆን፤ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ደግሞ በተፈጥሮ ያለዉን ነገር በማስመሰል የሚሰራ ቢሆንም፤ የተፈጥሮ ችሎታን ያካተተ ነው፡፡ ቀራፂ የመሚሰራ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ተመልካችን እንዲስብ/ማራኪ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ ነገሮችን በመጨመር ማሳመር እንዲችሉ በደንብ አስረዷቸዉ፡፡

ቅርፃ ቅርፅ እና የመታሰቢያ ሃዉልት ልዩ የሚያደርጋቸዉ መጠናቸው ነው፡፡ ብዝ ጊዜ የመታሰቢያ ሃዉልት በመጠን ተለቅ ተደርገዉ ያሰራል፡፡ በትንሹ የሚሰራ ከሆነም በተፈጥሮ ልክ መሆን አለበት፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ግን በመጠን የሚወሰን አይደለም፡፡ ወሳኙ የቀራፂዉ ትኩረት ቦታ/ሃሳቤን እንዴት ልግለፀዉ ብለዉ የሚሰራ? በምን ልስራ? ከሰራዉ በኋላ ቅርፃ ቅርፁን የት አቆማለዉ የሚለዉ ነገር ለዉ እንጂ፤ እንዴት ልስራ በሚለዉ ሃሳብ አይገባዉም፡፡ ይህ ማለት የሚያስተላልፈዉ መልዕክት መጨመር እና ማነስ በተሰራ ነገር በደንብ አስረዷቸዉ፡፡

ቅርፃ ቅርፅ አንድን ነገር የሚገልፅ አጠቃላይ ፎርም ወይም ምስል የሰዉ ልጅ በተፈጥሮ የሚመስለዉን አስመስለን መስራት አለብን፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልት ግን ሁልጊዜ የአንድን ነገር ምስል፤በተፈጥሮ ያለዉ ወይም የነበረዉን እናዳለዉ ለማስመሰል፤ የሚሰራ ሊሆን ይችላል፡፡ ስዕል/ምስል ስንል ደግሞ፤ ለምሳሌ፡- የሰዉ የመታሰቢያ ሃዉልት የሚንሰራ

ከሆነ፤ሰዉ በተፈጥሮ ያለዉን ነገር ሁሉም አስመስለን መስራት እናዳለብን በደንብ አስረዷቸዉ፡፡



*ስዕል.3.1. የአባገዳና ሀደ ሲንቄን የምየሰይ የመታሰቢያ ሃዉልት*

የመታሰቢያ ሃዉልት  ትርጉምእና ጥቅም  በዚህ ሁኔታ ከገለፃችሁ በኋላ፤ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፤ ስለ የእጅ ሙያ  የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋገጡ፡፡

## ዉይይት 4

በአከባቢያችሁ የመታሰቢያ ሃዉልት ካሌ፤ ለምን መታሰቢያ እንደተሰራ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ  ለክፍል ከአስረዱ በኋላ፤ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት ለአጠቃላይ ግብረ መልስ ስጡ፡፡

**ዉይይት** 5

*ሃዉልት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ  ለክፍል ከአስረዱ በኋላ፤ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት ለአጠቃላይ ግብረ መልስ ስጡ፡፡*

የድንጋይ ሃዉልት ሁል ጊዜ ቀጭን እና በቁመት ረጅም ሆኖ ይሰራል፡፡ ለኃይማኖታዊ፣ ፖሎቲካ፣ባህል፣ለበላይነት፣ እሴት እና ሌሎች ምልክቶችን ለማሳየት የሚሰራ ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታ ህብረተሰቡ ለንጉስ ያላቸዉን ክብር ለማሳየት ንጉሱ ሲሞት በመቃብራቸዉ ላይ የሚያቆሙት ነው፡፡ ሃዉልት ስዕል እንዳልሆነ አብራሯላቸዉ፡፡ የአንድን ነገር አጠቃላይ ፎርም የሚያሳይ መሆኑን አስረዷቸዉ፡

የመታሰቢያ ሃዉልት እና የድንጋይ ሃዉልት ልዩነት፤ የድንጋይ ሃዉልት ፎርም ሲሆን፤ የመታሰቢያ ሃዉልት ደግሞ በተፈጥሮ ያለዉ/የነበረዉን ነገር ምስል ነው፡፡  እንደ ሃገር ከሚታወቀዉ የድንጋይ ሓዉልት ውስጥ አንዱ የአክሱም ሃዉልት እንደ ሆነ አስረዷቸዉ፡፡

በአክሱም ከተሰራ ሃዉልቶች በአብዛኛዉ ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍለዉ በመሮ የተሰሩት ናቸው፡፡ በመሮ ብቻ እንደማይሰራ አስረዷቸዉ፡፡ ምክንያቱም የፎርሙ ግንባታ ዉበት በባህላዊ እና በቴክኖሎጂ ዘዴ በመጠቀም የሚሰራ መሆኑን አስረዷቸዉ፡፡ አክሱም ውስጥ ብዙ ሃዉልቶች ነበሩ፡፡ ነአሁኑ ጊዜ ግን የሚቆሙ/ያሉት በቁጥር ትንሽ ናቸው፡፡ ብዙዎች እንደተሰባበሩ አስረዷቸዉ፡፡ ምክንያቱም የአሰራር ጥራት፣ በጥንት ጊዜ በተከሰተዉ የእሳት ጎመራ ፍንዳታ እንዲሁም የጣሊያን ጦር በአድዋ ላይ ከመሸነፉ ጋር በተያያዘ አፀፋ ለመመለስ  ባደረሱበት ጥቃት ለ2ኛ ጊዜ ኢትዮጵያ ሲወሩ፤ ሃዉልቶች እና የተለያዩ ታሪካዊ ቅርሶችን ሲዘርፉ እና ስደመስሱ ስለነበር ተጎድቷል፡፡

አሁን በአክሱም ቆመዉ የሚገኙ ሃዉልቶች ዉብ እና ረጅም የሆነ፤ ርዝመቱ ሃያ አራት (24ሜትር) እና አንድ መቶ ስድሳ (160 ቶን) የሚመዝን ነው፡፡ ይህ ሃዉልት በጣም ተዉበዉ የተሰራ እና ሰዉን የሚስብ ነው፡፡ የመግቢያ በር ዲዛይን አስመስለዉ የሰሩትን፣ በሩ የተሰራዉ በሁለቱ በኩል እና  መስኮት አስመስለዉ የሰሩት በሁሉም አቅጣጫ ሲሆን በጫፍ ላይ ደግሞ ጎበጥ ያለዉ ፎርም በለዉ የተዋበ ነው፡፡ የአክሱም ሃዉልት ለንግስታት መታሰቢያ የቆሙ መሆናቸውን አስረዷቸዉ፡፡



*ስዕል.3.2. የአክሱም ሃዉልትን የሚያሳይ ምስል፡፡*

የመታሰቢያ ሃዉልት  ትርጉምእና ጥቅም  በዚህ ሁኔታ ከገለፃችሁ በኋላ፤ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፤ ስለ የእጅ ሙያ  የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋገጡ፡፡

**ተግባር  2**

በአከባቢያችሁ የተሰራ ሃዉልት አለ? ካሌ የምን ሃዉልት እንደሆነ እና ለምን እንደተሰራ በተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ወይም ታላላቅ ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡ ፡

በመጨረሻም ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት፤ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸው በመለየት ለማጠቃለያ

ሃሳብ  ግብረ መልስ እንደሚከተለዉ ስጡ፡፡

**ተግባር 3**

በአከባቢያችሁየጥንት ጊዜ የተሰራ ቤት አለ? የሚኖር ከሆነ የጥንት ጊዜ ቤትምንነት እና ለምን እንደተሰራ ቤተሰቦቻችሁን ወይም ታላላቅ ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡

በመጨረሻም ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት፣ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸው በመለየት፣ ለማጠቃለያ ሃሳብ  ግብረ መልስ እንደሚከተለዉ ስጡ፡፡

በሃገራችን በጥንት ጊዜ የተሰሩትን ቤቶችን ሲንመለከት፣ በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ቤተ-እምነቶች እና ቤተ-መንግስት ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ብዙ አለመኖራቸዉን ንገሯቸዉ፡፡ ይህ ቤቶች ከወጥ ድንጋይ የተቀረፁ በአብዛናዉ  በትግራይ እና በላሊበላ ይገኛሉ፡፡  በትግራይ የሚገኝ ከድንጋይ የተቀረፁ ቤቶች የክርስትና እምነት ወደ ሃገራችን ሳይገባ በፊት የተሰሩ እና ለተለያዩ እምነት ጉዳዮች ሲገለገሉበት እንደበበር አስረዷቸዉ፡፡


በላሊበላ አከባቢ ከአንድ ድንጋይ የተወቀረ ቤተ-እምነት መሰራት የተጀመረዉ፣ በ6ኛ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ታሪክ እንደሚያስቀምጥ አስረዷቸዉ፡፡ ይሁን እንጂ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ያገኘዉ፣ በአብዛኛዉ በአንድ ቦታ መሰራት የጀመረዉ በ12ኛ ክፍለ ዘመን በላሊበላ ንጉስ ጊዜ ነበር፡፡የላሊበላ ንጉስ ከተለያየ ምክያቶች ጋር ተያይዞዉ፣ በአንድ ቦታ የሚገኙ ቤተ-ክርስቲያን ከእሳተ ጎመራ ድንጋይ በመፈልፈል ሲያሰራ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡

ቤተ-እምነቶችን ከድንጋይ አዋቅሮ የሚሰሩበት ምክንያት፣ ጥንካሬ ስላለዉ እንዲሁም አደጋን እና የተለያዩ ሁኔታዎችና መቋቋም መቻሉ ነው፡፡ እሂንን ቤተ-እምነት ልዩ የሚያደርገዉ ቤት ሲሰራ ከመሰረቱ ወደ ላይ ይሰራል፡፡ ይህ ግን ተቃራኒ የሚሰራ ነው፡፡ ልክ በሰዉ እግር በታች እየተሰራ የሚሄድ እና በመጀመሪያ ከላይ ያለዉ ይሰራል በመቀጠል፣ዝናብ  ማስተላለፍያ፣መስኮት፣በር  እና  የመሳሰሉትን  እያሉ  ወደ  ታች እንደሚሰራ አስረዷቸዉ፡፡

በላሊበላ የሚገኙ ቤተ-እምነቶች በሆነ በኩል ከድንጋይ ጋር የተያያዙት ሆነው በሆነ ድግሪ ፈቀቅ ብለዉ ይገኛሉ፡፡ ይህ ማለት መሰረታቸዉ እና በአንድ በኩል ከተፈለፈለበት ድንጋይ ጋር ተያይዟል፡፡ እንዲሁም እራሳቸዉን ችለዉ የቆሙ እና በሁሉም አቅጣጫ መታየት የሚችሉም እንደሚገኙ ለተማሪዎች ንገሯቸዉ፡፡

በአጠቃላይ ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍለዉ በሰሜን ሃገራችን የሚገኙ ቤተ-እምነቶች በቁጥር የሆኑት በላሊበላ ንጉስ ጊዜ የተሰሩ አስራ አንድ (11) ናቸው፡፡ የላሊበላ ንጉስ እሂንን ቤተ-

እምነት ለማሰራት ሃያ አራት (24 ዓመታትን) እንደፈጀባቸዉ የሚከተለዉን ስዕል ለተማሪዎች በማሳየት በደንብ አስረዷቸዉ፡፡



ስዕል.3.3 የላሊበላ ቤተ-እምነት የሚያሳይ ምስል፡፡

የጥንት ቤቶች ትርጉም እና ጥቅም  በዚህ ሁኔታ ከገለፃችሁ በኋላ፤ ሁሉም ተማሪዎች መረዳታቸዉን ለመለየት፤ስለ የጥንት ቤቶች  የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

**3.3 በአከባቢያችን የሚታወቁ ተረቶችን በትያትርና ፊልም/ምስለ-ድምጽ መቅረብ፡፡**
**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ…………3**

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፉት የሚገባቸው የትምህርት ብቃት**

**በዚህ ትምህርት ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች**

**ከዚህ ርዕስትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ተረቶችን ወደ ትያትር ጥበብና ፍልም በመቀየር በተግባር ያሳያሉ፡፡.
- የተረት-ተረት ምንነት ይረዳሉ

**የመማር ማስተማር መርጃ መሳሪዎች**

- የመለማመጃ አደራሽ/ክፍል (ትያትር አደራሽ)
- እርሳስ
- አልባሳት
- ወረቀት

**የትምህርት ይዘት መብራሪያ**

የዚህ ርዕስ ዋና ትኩረት በአከባቢያችን የምገኙ ተረቶችን በትያትርና በፍልም ጥበብ ማቅረብ የምቻለዉን በማቅረብ ማህበረሰባችን ማስተማርና በመዝናናት ነው፡፡ እነዲሁም ከመምህራን እንዲንማርና እቅጣጫ የምጠቆምን ነው፡፡ በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የእርግማን ልጅ በሚል ርዕስ የተቀመጠዉን ተራት እንዴት ወደ ተዉኔት መቀየር እንደሚችል ለተማሪዎች አስረዱ፡፡.

**የመምህር ድርሻ**

- ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፤ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፤ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.

- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**የተግባር 4 መልስ**

I. በዚህ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች ማህበረሰባቸዉ ውስጥ ያሉትን ለምሳሌ ተረቶችን፣ እንቆቅልሽ አባበሎችን እና የመሳሰሉትን በትያትር መልክ መስራት የሚችሉ መሆናቸውን በማስረዳት ከነዚህ ከተጠቀሱት አንዱን መርጠው እንዲያሳዩ አበረታቱ፡፡

**ታከታታይ ምዘና**

- የግል መብራሪያ
- የቡድን ሥራ ጽብሪቃ
- ቃለ-መጠየቅ
- የቤት ሥራ
- ንሁስ ፈተና
- መጠቃለየ ፈተና
- የተማሪዎች ኑበሬ  ወረቀት

## የምዕራፍ 3 መልመጃ መልስ

1 “የእዉነት ወይም ሐሰት” በማለት መልስ

1. እዉነት 2. እዉነት 3.እዉነት 4.እውነት 5.ሐሰት

6. ሐሰት 7. እዉነት 8.እዉነት 9.ሐሰት 10. እዉነት

11. ሐሰት 12. ሐሰት 13. ሐሰት

ለ. የምርጫ መልስ

1. ለ 2. መ 3.መ 4.ሀ 5.ሐ 6. ለ 7.መ 8.መ 9.መ 10.መ

# ምዕራፍ 4 : የስነ-ጥበብ መስህብነት

**የክፍለ ጊዜ ብዘት……17**

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ዉጤቶች**:

**ከዚህ  ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በተግባር የምቀርቡ ስነ-ጥባባትን ያናጻጽራሉሁ፡፡
- በአቀራረብ ስልቶቻቸዉ ላይ ያላቸዉን ልዩነት(ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣የትያትርና ፍልም ስነ-ጥበባት) ይለያሉ፡፡
- የሃዉልት ምልክቶች ያላቸዉን መልዕክት የስረደሉ፡፡
- ሃዉልት ለምን እንደተሰራ ይረዳሉ፡፡

**መግቢያ**

መፅሐፍ በፅሑፍ ታሪክን፣ዕሴት፣ባህል፣ምንነት፣የሰዎችን ማንነት ወይም አንድን ብሔር በፅሑፍ መልክ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለማስተላለፍ እንደሚረዳ ሁሉ፤ የሃዉልት ስራም የግለሰብ ወይም ብሔር ማንነት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡ የሃዉልት ስራ ምሳለነት ወይም አንድ ሰዉ ያለዉ መልካም ስራ ለትዉልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በአጭሩ፤ ሓዉልት መስራት መፅሐፍ ወይም ፊልም ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## የምዕራፉ አንኳር ይዘቶች

4.1. የስነ-ጥበባት ስራዎችን በተግባር ማሳየትጥቅሞች፡፡

**4.2. ትያትር ከሌሎች የስነ-ጥበብ ትምህርት ጋር ያለው ትስስር**

**4.3 የሃዉልት እና የጥንት ዘመን የእጅ ሙያ ምልክቶች መልእክት**

## 4.1. የስነ-ጥበባት ስራዎችን በተግባር የማስተማር ጥቅሞች

***ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ----------6***

***ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:***

***በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች ፡***

- የስነ-ጥበባት ጥቅምን ይዘረዝራሉ፡፡

ስነ-ጥበባት በምንጠቀምባቸው ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተለያዩ ጥቅሞች አላቸው፡፡ ይህም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በዕድገትና ልማት ውስጥ እና በጤና አጠባበቅ ውስጥ ስነ-ጥበባት የሚሰጡት ጥቅሞች የሚደነቁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የፈጠራ ችሎታዎችን ለማዳበር የስነ-ጥበባት ስራ ከፍተኛ ጠቃሜታ አለው፡፡ ከዚህም በላይ የስነ-ጥበባት ችሎታና ፍቅር ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለማህበራዊ ግንዘቤና ለመሳሳሉት ከፍተኛ ጠቃሜታ ስላላቸው ስነ-ጥበባትን በቅርፃ ቅርፅ፣ በሙዚቃና ውዝዋዜ፣ በትያትርና ድራማ እና በመሳሳሉት መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡

ተግባር 1

በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ስነ-ጥበባት የሚሰጡትን ጥቅሞች በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል አቅርቡ፡፡

***የመማር ማስተማር ዘዴዎች***

- ማሳየት
- የቡድን እና ጥንድ ዉይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- ፕሮጀክት

***የትምህርት መርጃ መሳሪያ***

የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚያስፈለጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያ፡፡

- ስዕል
- ፖስተር

በለፉት ክፍሎት ውስጥ እንደተማራቹት ፣የሙዚቃ አፈጣጠርን ፣በተመለከተ አንደንድ ምሁራን ፣እንደምሉት በተለይ፣የሙዚቃ መሣሪያዎች የተፈጠሩት በአከባቢያችን ፣ የምንሰማዉን፣ በተፈጥሮ፣በሉት ድምፆች በማስመሰል ነው፡፡ የስዉ ልጆች ያዩትን ሁሉ እያስመሰሉ እንደምሰሩ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ፣ጥቅት ምሳሌ ብናነሳሣ፣በሰማይ ላይ የምበሩ ወፎችንና በባህር ውስጥ የምወኙትን፣አሣዎችን በመመልከት ፣በጥናትና ምርምር ፣ በማስደገፍ ፣አይሮፕላን ፣መሰረት እንደቻሉ፣ይታወቃል፡፡ እባብን በመመልከት ባቡሪን ሠርተዉ ልክ እንደዚያዉ የሙዚቃ መሣሪዎችንም ፣በጥናትና ምርምር ተደግፈዉ እንደ ሰሩ ግልፅ ነው፡፡ በምሰማቸዉ ማራኪ ፣ድምጾችም፣እያስመሰሉ ከግጥም ጋር ፣በማቀናጀት ፣ እየተጨወቱ ተፈጥሮን ስያደንቁ ፣እንደ ነበረ ታሪክ ፣ያስረዳል፡፡ የወፎችምን ድምፅ ፣ እያስመሰሉ ፣ በግጥም እና ዜማ እንዴት እንደምጨወቱ ምሳሌ ብናይ፣

ጂላ፣

ጂላዬ…….(2)

ጂሊ፣ብቶ ቱሜ

ጂን ቦና ፣ዱሜ

ዮመነኬ፣ዱፉ

ራች ፣በር ፣ጋፍታ

ያን፣ወል ጋፍታ

ሰዱ፣ ጀቢ፣ ትክሳ

ጃርስ፣ሰንጋ፣ትክሳ

ጮመ፣ነዶ ገቴ፣

ሞርመ ፣ነኩቴ፣ጂቻ፣ከት፣ፉፉ

ትግበራ፣

በአከባቢያቸዉ ፣የምሰሙትን ፣ድምፆች፣ጊዜ ወስዳችዉ በጥሞና ፣

1.ጢት ማንም ሳይንቀሳቀስ

2.ማታ፣ሁሉም ፣ከተረጋጋ፣ቦኃላ፣ በጸጥታ ከልብ ስሙት !

ሀ.ምን ሰማቸዉ?

ለ.ዱሮ ልጆች ሆናቺዉ በምትሰሙት ፣ድምፅ እና ፣በአሁኑ፣መካከል ፣ልዩነት ፣አለዉ? ምን?

ሐ.ከዱሮዉ የተለየ፣አሁን ያለ፣ካለ፣ግለጹ

- የተፈጥሮ ድምፆች ምን ያህል፣የሰዉ ልጆችን፣እንደምማረኩ ግለጹ፣
- እነኝህን የተፈጥሮ ማራኪ ድምጾችን ፣ምን ያህል ታደንቃለቸዉ?ለቀጣይነታቸዉስ፣ ምን ማድግ አለበቸዉ?

እንግዲህ ፣ከላይ እንደየነው፣እርግብም፣ኩኩ፣ኩኩኩኩ.....እያለች ስትዘምር አናዉቃለን፡፡ በአከባቢያችንም ያሉ ትላልቅ ሰዎች ፣ስለ፣ተለያዩ ፣አራዊት መዝሙሮች ፣የምነግሩን ፣ነገር አለቸዉ፡፡

ኩኩ….ኩኩኩኩ..(2)

ጃርቲን ኤደ ዱቴ

ጆን ኬሬ፣ጉቴ

ኦቴን ፣ተቡሉቃ፣

ሙጫ ፣ሰቡሉቃ

ጉርባን ኤርጋ ዲዴ….እያሉ የድሮ ሰዎች የሙዚቃን ፣ድምጾች፣መሣሪያ፣ፈጥሯል፡፡ እነንተም በዚህ መሰረት የድሮ ትላልቅ ሰዎችን ፣ጠይቃችዉ በቡድን ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፣

## የቤት ሥራ

በአከባቢያቸዉ በምገኙ፣ቀላል ነገሮችን ፣በመተቀም ፣አንድ የምትወዱትን ፣የሙዚቃ መሣሪያ ፣ሠርታቸዉ አሰዩ፡፡

## 4.2. በተግባር የምታዩ ስነ-ጥበባትን ማነጻጸር (ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣የትያትር እና የፊልም ስነ-ጥበብ)

### 4.2.1. ትያትር ከሌሎች የስነ-ጥበብ ትምህርት ጋር ያለው ትስስር

***ለዝህ ርዕስ ትምህርት የተሰጣ ክፍለ ጊዜ …….3***

***ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:***

***በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች ፡***

- *የትያትር ጥበብ ከሌሎች ጥበብ ጋር ያለዉ ግንኙነት ይረዳሉ፡፡*

***አቢይ የትምህርት  ይዘቶች፣***

- *ሙዚቃ*
- *ዉዝዋዜ*
- *የእይታ ጥበብ*

***የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች***

- *የትያትር አደራሽ /የመላማመጃ ክፍል*
- *የትያትር አልባሳት*
- *የተለያዩ የትያትር ቁሳቁሶች*

***የትምህርት ይዘት መግለጫ/መብራሪያ***

*የስነ-ጥብብ ሥራ የምስብ የጥብብ ሥራ ነው፡፡ጥበብ ከሰዉ ልጅ ጋር ቁሪኝት ሰለለዉ ሰዎችን ለማሳብ ጥልቅ ምና አለዉ፡፡ለምሳሌ ማንኛዉንም ፍልም ተመልታቸዉ የፍልሙ ዋና ገፀ-ባህርይ የምያሳየዉን በህርይ ወይም ስራዉን በመዉደድ መመኘታቸዉ አይቀርም፡፡ሰለዚ የሙዚቃ ስራና የቪዧል አርት ከሌሎች ስራዎች ውስጥም  ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አንድን የጥበብ ሥራ ተመልክተን እንዲንወድ ያደረገዉ እንዲሁም እንዲናደንቅ ያነሳሳን አንዱ የጥበብ ዉበት ነው፡፡*

*በተግባር የምከናወኑ ወይም  የምታዩ ድርጊቶች በፅንስ ሀሳብ ከምገለጻዉ ልዩ ነው፡፡ ምክንያቱም በዓይናችን ስላየንና ስለዳምጠን እንዲሁም ለመማርም ጉልበትና ግዜያችንን ይቆጥበናል፡፡ለምሳሌ በአንደኛ ደረጃ ህሳብ ትምህርት ውስጥ እንደ ተማርከዉ ሥዕል*

ተጠቅማቸዉ መደመርና መቀነስ ተምራቿል፡፡ምክንያቱም በተግባር ወይም በስነ-ቅርፅ ስቀርብ ተማሪዎች በቀላሉ አይቶዉ በተጨባጭነት እንዲረዱ ይጠቅማቿል፡፡

በባለፈዉ ትምህርት ውስጥ ተዉኔትና ፍልም ተጠቅመን በትራካ መልክና በአፌ-ታሪክ እንዲሁም በሥነ-ጽሑፍ  የሕፃናቶች አይምሮ እንደምቀርፅ ተምራቿል፡፡  የስነ-ጥበብ ዓይነቶች ሁሉ (ዉዝዋዜ፣ሙዝቃ፣ስነ-ቅርፅ እና ሌሎች በፕሮዳክሽን ውስጥ የምያስተላልፉትን ምልዕክት ሙሉ ለማድረግ ከትያትር ጋር ተዛምዶ የተዋንያን አቀራረብ ፣በድርጊትና በመቼት የምያመሳስላቸዉ ባህርይ አሏቸዉ፡፡ማንኛዉም የስነ-ጥበብ ዓይነት ከትያትር ጥበብ ጋር የምያዘምዳቸዉ ተጨባጭ ልምድ አሏቸዉ፡፡ነገር ግን ከትያትር ጋር ግንኙነት ብኖራቸዉም በአጀማመር ታሪካቸዉ የተለያዩ ናቸው ፡፡እነዚ የስነ-ጥበብ ዓይነቶች ከትያትር ጋር ያለቸዉ ግንኙነት ለማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ሙዚቃ ማለት የአርት ዓይነት ሆኖ በድምፅ ስሜታችን የምያጎላ የጥበብ ዓይነት ነው፡፡አንድ የሙዚቃ አቀናባሪ ወይም አዘጋጅ የሙዚቃ ድረጊቱን የምያቀርብ ሰዉን ጠተቅመዉ የሙዚቃዉ ምልዕክት እንዲተላላፍ ያደርጋል፡፡አድማጮችምያደመጡትን ድምፅ ወደ ስሜትና ፍልስፍናቸው በመቀየር ጭብጡን ይቀበላሉ፡፡ስለዚ በድምፅ የተዘጋጅዉ ሙዚቃ መድረክ ላይ ማቅረቡ ከትያትር ጋር ያለዉ ግንኙነት ያሳየናል፡፡ ዉዝዋዜ ማለት የሙዚቃ ፐርፎርማንስ ሆኖ የተቀናጀ የአካላዊ እንቅስቃሴ በመደገፍ የሙዚቃዉን ጭብጥ ወይም ምልዕክት በተዘዋወሪም ሆነ በቀጥታ የምከናወን ነው፡፡ እንዲሁም በትያትር ውስጥ ዉዝዋዜ ጥልቅ ስፍራ ከመኖሩም አልፈዉ አካለዊ ብቃት እንደጨምር ያደርጋል፡፡ዉዝዋዜ ማት በድምፅ የምዘፈነው ሙዚቃ ወደ ትርጉም ያለዉ እንቅስቃሴ መቀየር ነው፡፡

ስለዚህ የዉዝዋዜ ጥበብ በሙዚቃ ተጅበዉ መድረክ  ስቀርብ ዉበት ሰለምኖረዉ የበለጠ ከትያትር ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፡፡ የእይታ ጥበብ ዓይነቶች ፣ሥዕል፣ስነ-ቅርፅ፣ቀለም ቅብ ና የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን የምያስተምር ጥበብ ነው፡፡ብዙን ጊዜ የጥበብ ሥራ የምያስተለልፈዉ መልዕክት በቀላሉ መገነዘብ አስቸጋሪ ነው፡፡

የእይታ ጥበብ ለመረዳት አስቀድመን የገፀ-ባህርይ ሁኔታ፣በለዉበት መቼትና ጭብጡን ማስተወል ግዴታ ነው፡፡ የእይታ ሰነ-ጥበብ  በትያትር ጥበብ ውስጥ መድረክ ላይ የምቀርቡ ትያትሮችን ለማስመር ጉልህ ሚና ይጨወታሉ፡፡የመድረክ ገፅታ ለተማልካች

እንዲያመች ዉበት የምያኖረዉ የእይታ ጥበብ ነው፡፡ይህም በትያትር ስራ ውስጥ የየገፀ-ባህርያት የዉስጣዊና ዉጫዊ ስሜትን ለማጉላት ይረደናል፡፡ለምሳሌ የገፀ-ባሪያት ንዴት፣ ደስታ፣ሀዘን ፣መከሳተር እና የመሳሰሉትን አጉልተዉ ለማሳየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖሯል፡፡ እንዲሁም በፊልም ጥበብ ሥራ ውስጥም የስነ-ጥበብ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ይህም ደግሞ በፍልም ውስጥ የምከናወኑ ክንውኖችን ተከትለዉ ከቀረጻ በኋላ እና በቀረፃ ጊዜ የምከናወኑ ስራዎችን ውበት ለመጨመር ስነ-ጥበብ ከትያትር ጋር ግንኙነት አለው፡፡

ጥበብ በተግባር ስቀርብ በቀላሉ የምናገኛቸው ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ትምህርት ለመማር ነው
- የምፈለገዉን ምልዕክት ለማስተላለፍ
- ሃሳባችንን ለማግለፅ
- ከሰዎች ጋር ተግባቦት ለመፍጠር

**የመምህር ድርሻ**

- ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፤ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፤ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
- መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**ተከታታይ የምዘና**

- የግል መብራሪያ
- የቡድን ሥራ ጽብረቃ
- ቃለ-መጠየቅ
- የቤት ሥራ
- ንዑስ ፈተና
- መጠቃለየ ፈተና
- የተማሪዎች ኑበሬ  ወረቀት

## 4.3 የሃዉልት እና የጥንት ዘመን የእጅ ስራ ሙያ ምልክቶች መልእክት

***ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ----------6***

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**:

**በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች ፡**

- የሃዉልት ምልክቶች ያላቸዉን መልዕክት ያደንቃሉ፡፡
- ሃዉልት ለምን እንደተሰራ ይረዳሉ፡፡

***የመማር ማስተማር ዘዴዎች***

- ማሳየት
- የቡድን እና ጥንድ ዉይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- ፕሮጀክት

***የትምህርት መርጃ መሳሪያ***

የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚያስፈለጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያ፡፡

- ስዕል
- ፖስተር

***የመምህር ድርሻ***

- ተማሪዎች ሃዉልት ለምን እንደሚሰራ እና እንዴት እንደሚሰራ  በፊት ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲገልፁ በመጠየቅ፣ ይህን ምዕራፍ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ሃዉልት ማስተላለፍ የሚችለዉን መልእክት በመጠየቅ፤ በቡድን እንዲወያዩ አድርጉ፡፡ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡
- በያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፤ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፤ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
  - በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
  - ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
  - መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡
  - መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

    እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ፡፡
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና
- የግል እና ቡድን ፕሮጀክት፡፡

**መልስ** በተማሪ መጸሀፌ ውስጥ የውይይት ነጥቦችና ድርግቶች በተመለከተ ተማሪዎች በርዕሱ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ለይ በመመርኮዚ ተጨማሪ ገለፀና ግብረመለስ ስጡአቸዉ፡፡

**ዉይይት 4 መልስ**

ተማሪዎች ሃዉልት ለምን እንደሚሰራ እና እንዴት እንደሚሰራ እንደ አቀማመጣቸዉ ተወያይተዉ ለክፍል እነንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ የእያንዳንዳቸዉን የዉይይቱን መልእክት ከሰማችዉ በኋላ፤ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት በመጨረሻ እንደዐጠቃላይ ሃሳብ ግብረ መልስ ስጡ፡፡  ብዙ ጊዜ የመታሰቢያ ሃዉልት ለታዋቂ ሰዎች እና እንስሳት በህይወት ካለፉ በኋላ የሚሰራ ነው፡፡ በተለይ እዉቅን፣ተወዳጅነት እና ክብር ያላቸዉ ሰዎች በህይወት ሳሉ እና ከሞቱ በኋላ ሊሰራ እንደሚችላ አስረዷቸዉ፡፡

ሃዉልት ጠሚያስተላልፉ መልዕክቶች ብዙ ቢሆኑም የተወሰኑ ታሪክ፤ዕሴት፣ጀግንነት፣ብሕል እና የመሳሰሉትን ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልት ታሪክን ያስተምራል፡፡ እንዲሁም ያለፈዉ ታሪክ እንዳለ የሚያንፀባርቅ እና የሚያቆይ ነው፡፡ታሪክ ወይም የህብረተሰቡ ክንዉን የተከናወነበት ጊዜ እና ቦታ እንዳለ ለማቆየት እና ለማሳየት እንዲያገለግሉ በደንብ አስረዷቸዉ፡፡

**ዉይይት5**

በኦሮሚያ የመሚታወቁ ሃዉልቶች ወይም የመታሰቢያ ሃዉልት የሚያወቁ ካለ፤ በቡድን በመወያየት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡  እንደ ክልላችን ሆነ እንደ ሃገራችን

ለጀግኖች የተሰራ የመታሰቢያ ሃዉልቶች ብዙ ናቸው፡፡ በክልላችን ከተሰሩ ሃዉልቶችን ጥቂቶች የሚከተሉት መሆናቸውን፤ በአንዳንድ  አስረዷቸዉ፡፡

### 4.3.1. ጫሊ ሾኖ

ጫሊ ሾኖ በ1796 በያዮ ወረዳ ተወልደዉ ያደገ ሲሆን፤ በኢሉ አባቦር ከ1842-1874 አከባቢ ስያስተዳድር የነበረ ጫሊ ሾኖ ወይም አባ ቦር ናቸው፡፡ በዚህ አከባቢ በጀግንነት ሲታወቅ እንደነበር ማስረዳት፡፡

የኢሉ አባ ቦር ዞን ስያሜ ያገኘዉ፤ የአራቱ ገዳ እና ዘጠኙ እሉ ሲያስተዳደረ የነበረ ሰዉ፤ አባ ጫሊ/አባ ቦር ከተባሉ ሰዉ ነበር፡፡ ከገዳ ስርዓት ገደብ ዉጪ ያስተዳደረበት ምክኒያት፤ በስልጣን ላይ በነበረበት ዘመን ከብዙ ጠላቶች ጋር ሲዋጋ  በጀግንነት ሲመራ ስለነበር በህበረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ስላተረፉ ማስተዳደር እንደቻሉ ይነገራል፡፡.

ያዮ ከተማ የአስተዳደሩ ማዕከል ስለነበረች፤ የእሉባቦር ንጉስ ወይም ጫሊ ሾኖ ሃዉልት በያዮ ከተማ ህዳር 19 2013 ዓ.ም ወይም ታህሳስ 1 2020 እ.አ.አ ተመረቀ፡፡ የዚህ ታሪክ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል 4.1.የጫሊ ሾኖ የመታሰቢያ ሃዉልት የሚያሣይ ስዕል፡፡

**ዉይይት 4**

መምህር ከዚህ በላይ ያለዉን የመታሰቢያ ሃዉልት ከጫሊ ሾኖ አጭር ፅሁፍ  ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲግለጹ  ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

## 4.3.2. አብሼ ገርባ

አቢሼ ግርባ የአባ ዱላ ኦዳ ቡሉቅ ልጅ ሲሆኑ፤ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ አከባቢ የነበሩ ናቸው፡ ፡ ገርባ ሁሩባ እንደ ገዳ ስርዓት በኦዳ ቡሉቅ ተመርጠዉ፤ እንደ አባ ዱላ ከ185.-1854 ሲያገለግሉ ነበር፡፡ አራት አመት ከአገለገለ በኋላ፤ ገርባ ህይወታቸዉ አለፈ፡፤ አቢሼ ደግሞ በዚህ በመጠቀም፤ ከአባቱ የቀረ አራት የአመት ለማገልገል ጥያቄ አቀረበ፡፡ ይህ ደግሞ በገዳ ስርዓት ተቀባይነት ስለ ሌለዉ፤ሲከራከር እንደነበር እና ብዙ የሚደግፉ ወጣቶች ነበራቸዉ፡፡

በመጨረሻም አቢሼ በ1855 አባ ዱላ በመሆን የቀሩት አራት አመታትን ቢጠናቀቅም ስልጣን አልለቀቁም፤ በመቀጠል አስተዳደሩ፡፡በሆሮ አከባቢ የጎጃም ወረራ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይመጣ ነበር፡፡ አቢሼ ስዋጋ ስለነበር ከሰዎቹ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ፡፡.

ከጎጃም የመጡ አቢሼን ተዋግተዉ ማሸነፍ ስላቃታቸዉ፤ ለመያዝ ዘዴ ዘየዱ፡፡ ሰላም እንፈልጋለን በማለት፤ መልዕክት ፈረስ ከወርቅ በመስራት ላኩለት፡፡በዚህ ሁኔታ አቢሼ ራስ ደረሱን የጎጃም የጦር ኃላፊ ከነበሩ ጋር ተገኛኝተዉ እንዲነጋገሩ አመቻቹ፡፡ በኦሮሞ ህግ መሰረት በመማል ከጎጃም የመጡ እና አቢሼ አጠናቀቁ፡፡ ከዚያ በኋላ የጎጃም ሰዎች ሰልፈኞቻቸዉን ደብቀዉ ሆሮ ውስጥ ስፍራ እንዲይዙ አደረጉ፡፡ አቢሼ ደግሞ በፊት የተስማሙበት ጉዳይ ስላሌ ሰልፈኞቹ የሰፈሩበት ቦታ ወደ ጎዳ ኮኮር የተሰኘዉ ቦታ ሄዱ፡፡ እዛ ከደረሱ በኋላ፤እንደ ኦሮሞ ባህል መሰረት የታጠቁት መሳሪያ ታጥቀዉ ወደ ዉይይት ቦታ ስለማይገባ፤ ትጥቁን ፈትተዉ ወደ ድንኳን ገቡ፡፡ እሱ እንደ ገባ የተባባሉትን በመካድ፤ በደንብ አሰሩ፡፡አቢሼ እንደያዙ ለሰልፈኞቹ ለማስተዋወቅ ከበሮ መቱ፤ በቅፅበት ከተደበቁበት በመዉጣት፤ አቢሼ ይዛቸዉ ሄዶ የነበረዉን ወታደሮች መዋጋት ጀመሩ፡፡ አቢሼ ክህደት ተፈፅመዉበት በመያዙ እሱም ወታደሮቹም ለአንደ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተሸነፉ፡፡

ብዙ የአቢሼ ወታደሮችም ተሰዉ፡፡ የካቲት 13 1877 አቢሼ ወደ ጎጃም በመዉሰድ አሰሩ፡ ፡ ካሰሩ በኋላ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ገደሉት፡፡ ለዚህ ጀግና መታሰቢያነት በሆሮ ጉዱሩ ዞን ሻምቡ ከተማ በፈረስ ላይ ተቀምጠዉ ጦር ይዘዉ፤ ጀግንነት እና ታሪኩን የሚገልጽ የመታሰቢያ ሃዉልት ተሰርቶላቸዉ፤ ግንቦት 30 2013 ዓ.ም እንደተመረቀ ለተማሪዎች በደንብ አስረዳ/ጂ፡፡  የዚህ ጀግና ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል 4.2. የአቢሼ ገርባ የመታሰቢያ ሃዉልት ፡፡

ዉይይት 5

መምህር ከዚህ በላይ ያለዉን የመታሰቢያ ሃዉልት ከአብሼ ገርባ አጭር ፅሁፍ  ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲገለጹ  ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

## 4.3.3. ባካር ዋሬ

ባካር ዋሬ የተወለዱ በምስራቅ ሃረርጌ ጃርሶ ወረዳ ነበር፡፡ ባካር ዋሬ በኦሮሞ ትግል ታሪክ ውስጥ በብዙ ነገር ይታወቃሉ፡፡ በተለይ በምስራቅ ኦሮሚያ ውስጥ የሚኖሩ አሮሞዎች፣ በነፍጠኞች ወራሪ ኃይል /የምኒልክ ወታደሮች በጥር 6 1887 በተደረገዉ ጦሪነት፣ የኦሮሞ ጦር መሪ ማን እንዲሆን ከተወያዩ በኋላ፣ ባካር ዋሬ እንዲመረ መረጧቸዉ፡፡ ይህ ጀግና ብርቱ፣ጅግንነት፣አዋቂ እና ከፍተኛ የማስተዳደር ችሎታ ነበራቸዉ፡፡

በጫል ጨለንቆ በተካሄደ ጦርነት የተነሳ ጀግናዉ የኦሮሞ ጦር መሪ ባካር ዋሬ በዚሁ በጦርነት እግሩ ተቆረጠ፡፡ እግሩ እንደተቆረጠ ሳያዉቁ፣ ዉጊያ እስኪያልቅ ሲዋጋ እንደነበረ ይነገራል፡፡እግሩ የት እና እንዴት እንደተቆረጠ የሚታወቅ ነገር ስለሌለ፣ ሃራርጌ አከባቢ ያሉ ሰዎችም እንደ ምሳሌ ሲጠቀሙ ጠፍተዉ ያልተገኘ ነገር ካለ . ***"እቺ ቡቴ ሚላ ባካር ዋሬ"***ትርጉሙም ጠፍተዉ የቀረ የባካር ዋሬ እግር እንደ በማለት ይናገራሉ፡፡ በዙህ ጦርነት ብዙ ሰዎች አልቀዉ ነበር፡፡ ይህ እልቂት እስከ ዛሬ **ጫሊ ጨለንቆ** በመባል ይታወቃል፡፡

ለዚህ ጀግና መታሰቢያ የሚሆን ከነ ፈረሳቸዉ የተሰራ የመታሰቢያ ሃዉልት በጨለንቆ ሰማዓታት ውስጥ መጋቢት 25 2015 እ.አ.አ ተሰርተዉ እንደተመረቀ ለተማሪዎች በደንብ አስረዱ፡፡የዚህ ጀግና ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል 4.3. የባካር ዋሬ የመታሰቢያ ሃዉልት የሚያይ ስዕል፡፡

**ወይይት 6**

መምህር ከዚህ በላይ ያለዉን የመታሰቢያ ሃዉልት ከባካር ዋሬ  አጭር ፅሁፍ  ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲገለጹ  ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

## 4.3.4. የአኖሌ ሰመአታት መታሰቢየ ሃዉልት

የአኖሌ **ሰመአታት መታሰቢየ** ሃዉልት በምስራቅ አርሲ ሄጦሳ ወረዳ ይገኛል፡፡ የኦሮሞ አርሲ የነፍጠኛን ወረራ በመከላከል፣ በተለይ ከ1881-1886 እ.አ.አ ከፍተኛ ጦሪነት አድርጓል፡፣ ምኒልክ በተለያየ ጊዜ ለ6ኛ ዙር ወደ አርሲ ሲያዘምት በነር፡፡ አርሲን መቆጣጠር ባይችልም ከፍተኛ ዋጋ ከፍሏል፡፡ ምኒልክ  በጊዜዉ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ በግዢ እና ከአዉሮፓ በሚያገኝ  ድጋፍ የበላይነት ቢኖሮዉም፣ በአርሲ ከአካሄደዉ ጦርነት ከሁሉም አደገኛ እና ደም የፈሰሰበት ነበር፡፡  በፊታቸዉ የተደቀነውን ኃይል ለመስበር፣ ምኒልክ የጦር መሳርያ ብቻ አልተጠቀመም ነበር፡፡ ህዝቡን ለማማረር ወንዶችን  የቀኝ እጅ እና ሴቶች ደግሞ ጠታቸዉን መቁረጥ እንደ አላማ ይዘዉ ነበር፡፡

ኦሮሞ ያሳለፋቸዉን ታሪክ አጥንተዉ ለማስታወስ፣ የዛሬዉን ለማጠናከር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የአኖል ሰማዕታት ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ የአኖሌ ሃዉልት ዲዛይን እና ስራ የነፍጠኛ ጥቁን ስርዓት በኦሮሞ ላይ የፈፀመ ድርጊት እንዴት እንደ ነበረ እና ቦታዉን የሚገልፅ ነው፡፡ የዚህ ሃዉልት ስራ ዋና አላማ፣ እንደዚ አይነት አስነዋሪ ድርጊት እንዳይደገም እና የሚቀጥነው ትዉልድ እንዲማሪበት ለማድረግ እንደሆነ ለተማሪዎች በደንብ አስረዱ የዚህ ሃዉልት ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ የተወሰደ ነው፡፡



ሰዕል 4.4. የአኖሌ ሰማዕታት መታሰቢያ ሃዉልት

**ዉይይት 7**

*መምህር ከዚህ በላይ ያለዉን የአኖሌ ሰማዕታት መታሰቢያ ሃዉልት እና አጭር ፅሁፍ ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲገለጹ  ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡*

### 4.3.5. ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ

ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ በ1920 በሰሜን ሸዋ ዞን ሰላሌ አከባቢ ተወለዱዉ እንዳደጉ ለጀግኖች የተፃፉ ብዙ ፅሁፎች ይመሰክራሉ፡፡ ጣሊያንን የሚዋጉ ሽምግ ተዋጊዎች አባል ነበሩ፡፡ በመጨረሻም በሶማሊያ ሞቃዲሾ እድሜ ልክ ተበይኖበት/ተፈርዶበት ታሰረ፡፡ እንግሊዝ በ1940 ሞቃዲሾን ወርራ ነጻ እስክትወጣ ድረስ እዛ ነበሩ፡፡ ከዛ በኃላ ተፈተዉ በኬንያ የዉትድርና ስልጠና ወሰዱ፡፡ ወደ ሃገራችን  በመመለስ በሆሎታ የጦር አሰልጣን በመሆን ሲያገለግሉ ነበር፡በ1954 ማዕረጉን ከፍ በማድረግ በፌጥኖ ደራሽነት ተሾሙ፡፡ በዚህ ጊዜ ሲታገል የደቡብ አፍሪካ ፕረስደንት ነልሰን ማንዴላን አሰለጠኑ፡፡ ሰኔ 1964 ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ የመጫ እና ቱላማ እርዳታ ድርጅት ሆኑ፡፡ በዚህ ድርጅት እርዳት ኦሮሞዎች እንዲማሩ እና እራሳቸዉን እንዲችሉ ስያስተምር ነበር፡፡ ይህ ደግሞ

ኃይለ ስላሴ እና ግብርአበሮቹን በጣም አናደዳቸዉ፡፡ ይህ ድርጅት እንዲዘጋ፣ የድርጅቱ አባል የነበሩ እንዲያዙ ሌሎች እንዲገደሉ እና የቀሩት ከሃገር እንዲሰደዱ ተደረገ፡፡ ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸዉ በኋላ፤ ወደ እድሜ ልክ እስራት ተቀየረላቸዉ፡፡ ሰኔ 1974 ኃይለ ስላሴ ከስልጣን ወርደዉ ደርግ ወደ ስልጣን ሲመጣ፤ ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ በገለምሶ ከታስረበት ሰብረዉ በመዉጣት ወደ ፊንፊኔ ተመለሱ፡፡

የደርግ መንግስትም በፖሊስ ኃይል ቁጥጥር ስር እንዲዉሉ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡ ብርጌደር ጀነራል ታደሰ ብሩ በመሰወር የጦርነት ንቅናቄ ወታደሮችን በሸዋ ማደራጀት ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም እሱን በመካድ ያዙኣቸዉ፤የሞት ፍርድም ተፈረደባቸዉ፡፡ ከብዙ የኦሮሞ አመራሮች ጋር መጋቢት 18 1975 ዓ.ም ተገደሉ፡፡ ቢሞቱም ስለ ማንነት፣ባህል እና አፋን ኦሮሞ በማስተማር ያበረከቱት አስተዋፅኦ ትልቅ ነበር፡፡ ስለዚህ በሰሜን ሸዋ ዞን ፍቼ ከተማ የብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ የመታሰቢያ ሃዉልት ግንቦት 25 2019 እ.አ.አ ተሰርቶላቸዉ እንደተመረቀ ለተማሪዎች በደንብ አስረዱ፡፡

የዚህ ሃዉልት ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል. 4.5. **ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ የመታሰቢያ ሃዉልት**

## ዉይይት 8

መምህር ከዚህ በላይ ያለዉንየብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ የመታሰቢያ ሃዉልት እና አጭር ፅሁፍ ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲገለጹ ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

### 4.3.6. በላይ ዘለቃ ቅልጡ

የዘር ሃረጉ ከወሎ ኦሮሞ ቦረና የሚባሉ ከኦሮሞ ቱላማ የዘር ግንድ በ1904 ተወለዱ፡፡ በላይ በሽምግ ተዋጊነት ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ዘዴ ጣሊያኖች እና ግብራበሮቻቸዉን እረፍት ሲያሳጣ ነበር፡፡ በተለያዩ ጦር ሜዳዎች ጣሊያንን በማሸነፍ ጀግንነቱን እስመስክሯል፡፡ የኦሮሞ ጀግና በላይ ዘለቀ የጦርነት ስልት ማሸነፍ ያቃታቸዉ የጣሊያኖች ተስፋ ቆረጡ፡፡ የዚህን እና የሌሎች ጀግኖች ጥንካሬ እና ጀግንነት ሃገር ለቀዉ ወጡ፡፡

ጣሊያኖች ከተሸነፉ በኋላ ኃይለስላሴ ለአምስት (5 አመት) ሸስተዉ ከነበረዉ ከእንግሊዝ ሃገር ሲመለሱ፤ እንደ ሌሎች ጀግኖች ወደ ስላጣን ላመጣ ይችላል በምል፤ በላይዘለቀ እንዲያዙ አደረገ፡፡ ተይዘዉም ወደ ፊንፊኔ ተወሰደዉ እድሜ ልክ ፍርድ ተፈረደባቸዉ፡፡ ነገር ግን እስር ቤቱን ሰብረዉ ወደ ጎጃም ሲመለስ፤ ከመንገድ ተይዘዉ ወደ ፊንፊኔ ከተመለሱ በኋላ፤ በሞት እንዲቀጡ በኃይለስላሴ መንግስት ስርዓት ተፈረደባቸዉ፡፡ ተወለደዉ በ35 አመታቸዉ ጥር 5 1937 ከሁለት ወንድሞቹ ጋር ተሰቀሉ፡፡ ስለዚህ በምስራቅ ጎጀም ዞን ቢቸና ከተማ የበላይ ዘለቀ የመታሰቢያ ሃዉልት ጥቅምት 10 2009 እ.አ.አ ተሰርቶላቸዉ እንደተመረቀ ለተማሪዎች በደንብ አስረዱ፡፡ የዚህ ሃዉልት ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል. 4.6. **የበላይ ዘለቀ ቅልጡ የመታሰቢያ ሃዉልት**

በአጭሩ ከመታሰቢያ ሃዉልት የሚገነዘበት የሚንችለዉ ነገር፣ እነዚህ ሃዉልት ለምን እንደተሰሩ እና የሚያስተላልፈዉን መልዕክት ነው፡፡

ዉይይት 9

**መምህር**፣ ከዚህ በላይ ያለዉንየበላይ ዘለቀ የመታሰቢያ ሃዉልት እና አጭር ፅሁፍ ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲገለጹ  ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

### 4.3.7. ሃጂ አደም ሳዶ

ሃጂ አደም ሳዶ በ1877 በባሌ ዞን ጎባ ወረዳ ተወለዱ፡፡ ከ15 እድሜ ጀምረዉ  ቅኝ አገዛዝ በመቃወም ወደ ትግል ተቀላቀሉ፡፡ የምኒልክ ጦር በሌ በወረሩ ጊዜ፣ የነፍጠኝነት ስርዓት በሃገራችን ተቀባይነት አይኖረዉም በማለት ህዝቦችን ሲያነሳሱ ነበር፡፡ ሃጂ እንደ ሌሎች ታጋዮች በጠመንጃ አፈሙዝ ብቻ አይታመኑም ነበር፣

***"ነፃ የሚያወጣን፣የለዉጥ አዕምሮ ነው ይላሉ"***፡፡ በቤሌ የጀመረዉ የትጥቅ ትግል፣ በፊንፊኔም እንዲጠናከር የባሌ አመራሮች እና ታጋዮች እነ ጀነራል ዋቆ ጉቱ እና ጀነራል ሁሴን ቡኔ የፃፉት ደብዳቤ፣ የኦሮሞ ትግል ምስጢር ያለዉ ለብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ ለማድረስ ስሄድ በመንግስት ፖሊሶች ተይዘዉ ታሰሩ፡፡በዛም ወደ ፊንፊኔ በመጡ ጊዜ የያዙት ደብዳቤ ምስጢር እንዳይወጣ ወደ መፅዳጃ ቤት ገብቶ ለመጣል አስቦ የዎጣሉ ብሎ ስለሰጋ በአፉ አኝከዉ ዋጣዉ፡፡ የተፃፈ ደብዳቤ ይህን የትጥቅ ትግል እንዴት

አድርገዉ ተጋግዘዉ ከግብ እንዲያደርሱ የሚያሳይ ነበር፡፡ ሽንት ቤት ሄደዉ ሲመለሱ የመንግስት አካል/ የመንግስት ፖሊሶች አባል ይዘዉ፤ ያመጡትን ሰነድ እንዲሰጣቸዉ ጠየቋቸዉ በዛም መፈተሽ ጀመሩ፡፡ ሃጂ ግን ደብዳቤዉን ዉጦት ስለነበሩ ***"ሆዳችን የወጣዉን ነገር በሆዳችን መለስን"*** በማለት ምስጢሩ አእናዳይወጣ አደረጉ፡፡

ሃጂ አደም ሳዶ የባሌ ህዝብ በኃይለስላሴ ንጉስ  ላይ ስያደርግ የነበረዉን ትግል በቀዳሚነት ድርሻዉን ሲወጣ ነበር፡፡ በመጨረሻም የመጫ እና ቱለማ ድርጅት አባል እና በኦሮሞ ባሌና አርሲ መሃል ድልድይ በመሆን ሲያገናኛቸዉ እንደነበር የዚህ ጀግና ታሪክ ያስረዳል፡፡

ከሃጂ አደም ሳዶ የሚንማር ነገሮች፡-

- በእዉነት ለኦሮሞ ህዝብ መናገር፡፡ (ሃጂ አደም ለቆሙት እዉነት ለማደናቀፍ፤ ብዙ ጊዜ መሬት፣ገንዘብ እና በተለያዩ ነገር ለማታለል ሞክረዉ አቃታቸዉ)
- ቁርጠኝነት
- ራስን መስጠት
- ለያዙት አላማ መቆም፤ ምስጥር ጣበቂነትና ወዘተ….ነቸዉ ፡፡

ሃጂ አደም በ1981 ህይወታቸዉ ሲያልፍ፤ በትዉልድ ቦታቸዉ ተቀበሩ፡፡ እሳቸዉ ቢቀበሩም ታሪካቸዉ ግን ከዘመን ወደ ዘመን በትዉልድ ይታወሳል፡፡ ስለዚህ በባሌ ዞን ጎባ ከተማ የሃጂ አደም ሳዶ የመታሰቢያ ሃዉልት ተሰርቶላቸዉ እንደተመረቀ ለተማሪዎች በደንብ አስረዱ፡፡ የዚህ ጀግና ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ የተወሰደ ነው፡፡

.



ስዕል. 4.7. የሃጂ አደም ሳዶ የመታሰቢያ ሃዉልት፡፡

ዉይይት10

**መምህር፤** ከዚህ በላይ ያለዉንየበላይ ዘለቀ የመታሰቢያ ሃዉልት እና አጭር ፅሁፍ ተማሪዎች ምን እንደ ተረዱ በቡድን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል እንዲግለጹ  ቅድመ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡

**የምዕራፉ  አረት መልመጃ መልስ**

**የእዉነት ወይም ሐሰት ጥያቄዎች መልስ**

1.ሐሰት 2. እውነት 3.ሐሰት 4. እዉነት 5. እዉነት
6.አውነት 7. እውነት 8. ሐሰት 9. ሐሰት 10. ሐሰት
11. እዉነት 12. እዉነት 13. እዉነት

## የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

1. መ
2. መ
3. ለ
4. መ
5. ለ
6. መ
7. መ
8. መ

# ምዕራፍ 5: የስነ-ጥበባት ትስስር

ለዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-----------4

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ዉጤቶች**:

**ከዚህ  ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ስነ-ጥበባት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያላቸዉን ትስስር በመለየት ያደንቃሉ፡፡
- ስነ-ጥበባት በሌሎች ትምህርት ውስጥ ያለዉ ጥቅም ይነግራሉ፡፡
- ስነ-ጥበባት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለዉ ትስስር ያስረዳሉ፡፡

**መግቢያ**

ስነ-ጥበባት ሌሎች ትምህርት ለማስተማር ያላቸዉ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ሥነ-ጥበባት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሌላዉን ትምህርት አይነት ለማስተማር እና ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ በአንደኛ ደረጃ እና ቅድመ መደበኛ ክፍል የሚማሩ ካለ ስነ-ጥበባት አይታሰብም፡፡አሳ ከወኃ ውስጥ ወጥታ ካለ ወኃ መኖር እንደማትችል ሁሉ፣ ከስነ-ጥበባት ዉጪ የቅድመ መደበኛ ትምህርትም ሆነ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ማሳካት አይቻልም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ጥበባት ለአከባቢ ጥበቃ እና በተለያዩ ጉዳዮች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያለዉ ድርሻ ሰፊ ነው፡፡በአጭሩ በሰዉ ልጅ እለት እለት ኑሮ ምቹ እና ቀላል በማድረግ ስነ-ጥበባት ከፍተኛ ጥቅም አለዉ፡፡

**የምዕራፉ አንኳር ይዘቶች**

## 5.1. የስነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርት ዓይቶችና ከወቅታዊ ጉደይ ጋር መያያዝ

ለዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-----------2

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት**:

**በዚህ ትምህርት መጨረሻ ፡**

- ስነ-ጥበባት በሌሎች ትምህርት ውስጥ ያለዉ ጥቅም ይነግራሉ፡፡
- ስነ-ጥበባት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለዉ ትስስር ያስረዳሉ፡፡

### 5.1.1. ስነ-ጥበባትን ከወክታዊ ጉዳዮች ጋር በመያያዝ መስታማር

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ማሳየት
- የቡድን እና ጥንድ ዉይይት፡፡
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- ፕሮጀክት

### የተምህርት መርጃ መሳሪያ

የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚያስፈለጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያ፡፡

- እስቱዲዮ
- ስዕል
- ፖስተር
- ሎጎ/የአንድን ድርጅት ምልክት የሚያሳይ

### የመምህር ድርሻ

- ተማሪዎች ስነ-ጥበባት ሌሎች ትምህርቶችን በማስተማር ውስጥ ያለዉን ጠቀሜታ/ፋይዳ በተመለከተ፣ በፊት ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲገልፁ በመጠየቅ፣ ይህን ምዕራፍ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ስነ-ጥበብ ከሌሎች ትምህርት ጋር ያለዉን ትስስር በተመለከተ፣ በቡድን እንዲወያዩ አድርጉ፡፡ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡
- በያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡት ተግባራት በፊት ያላቸዉን ችሎታ እና እዉቀት በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚረዱ፣ መምህራን ወደ ማብራሪያ ከመግባታቸው በፊት፣ በተሰጡት ተግበራት ላይ በቡድን እንዲወያዩ እና ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንድረዱ ይረዳቸዋል፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች የቤት እና ክፍል ስራ በመስጠት እንዲሰሩ አድርጉ፡፡.
- ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ትክክለኛዉን ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- *መምህራን በሚታስተምሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡*
- *መጎናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡*

  *እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባራት መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሰሩት የትምህርቱ ተግበራት ውጤቱ ካልተመዘገበላቸዉ እና እንዲሁ የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች በሂደት ውስጥ የመሰላቸት ባህሪይ ስለሚያሳዩ የሚሰጣቸዉ ተግባራት ዋጋ እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡*

***ተከታታይ የምዘና***

- *የግል እና ቡድን ፅብረቃ፡፡*
- *ፖርትፎሊዮ*
- *የቃል ጥያቄ*
- *የሙከራ ጥያቄ*
- *ፈተና*
- *የግል እና ቡድን ፕሮጀክት፡፡*

***ለተግበር መልስ*** *በተማሪ መጸሀፌ ውስጥ የውይይት ነጥቦችና ድርግቶች በተመለከተ ተማሪዎች በርዕሱ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ለይ በመመርኮዚ ተጨማሪ ገለፀና ግብረመለስ ስጡአቸዉ፡፡*

**ተግባር 5**

*ተማሪዎች ስነ-ጥበብ ሌሎች ትምህርት መማር ውስጥ ያለዉን ድርሻ ምን እንደሆነ በቡድን ተወያይተዉ የዉይይቱን ዉጤት ለክፍል እነንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ ለተማሪዎች ሞራል በመስጠት በመጨረሻ እንደዐጠቃላይ ሃሳብ ግብረ መልስ ስጡ፡፡ ስነ-ጥበብ በሌሎች ትምህርት ውስጥ ያለዉ ጥቅም ብዙ እንደሆነ ባለፈዉ ትምህርት ተምራቿል፡፡ ለምሳሌ፡-*

- በምልክት እና በስዕል በመጠቀም ማስተማር፤ የመማር ተነሳሽነትን/ፍላጎት የሚያበለፅግ መሆኑን አስረዱ፡፡
- ተማሪዎች የትምህርት ይዘቱን በቀላሉ እንዲረዱ ያግዛቿል፡፡
- በቀላል መንገድ ከአከባቢያቸዉ ጋር በመተዋወቅ፤ ፍላጎት እና የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ይረዳቿል፡፡.
- በሌላ ትምህርት የሚማሩ አላማ፤ ከግብ እንዲደርስ እንደ ድልድይ ያገለግላል፡፡.
- የተማሪዎችን ተሳትፎ ይጨምራል፡፡ ሌሎች ትምህርት መማር ውስጥ ያለዉ የስነ-ጥበብ ጥቅም ሲንመለከት፤ የተማሪዎች በራስ መተማመን ለማጎለበት እና የመሳሰሉትን መጥቀስ እንደሚቻል በደንብ አስረዱ፡፡

  ለምሳሌ፡- ሂሳብ በመማር ውስጥ ያለዉ የስነ-ጥበብ ድርሻ በሁለት ይዘቶች እንመልከት፡፡ እነርሱም፡-

### ከ1-4 የሚማሩ ይዘቶች

ከ1-4 የሚማሩ የሂሳብ ይዘት እንዱ ሰለ ሂሳብ ስሌቶች እና መሰረታዊ ምልክቶች ናቸው፡፡

የሂሳብ ስሌቶች አራት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

**+, -, × እና ÷**

መሰረታዊ ምልክቶች  እንደ፡

•, $<$ , ≤ እና ≥


ማየት እንችላለን፡፡ ስሌቶችም ሆነ ይህ ምልክቶች ቅርፅ ናቸው፡፡ ቅርፃቸዉ ደግሞ ከመስመር የተሰሩ ናቸው፡፡ ቅርፅ እና መስመር ደግሞ የስነ-ጥበብ መሰረታዊ ናቸው፡፡

### ከ 5ኛ ክፍል በላይ ያሉ ይዘቶችን፡

ከ5ኛ ክፍል በላይ የሚሰጡ ይዘቶችና ሲንመለከት፡-

☞ **የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆች**

የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆችየሚባሉ፡-





ስዕል .5.1.የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆች ስዕል

እነዚህ ሁሉም ቅርፅ እና ቅርፃ ቅርፅ ናቸው፡፡ ቀርፅም ኆነ ቅርፃ ቅርፅ ከስነ-ጥበብ መሰረታዊ ባህሪይ ናቸው፡፡

☞ / **ግራፍ**(graph)

ቀመር መስመር ወይም ቅርፅ/ፎርም ይሰራል፡፡በአጭሩ የስነ-ጥበብ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡.




ስዕል. 5.2. የግራፍ ሥዕል

ስነ-ጥበብ ሌሎች ትምህርት ለማስተማር ያለዉ ጥቅም ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በሌሎች ትምህርት ማስተማር ውስጥ ይህ የማይባል ድርሻ አለዉ፣ በተጨማሪም እንደምሳሌ የህብረተሰብ ትምህርት አይነት ቢንወስድ፣ የተለያዩ ካርታዎች አለዉ፡፡ ካርታ ደግሞ ስዕል ነው፡፡ ሥዕል ደግሞ ከስነ-ጥበብ ስራ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የስነ-ህይወት (ባዮሎጂ) ትምህርት ቢንወስድ በተለያዩ ሥዕሎች የተደገፈ ነው፡፡

በትምህርቱ አይነት የሚንጠቀማቸዉ ሥዕሎች ሁሉም የስነ-ጥበብ ስራዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የስነጥበብ ትምህርት ሌሎች ትምህርት ማስተማር ለማሳካት ያለዉ ጥቅም ብዙ መሆኑን ለተማሪዎች በደንብ አስረዳዱ፡፡  ስነ-ጥበባት ከተለያዩ ትምህርት አይነት ጋር ትስስር አለዉ፡፡ በጤና ላይ የተዘጋጀ የትያትር  ስራ፣ ይዘቱ ስለ በሽታ እና የመተላለፊያ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡በመማር እና ማስተማር ላይ የተዘጋጀ ትያትር ስለ ትምህርት ይሆናል፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ስነ-ጥበባት በማንኛዉም ትምህርት አይነት ጋር ትስስር አለዉ፡፡

### 5.1.2. የስነ-ጥባባት ትምህርትን ከሌሎች ትምህርት ዓይቶችና ከወቅታዊ ጉደይ ጋር በመያያዝ መስተመር

**የተሰጠው ክፍለ ጊዜ……………….2**

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

**በዚህ ትምህርት መጨረሻ ፡**

- ስነ-ጥበባት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያላቸዉን ትስስር በመለየት ያደንቃሉ፡፡
- ስነ-ጥበባት በሌሎች ትምህርት ያለዉን ጥቅም ይለያሉ፡፡

**አቢይ የትምህርት ይዘቶች፣**

- ስነ-ጥበብና ጤናን መገናኘት
- ስነ-ጥበብ ለእኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ጋር መገናኘት

**የመርጃ የትምህርት መሣሪያ**

- የልምምድ ክፍል(ትያትር አደራሽ)
- ለትያትር የምዉል አልባሳት
- የተለያዩ ቁሳቁሶች ለትያትር

**የይዘት መብራሪያ**

ጥበብ የተለያዩ አገልግሎት ይኖሯል፡፡ ለምሳሌ ፓሊቲካ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊን ለማንፀባረቅ ጉልህ ሚና ይጨወታል፡፡ በፓሊቲካ ማዕዘን ስንመለከት በፊልሙ ታሪክ ውስጥ በተላይ በሁለተኛ ዓለም ጦሪነት ውስጥ ፊልም ጥልቅ የፕሮፐጋንዳ መሳሪያ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡

የተለያዩ ችገሮች ስከሰት ለምሳሌ ተላላፊ በሽታዎች፣ድንገተኛ ባሽታዎች ኤ.ች.አይ.ቪ.፣ ኮቪድ -19፣እና የወባ በሽታ እንዲሁም የትራፊክ አደጋ ስከሰት ስነ-ጥበብን ተጠቅመን የመከላኪያመንገዶች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ይቻላል፡፡ በምንም ግዜ ስለ-ስነ ጥበብ ስነሳ በሦስት ትላልቅ ነገሮች ውስጥ መታየት አለባቸዉ፡፡ እነርሱም፣

- መዝናናት

- ማስተማር
- የህበረተሰብ ችግርን መፍታት

ሰነ-ጥበብ ለተለያዩ አገልግሎት ብዉሉም ከነዚህ ከላይ በሦስት ነገሮች በተጠቀሱ ዉጭ አገልግሎት ልኖራቸዉ ይችላል፡፡ የማህበረሰብ ችግር ለማፍታት ስነ-ጥበብ ከፍታኛ ሚና አሏቸዉ፡፡

ለምሳሌ ፤ አንድን የማህበረሰብ ችግር ለመፍታት አንድ ድምፃዊ የህበረተሰቡን ችግር በዘፈን ምልዕክቱን በማስተላለፍ እንደ መሳሪያ ለጠቀምበት ይችላል፡፡ እንዲሁም በትያትርም ሆነ በፊልም ዘዉግ ሕበረተሰባችን ያለበት የማህበረዊዉ እዉነታ የመገለጫ መንገድ የትያትርና ፊልም ጥበብ ነው፡፡

**የመምህር ድርሻ**

- በዚሁ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች ወደ መምህር መብራሪያ ሳያልፉ በፊት የተረት-ተረት ልምዳቸዉንና ግንዛቤያቸዉን ክፍል ውስጥ እርስበረሳቸዉ በማከፈል የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ግንዛቤያቸዉን በማጨበጥ መብራሪያ እንዲሰጣጡ፣እንዲሁም እንዲጠነከሩ አድርጉ፡፡
- የተሰጡ  ክንዉኖችና ጥያቄዎች በለተላይ፣የቤት ሥራ፣የግል ሥራ፣የጥምድሥራ፣የቡድን፣ ፕሮጀክት እንዲሰሩ አቅጣጫ አሳዩ፡፡
- በአከባቢያቸዉ ያሉ ተረት-ተረቶችን ወደ ትያትርና ፊልም ጥበብ ቀይሮዉ እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡
- በዚህ ትምህርት ምዕራፍ ውስጥ የተሰጠት ሁለም ተግባራት ተማሪዎች እንዲሰሩ ክትትል አድርጉ፡፡
- መነናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በታች ለሰሩ ተማሪዎች እገዛ ስለሚያስፈልጋቸው ልዩ ትኩረት በመስጠት በትርፍ ጊዜ ለነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- ተማሪዎች መነናፀፍ ከሚገባቸው የትምህርት ብቃት በላይ ከሰሩ፤ መበረታታት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸዉን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለወደፊት ከዚህ የበለጠ ጠንክረው እንዲሰሩ መበረታታት አላባቸው፡፡

**ተከታታይ የምዘና**

- የግል መብራሪያ
- የቡድን ሥራ ጽብሪቃ
- ቃለ-መጠየቅ
- የቤት ሥራ
- ንሁስ ፈተና
- መጠቃለየ ፈተና
- የተማሪዎች ኑበሬ  ወረቀት

**የምዕራፍ 5 መልመጃ መልስ**

**ሀ. "የእዉነት ይም ሐሰት"መልስ**

**1. ሐሰት  2. ሐሰት  3.እዉነት  4.እውነት**

# የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ
# 8ኛ ክፍል

## የመማር ዉጤቶች፡

## በዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች:-

- ሙዚቃ፣ ቲአተርና ቪዲዮ በመጠቀም የሚገኙበትን ሁኔታ፣ የምሰማቸዉን ስሜት፣ ሀሳባቸዉንና መልዕክታቸዉን ያስተላልፋሉ
- የህትመትና የቅርጻ ቅርጽ (የሸክላ ጭቃና ፔፐር ማሼ) ስራ ይሰራሉ
- የኢትዮጵያ የሙዚቃና የሙዚቃ መሳሪያ አይነት ይገልጻሉ
- የሙዚቃ ኖታን በመጠቀም ምልክት እያሳዩ በተለያዩ ጊዜያት($^6/_8$, $^2/_2$ , $^2/_4$ ) ሶልፌጆን ይማራሉ
- ኖታን (ምትና ማረፊያ ) በመጠቀም የህገራችን የሙዚቃ ስልት የጫወታሉ (ሹሩቤና አምባሰል)
- የተለያዩ ባህሎች ዉዝዋዜ ይጫወታሉ
- ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሣሪያና ዉዚዋዜን በባህላዊ መልኩ ይገልጻሉ
- የህብረሰቡን የሀገር በቀል ዕዉቀት በቲአተር፣ በፊልም፣ በቪዲዮ ይገለጻሉ
- የስነጥበባት ስራዎችን ያደንቃሉ
- የቀድሞ ጊዜያት የህዉልት ምልክቶችና የእጅ ስራ ጥበቦችን ያደንቃሉ
- የስነጥበባት ትምህርትን ከሌሎች  የትምህርት አይነቶችና ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በዜማ፣ በዉዝዋዜ፣በቲአተር፣ በቪዲዮ… በማስተሳሰር ይረዳሉ
- የእጀጥበባት ትርጉም፣ ግንኙነት፣ አተገባበር ይረዳሉ፡፡

| የትምህርት ዐበይት ነጥቦች | ይዘት | የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች | ምዘናና ክትትል |
|---|---|---|---|---|
| ስነጥበባትን መረዳት | **ምዕራፍ** 1:የስነ-ጥበባት ግንዛቤዎች-16<br>1.1 የቅርጻ ቅርጽ አላባዊያን ድርሻ ና ጥቅሞች (ክፍለ ጊዜ )<br>1.2 የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝትና ውዝዋዜ (ክፍለ ጊዜ )<br>**1.2.1 ትላልቅየኢትዮጵያ ሙዚቃ ዓይነቶች**<br>(ክፍለ ጊዜ )<br>1.3 የትያትር እና የፊልም ጥበብ ፕሮዳክሽን አላባውያን<br>(ክፍለ ጊዜ ) | • የሀገራችን አበይት የሙዚቃ አይነቶችና የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲሁም የዉዝዋዜ አይነቶችን በስም እንዲማሩ ማድረግ<br>• በማሳየት ማስተማር<br>• የቲአተርና መሰረታዊ መድረክነ የፊልም ዝግጅት በማስረዳት ማስተማር | • የልምምድ ክፍል<br>• የድምጽና የቪዲዮ ማጫወቻ፣<br>• የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎችና ስዕሎች<br>• ወረቀት፣ እርሳስ፣ ክራወንና በአከባቢ የሚገኙ መሳሪያዎች<br>• በአከባቢ የሚገኙ የጽህፈትመሰሪያዎች | ✓ ምልከታ<br>✓ ዉይይት<br>✓ የግል ገለፃ<br>✓ የቡድን ገለፃ<br>✓ ግብረመልስ<br>✓ ፖርትፎሊዮ<br>✓ የቃል ጥያቄ<br>✓ የቤት ሥራ<br>✓ ፈተና |
| የፈጠራ ክሂሎት | ምዕራፍ 2: የፈጠራ ችሎታ<br>(ክፍለ ጊዜ 20)<br>2.1 ሶልፌጅዮን በኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት(በአንቺ ሆዬ ለኔ እና አምባሰል)<br>(ክፍለ ጊዜ 5) | • ሀትመትና የቅርጻ ቅርጽ ስራዎችን (የሽክላ ጭቃና ፔፐር ማሼ) መስራት ማስተማር<br>• የሙዚቃ ኖታን በመጠቀም ምልክት እያሳዩ በተለየዩ ጊዜያት ($^{6}/_{8}$, $^{2}/_{2}$, $^{2}/_{4}$ ) ሶልፌጅ በመቁጠር ማስተማር<br>• ኖታና ማረፊያን በመጠ | • የልምምድ ክፍል<br>• የልምምድ አደራሽ<br>• የድምጽና የቪዲዮ ማጫወቻ፣<br>• የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎችና ስዕሎች<br>• ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>• የሚመቱ፣ ሌሎች | ▪ ምልከታ<br>▪ የግል ገለፃ<br>▪ የቡድን ገለፃ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ<br>▪ የቤት ሥራ<br>▪ ፈተና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2.2 ባህላዊ ውዝዋዜ (ክፍለ ጊዜ 4)<br>2.3 የትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን (ፈጠራ፣አጭር ታሪክ መፃፍና መመዘን) የትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን (ፈጠራ፣አጭር ታሪክ መፃፍና መመዘን) (ክፍለ ጊዜ5 )<br>2.4 የህትመትእና ቅርጻቅርጽ ስራ (የሸክላ አፈር፣ ፔፐር ማሼ) (ክፍለ ጊዜ6) | ቀምየሀገራችን የሙዚቃ ስልት ሹሩቤንና አምባሰልን በማደራጀት እንዲጫወቱ ማድራግ<br>• ባህላዊ የሙዚቃ ውዝዋዜን በተግባር በማሳየት ማሳየት<br>• የቲአተርና የፊልም አዘገጃጀት እንዲፈጥሩና እንዲየሄሱ በማድረግ ማስተማር | በአከባቢያችን የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች<br>▪ የእስኮች ወረቀት፣ ማጣበቂያ እርሳስ፣ ክራወንና በአከባቢ የሚገኙ መሳሪያዎች<br>• ለቲአተሮች የሚያስፈልጉ አልባሳትና መሳሪያዎች | |
| ባህላዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች | ምዕራፍ 3: የስነ-ጥበባት ባሂልና ታሪክ (ክፍለ ጊዜ 14)<br>3.1 የሙዚቃ ባህላዊ ገጽታ፣የሙዚቃ መሳሪያዎችና ውዝዋዜ (ክፍለ ገዜ5)<br>3.2 የቅርፃ ቅርፅ (ሃዉልት) እና የጥንት ዘመን የእጅ ሙያ ታሪክ (ክፍለ ጊዜ 5)<br>3.3 በአከባቢያችን የሚታወቁ ተረቶችን በትያትርና ፊልም ጥበብ መልክ ማቅረብ (ክፍለ ጊዘ 4) | • የሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያና የዉዝዋዜ ታሪክ ከባህል አንጻር በማጥናት ማስተማር<br>• ሀገር በቀል እዉቀትን በቲአተርና በፊልም ተጠ ቅመዉ በተግባር ማስተማር<br>• በትዕይንትና በምልከታ ማስተማር | • የልምምድ ክፍል<br>• የልምምድ አደራሽ<br>• የድምጽና የቪዲዮ ማጫወቻ፣<br>• የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎችና ስዕሎች<br>• የጽህፈት መሳሪያዎች | ▪ ምልከታ<br>▪ ዉይይት<br>▪ የግል ገለፃ<br>▪ የቡድን ገለፃ<br>▪ ግብረመልስ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ<br>▪ የቤት ሥራ<br>▪ ፈተና |
| የስነጥበባት ሳቢነት | ምዕራፍ 4:<br>4 የስነጥበባት መስህብነት (ክፍለ ጊዜ 17)<br>4.1 የስነጥበባት ስራዎችን በተግባር | •የስነጥበባት ተግባራትን በአድናቆት ማስተማር<br>•የስነጥበባት ተግባራትነ በተገባር እያሳዩ ማስተማር | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የልምምድ አደራሽ<br>▪<br>▪ የሚመቱ፣ የክር፣ የሚነፉና ሌሎች | ✓ ምልከታ<br>✓ ዉይይት<br>✓ የግል ገለፃ<br>✓ የቡድን ገለፃ<br>✓ ግብረመልስ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የማስተማር ጥቅሞች የማስተማር ጥቅሞች (ክፍለ ጊዜ 4)<br>4.2 በተግባር የሚታዩ የስነጥበብ ስራዎችን በማነሳጸር ማወዳደር (ሙዚቃ፣ ዉዝዋዜ፣ትያቲር ምስለድምጽ) (ክፍለ ጊዜ 4)<br>4.3 ቅርጻ ቅርጽ፣የሃዉልትእና የእጅ ስራ ሙያ ምልክቶች መልዕክት (ክፍለ ጊዜ 5) | • በቅርጻ ቅርጽና የድሮ ጊዜ የእጅጥበብ ስራዎች የሚተላለፉ መልዕክቶችን አክብረዉ በማድነቅ ማስተማር | በአከባቢያችን የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የመድረክ ጨዋታ…<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎችና ስዕሎች<br>▪ የድሮ ጊዜ እጀጥበባትና ስዕሎች | ✓ ፖርትፎሊዮ<br>✓ የቃል ጥያቄ<br>✓ የቤት ሥራ<br>✓ ፈተና |
| ትስስር፣ ግንኙነትና ተግባራዊነት | **ምዕራፍ** 5:<br>5. **የስነ-ጥበብት ትስስር**<br>(ክፍለ ጊዜ 11)<br>5.1 የስነ-ጥበባት ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶችና ትኩረት ከሚሹ ወቅታዊ ጉዴዮች ጋር ማስተሳሰር (ክፍለ ጊዜ 11) | • የስነጥበባት ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶችና ትኩረት ከሚሹ ወቅታዊ ሁኔታዎችን (በዜማ፣ በዉዝዋዜ፣በቲአተር፣ በቪዲዮ… ) ጋር በማስተሳሰር ማስተማር<br>• ጠቃሚ የሆኑ የድሮ ጊዜ የእጅጥበብ ስራዎችን አተገባበር ማስተማር | • የልምምድ ክፍል<br>• የልምምድ አደራሽ<br>• የድምጽና የቪዲዮ ማጫወቻ፣<br>• የሚመቱ፣ የክር፣ የሚነፉና ሌሎች በአከባቢያችን የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የመድረክ ጨዋታ…<br>• እጀጥበባት፣ ፖስተርና ስዕሎች | ▪ ምልከታ<br>▪ የግል ገለፃ<br>▪ የቡድን ገለፃ<br>▪ ግብረመልስ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ<br>▪ የቤት ሥራ<br>▪ ፈተና |